
# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ



## 6ኛ ክፍል

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ

# አማርኛ

## እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 6ኛክፍል

አስማምቶ አዘጋጆች፡- -አሸናፊ ደጉ

-በቀለ ሙዳ

-ስናፍቅሽ አስፋው

በአዲስ አበባ ት/ቢሮ ተዘጋጅቶ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ትምህርት ቢሮ እና በዲላ መምህራን ትም/ኮሌጅ የተስማማ

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት ትምህርት ቢሮ

ማውጫ ገጽ

ምዕራፍ አንድ 1
ባህላዊ አለባበስ 1
ክፍል አንድ፡ ማዳመጥ 2
ክፍል ሁለት፡- ማንበብ 4
ክፍል ሶስት፡- ቃላት 8
ክፍል አራት፡- ጽሕፈት 9
ክፍል አምስት ሰዋስው 10
ማጠቃለያ -, 13
ምዕራፍ ሁለት 14
ታዋቂ አትሌቶች 144
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ 15
ክፍል ሁለት፡- ማንበብ 16
ክፍል ሶስት፡- ቃላት 20
ክፍል አራት፡- ጽሕፈት 22
ክፍል አምስት፡- ሰዋስው 24
ማጠቃለያ 25
ምዕራፍ ሶስት 27
ቃላዊ ግጥም 27
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ 28
ክፍል ሁለት፡- ማንበብ 31
ክፍል ሶስት፡- ቃላት 39
ክፍል አራት፡- ጽህፈት 40
ክፍል አምስት፡- ሰዋስው 41
ማጠቃለያ 43
ምዕራፍ አራት 444
ዘመናዊ እርሻ 444
ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ 45
ክፍል ሁለት፡- ማንበብ 46

ክፍል ሶስት፡- ቃላት ______ 52
ክፍል አራት፡- ጽሕፈት ______ 54
ክፍል አምስት፡- ሰዋስው ______ 55
ማጠቃለያ ______ 58

**ምዕራፍ አምስት ______ 59**

**ቱሪዝም ______ 59**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ______ 61
ክፍል ሁለት-ማንበብ ______ 63
ክፍል ሶስት ቃላት ______ 72
ክፍል አራት ጽሕፈት ______ 74
ክፍል አምስት ሰዋስው ______ 75
ማጠቃለያ ------------------------------75

ምዕራፍ ስድስት ______ 76

**አደንዛዥ ዕፆች ______ 76**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ______ 77
ክፍል ሁለት ማንበብ ______ 79
ክፍል ሶስት ቃላት ______ 84
ክፍል አራት ጽሕፈት ______ 85
ክፍል አምስት ሰዋስው ______ 88
ማጠቃለያ ______ 910

ምዕራፍ ሰባት ______ 92

**የጥላቻ ንግግር ______ 92**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ ______ 93
ክፍል ሁለት ማንበብ ______ 95
ክፍል ሶስት ቃላት ______ 99
ክፍል አራት ጽሕፈት ______ 102
ክፍል አምስት ሰዋስው ______ 104
ማጠቃለያ ______ 1074

ምዕራፍ ስምንት 108

**ኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ በኢትዮጵያ 108**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ 109

ክፍል ሁለት ማንበብ 111

ክፍል ሶስትቃላት 116

ክፍል አራት ጽሕፈት 118

ክፍል አምስት ሰዋስው 121

ማጠቃለያ 1231

ምዕራፍ ዘጠኝ 1242

**ባህላዊ ክንዋኔዎች 1242**

ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ 125

ክፍል ሁለት ማንበብ 127

ክፍል ሶስት ቃላት 132

ክፍል አራት ጽሕፈት 134

ክፍል አምስት ሰዋስው 138

ማጠቃለያ 139

ምዕራፍ አስር 140

**ሴቶችን ማብቃት 140**

ክፍል አንድ ማዳመጥ 141

ከፍል ሁለት፡- ማንበብ 143

ከፍል ሶስት፡- ቃላት 148

ክፍል አራት፡- ጽሕፈት 151

ከፍል አምስት ሰዋስው 155

ማጠቃለያ 157

## ❖ መግቢያ

ይህ መጽሐፍ አማርኛን በአፍ መፍቻ ቋንቋነት የሚማሩ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በቋንቋዉ በብቃት ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍእንዲችሉ፤ በተጨማሪም የቃላት እና የሰዋስው ዕውቀት እንዲያገኙ ለማድረግ የተዘጋጀ የሥርዓተ ትምህርት አካል ነው። ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ ለዚህ የክፍል ደረጃ ሥርዓተ ትምህርትና ለሚሰጠው የትምህርት ሽፋን መረጃ ይሰጣል።ከዚህም በላይ ተማሪዎችና ወላጆች በትምህርት ቤት የተከናወኑ ተግባራትን ለማስቀጠልና ይበልጥ ለማዳበር በጋራ ለመሥራት ያስችላቸዋል።

## ❖ መሰረታዊ መርሆዎች

- ተማሪዎች በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ።
- ለነዚህ የማዳመጥ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች የተጻፉ ምንባቦችን ካዳመጡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ይናገራሉ።
- በቀጣይም በማሕበረሰቡ ውስጥ አስፈላጊ ስለሆኑ የምንባብ ይዘቶችና ርዕሰ ጉዳዮች ይማራሉ። ስለነዚህ የምንባብ ይዘቶች የተጻፉ ምንባቦችን ካነበቡ በኋላ፣ በእነሱ ላይ በመመስረት ይጽፋሉ።
- አራቱን ክሂሎች ከላይ በተቀመጠው መሰረት ከተማሩ በኋላ በክፍል ሶስትና አምስት የቀረቡትን የቃላትና የሰዋስው ትምህርቶችን በየምዕራፉ በተገለጸው ዓላማ መሰረት ይማራሉ።
- ተማሪዎች በግላቸው ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ካሉ ጓደኞቻቸው ጋር ይማራሉ።

## ❖ በቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር መማር

- ተማሪዎች በትምህርት ቤት የሚቀስሟቸውና በቤታቸው ከወላጆቻቸው ጋር የሚሠሯቸው በርካታ ትምህርታዊ ተግባራት አሉ። ከእነዚህ ተግባራት ቢያንስ የተወሰኑትን ከልጆቻቸው ጋር በጋራ እንዲሠሩ ይጠበቃል።

1) የየዕለቱን ትምህርት ይዘት በተመለከተ ከቴሌቪዥን፣ከሬዲዮ ወይም ከድረ ገጽ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ አዳምጡ ወይም ተመልከቱ፤
2) ልጆች የተሰጣቸውን የቤት ሥራ ሲሠሩ፣ራስን ወይም ሌሎች የቤተሰብ አባላትን በቃለ መጠይቅ፣ንግግርን በመጻፍ ወይም በንግግር ልምምድ ወቅት በመሳተፍ አብሮ መሥራት ተገቢ ነው፤

3) ወላጆች የሳምንቱን ወይም የዕለቱን የምንባብ ይዘት ወይም ርዕስ ጉዳይ ልጆቻችሁን በመጠየቅ ተረዱ።በትምህርት ቤት ያነበቧቸውን ምንባቦች በጋራ አንብቡ። ይህንንም ልጆች ወይም ወላጆች ለብቻ ወይም በየተራ በማንበብ ሊተገብሩት ይችላሉ፤
4) ልጆቻችሁን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለምንባቡ ተወያዩ፤
5) ስለ ርዕሰ ጉዳዩ የሚያወሱ ሌሎች ጽሁፎችን ከመጻሕፍት፣ከጋዜጦች ወይም ከመጽሔቶች ፈልጋችሁ አንብቡ።
6) በግል ያንብቡ (ልጆች ራሳቸውን ችለው በግላቸው እንዲያነቡ አበረታቱ)ከዚያም ስላነበቡት ጉዳይ ተወያዩ፤
7) ልጆች በክፍል ውስጥ ምንምን እንደተማሩ ደብተራቸውን በጋራ ተመልከቱ፤ስለምን እንደተማሩና ምን እንደተሰማቸው ጥያቄዎች በማንሳት ተወያዩ፤
8) የመጻፍ ችሎታቸውን ለማዳበር የተማሯቸውን ዝርዝር ክሂሎች በመረዳት ምን እንደተማሩ ለማወቅ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ልጆቹን ጠይቋቸው። ለምሳሌ፡-የቃላቱ ፊደላት በተገቢ ሁኔታ ተጽፈዋል/ ተሰድረዋል ወይ? በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ /መካከል/ ያሉት ሥርዓተ ነጥቦች (አራት ነጥብ፣ነጠላ ሰረዝ፣ድርብ ሰረዝና የመሳሰሉት) በተገቢ ቦታቸው ገብተዋል ወይ?ወዘተ.
9) ልጆች አጫጭር ደብዳቤዎች (ለምሳሌ፡- ለቤተሰብ አባላት ወይም ለጓደኞች) እንዲጽፉ ወይም በዕለቱ ወይም በሳምንቱ ስለተከሰቱ ጉዳዮች ወይም ስለ አንድ ጉዳይ ያላቸውን አስተያየት ወዘተ.እንዲጽፉ አበረታቷቸው።

# ምዕራፍ አንድ

## ባህላዊ አለባበስ

❖ **ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡- ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፡-**

- ✓ በተገቢው ፍጥነትና በትክክለኛ ድምጸት ታነባላችሁ፡፡
- ✓ የቃላትን አገባባዊ ሥርዓት ተከትላችሁ አረፍተነገር ትመሰርታላችሁ፡፡
- ✓ ከምንባቡ ውስጥ ለወጡ ቃላት ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ ቃላትን እያጣመራችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ✓ በፅሁፍ ውስጥ ያሉ ስርዓተ ነጥቦችን በተገቢው መንገድ ትጠቀማላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ፡ ማዳመጥ

## የሀገር ባህል ቀሚስ









### ቅድመ ማዳመጥ

**መልመጃ 1፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. ከስዕሉ በመነሳት ምንባቡ ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?
2. ከስዕሉ ላይ ምን ምን ባህላዊ ቀሚሶችን አስተዋላችሁ?

### የማዳመጥ ሂደት

‹‹የሀገር ባህል ቀሚስ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን መረጃ ሰጪ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ የምንባቡን ጭምቅ ሀሳብ ለማወቅ ማስታወሻ እየያዛችሁ አዳምጡ፡፡

### አዳምጦ መረዳት

**2፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ባዳመጣችሁት መሰረት በቃል መልሱ፡፡**

1. ባህላዊ አለባበሶች በምን በምን አጋጣሚዎች ይለበሳሉ?
2. ባህላዊ አለባበስ ከዘመናዊ አለባበስ በምን ይለያል?
3. ባህላዊ ልብሶች ከምን ከምን ይዘጋጃሉ?
4. በምንባቡ ውስጥ ከቀረበው የባህል አለባበስ ሌላ ምን አይነት ባህላዊ አለባበስ ታውቃላችሁ?

5. ባህላዊ አለባበሶቻችን ጠብቀን ለማቆየት ከእያንዳንዳችን ምን ይጠበቃል?

፫፡-በአዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ለሚከተሉት ቃላት አውዳዊ ፍቺ ስጡ

ሀ. ትውፊት
መ. በየፈርጁ
ለ. ሀገረኛ
ሠ. አጥቢያ
ሐ. ሽማ ሰሪ

መልመጃ-2

የምታውቁትን አንድ ባህላዊ አለባበስ መርጣችሁ ስለዚያ ባህላዊ አለባበስ፣አሰራርና መቼ እንደሚለበስ ከሚያውቁ ሰዎች ጠይቃችሁለክፍል ጓደኞቻችሁ የቃል ንግግር አድርጉ

# ክፍል ሁለት፡- ማንበብ

## ባህላዊ አለባበስ



### ቅድመ ንባብ

**መልመጃ-3**

**፩፡-ተማሪዎች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. በርዕሱና በምስሉ መካከል ያለውን ዝምድና ግለጹ፡፡
2. ርዕሱን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለ ምን የሚናገር ይመስላችኋል?

፪፡-ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትንቃላትበመነጠልና በማጣመር አንብቡ፡፡

| ተ.ቁ | ነጥሎ ማንብበ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|---|
| 1 | በ-የ- አ-ለባበስ -ኦች - ኣችን | በየአለባበሶቻችን |
| 2 | የ -ሁለንተን - ኣዊ | የሁለንተናዊ |
| 3 | ከ - አስ- ተዳደግ - ኣችን | ከአስተዳደጋችን |
| 4 | የ - ሚ-መረት- ኡ - በት -ና | የሚመረቱበትና |
| 5 | ተ-ወዳጅ - ነት - ኣቸው | ተወዳጅነታቸው |
| 6 | የ - ተ - ዥጎረጎረ | የተዥጎረጎረ |
| 7 | ባህል - ነት -ኣቸው - ን | ባህልነታቸው |

## የንባብ ሂደት

የሚከተለውን ምንባብ በለሆሳስ አንብቡ ፡፡ ስታነቡ ግልፅ ያልሆነ ሀሳብ ሲያጋጥማችሁ በማሳታወሻ ፃፉ፡፡

ኢትዮጵያዊያን እንደየባህላችን በልዩ ልዩ ቅርፅና ቀለማት ያሸበረቁ ባህላዊ አለባበሶች አሉን፡፡እነዚህ ባህላዊ አለባበሶቻችን የሁላችንም የሁለንተናዊ ማንነታችን መገለጫዎች ናቸው፡፡ ይህ ውብ የሆነ ያልተበረዘና ያልተከለ ባህላዊ አለባበሳችን ሀገራችንን ከሌሎች የአለም ሀገራት እንድንለይ ያደርገናል፡፡ ባህላዊ አለባበሳችን ከማንነታችን የሚመነጭ ሲሆን ከተለያዩ ሀገራት በሚመጡና እኛም ወደ ተለያዩ ሀገራት ስንሄድ በአሸበረቀው ባህላዊ አለባበሳችን ውበት የሚደነቁት ብዙዎች ናቸው፡፡

ከሌሎች ሀገራት አለባበሶች የኛን ልዩ የሚያደርገው የራሳችንን የፈጠራ ስራ የሚያካትት መሆኑ ነው፡፡ በተለያዩ የደስታና የሀዘን ስሜቶች የምንላበሳቸው ባህላዊ አለባበሶቻችን ለስራው የሚሆኑትን ጥሬ እቃዎች፣የሚመረቱበትና ወደልብስነት የሚለወጡት በራሳችን ጥበብ ነው፡፡እንደየባህላችን በተለያዩ ጥልፎች፣ጌጣጌጦችና ጥበቦች ያሸበረቁ ባህላዊ ልብሶችን ለብሰን ልዩ ልዩ ባህላዊ ክንውኖችን ስንከውን ልዩ ህብር ፈጥሮ ስሜትን ይቀሰቅሳል፡፡

❖ ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት ምን ተረዳችሁ? ቀጣይስ ክፍል ስለምን የሚናገር ይመስላችኋል?

ባህላዊ አለባበሶቻችን ከጊዜ ወደ ጊዜ አለምአቀፋዊ ተወዳጅነታቸው እየጨመረ መጥቷል፡፡ የተወዳጅነት ሚስጥሩም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ቱሪስቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረመምጣቱ ነው፡፡ በአለባበሳችን ተማርከው እነሱም የተለያዩ አልባሳትን እየገዙ በመልበስ ሀሴትን መጎናፀፍ ችለዋል፡፡ እነዚህም ባህላዊ አለባበሶች በተለያዬ አመታዊ ክብረበዓላትና ህዝባዊ በአላት ማለትም በሰርግ፣በጥምቀት፣በአረፋና በመውሊድ መሰል አጋጣሚዎች ይለበሳሉ፡፡

እነዚህ ባህላዊ አለባበሶች እንደየህብረተሰቡ ባህል በተለያዩ ቀለማት የተዥጎረጎሩ ሆነው በቀሚስ፣በነጠላ፣ በኮትና በሱሪ መልክ ልንለብሳቸው እንችላለን፡፡ የወንድና የሴት፣የወጣቶችና የአዛውንቶች፣ እንደየእድሜ ደረጃችን የባህሉ አሻራ ያረፈባቸውም ናቸው፡፡ በዚህ መካከል በየአለባበሳችን የባህል ልውውጥ መኖሩን የሚያሳዩ ሲሆን የማንነታችን መገለጫዎች ከመሆናቸው ባሻገርም አምረንና ተውበን እንድንታይ ያስችላሉ፡፡

ባህላዊ አለባበሶችን ለቀጣዩ ትውልድ የምናወርሳቸው ውድ ቅርሶቻችን ናቸው፡፡ ‹‹ ባለቤት ያቃለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም›› እንደሚባለው ባህላዊ አለባበሶቻችንን ለተተኪው ትውልድ ለማስተዋወቅና ለማስተላለፍ እንዲሁም ባህልነታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ሁላችንም የድርሻችንን ልንወጣ ይገባል፡፡

ምንጭ፡-ፈንታሁን እንግዳ፣2000 ታሪካዊ መዝገበ ሰብዕ ከጥንት እስከዛሬ ለ6ኛ ክፍል ማስተማሪያ በሚያመች መንገድተሻሽሎየቀረበ፡፡

## አንብቦ መረዳት

**፫:-ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል ከሆኑ ‹‹ እውነት›› ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ‹‹ሐሰት›› በማለት በጽሁፍ መልሱ፡፡ ለምትሰጡት መልስ ምክንያት አቅርቡ፡፡**

1. ባህላዊ አለባበሶቻችን የማንነታችን መገለጫዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡
2. ባህላዊ ልብሶቻችን ከሌሎች የሚለዩት የራሳችን የፈጠራ ውጤት በመሆናቸው ነው፡፡
3. ባህላዊ ልብሶቻችን ከጊዜ ወደጊዜተወዳጅነታቸው እየጨመረ መጥቷል፡፡
4. የባህል አልባሳትን ይዘት ጠብቆ የማቆየት ድርሻ የባህልና ቱሪዝም ብቻ ነው፡፡
5. በማህበረሰብ ባህልና እሴት መሰረት ባህላዊ አልባሳት በተለያየ ቅርፅ ይዘጋጃሉ፡፡

**፬:-ለሚከሉት አዳዲስ ቃላት በጽሁፍ ፍች ስጡ፡፡**

ሀ. ቱሪስት      ሐ. ሁለንተናዊ      ሠ. ባህላዊ

ለ. ሀሴት      መ. መገለጫ      ረ. ያልተበረዘ

**መልመጃ-4፡- ተማሪዎች ከዚህ በታች ባህላዊ አለባበስ ከሚለው ርእስ ተቀንጭቦ የቀረበውንምንባብ በጥንድ በጥንድ በመሆን ደቂቃ እየያዛችሁ በተገቢው ፍጥነትአንብቡ፡፡**

ባህላዊ አለባበሶቻችን ከጊዜ ወደ ጊዜ አለማቀፋዊ ተወዳጅነታቸው እየጨመረ መጥቷል፡፡ የተወዳጅነት ሚስጥሩም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ቱሪስቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ መምጣቱ ነው፡፡ በአለባበሳችን ተማርከው እነሱም የተለያዩ አልባሳትን እየገዙ በመልበስ ሀሴትን መጎናፀፍ ችለዋል፡፡ እነዚህም ባህላዊ አለባበሶች በተለያየ አመታዊ ክብረ በዓላትና ህዝባዊ በዓላት፣በሰርግ፣ በጥምቅት፣በአረፋና በመውሊድ መሰል አጋጣሚዎች ይለበሳሉ፡፡

# ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## መነጠልና ማጣመር

❖ ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በመነጣጠል አሳዩ

ሀ. አስተማሪዎቻቸዉን

መ. ኢትዮጵያዉያን

ለ. ጊዜያዊነት

ሠ. አስተምሮአቸዋል

ሐ. ህብረተሰባዊነት

**መልመጃ- 5**

**፩፡-ከዚህ በታች በ ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩትበፍቺተመሳሳይ የሆኑትን በመምረጥ አዛምዱ**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1) በጋራ | ሀ. ልዩ |
| 2) ውርስ | ለ. ብቸኛ |
| 3) ደንብ | ሐ. ብዙ |
| 4) ነጠላ | መ. ስርዓት |
| 5) መላምት | ሠ. ግምት |
| 6) ብርቅየ | ረ. በቡድን |
| | ሰ. ስጦታ |

**ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አውዳዊ ፍቺ መሰረት አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ሀ. ያሸበረቀ

ለ. ፈጠራ.

ሐ. አሻራ

ሐ. ኣሻራ

መ. አዛውንት

ረ. ጥበብ

**፪፦ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ቃላት በፍቺ ልዩ ሆነውን አውጡ፡፡**

1. ሀ. አማረረ. ለ. አመሰገነ ሐ. አሞገሰ መ. አወደሰ
2. ሀ. ጥድፊያ ለ. ትጋት ሐ. ንቃት መ. ልግመኛ
3. ሀ. ቀላወጠ ለ. ለመነ ሐ. ደከመ መ. ተመፀወተ
4. ሀ. ተወዘፈ ለ. ተዘረጋ ሐ. ተዘረፈጠ መ. ተኀለተ
5. ሀ. እንደነገሩ ለ. ለይስሙላ ሐ. ለማስመሰል መ. ለቁም ነገር

## ክፍል አራት፦- ጽሕፈት

### የአንቀፅ ቢጋር አዘገጃጀት

**መልመጃ- 6**

**፩፡ ከዚህ በታች የቀረበውን ምሳሌ መነሻ በማድረግ አንቀፅ ለመፃፍ የሚያስችላችሁን ቢጋር አዘጋጁና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ምሳሌ፦-

የቢጋር ርዕስ፦- የሀበሻ ቀሚስ አሰራር

1. የሀበሻ ቀሚስ ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ግብአቶች
   1.1. የሀበሻ ጥጥ
   1.2. ------------------------------------------------
   1.3. ------------------------------------------------
   1.4. ------------------------------------------------
   1.5. ------------------------------------------------

2. የሀበሻ ቀሚስ ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ የሸማኔ ቁሳቁሶች

2.1.መወርወሪያ

2.2. ------------------------------------------

2.3. ----------------------------------------

3. የሀበሻ ቀሚስ ለማስጌጥ የሚያገለግሉ

3.1. መርፌ
3.2.----------------------------------------

3.3. ----------------------------------------

፪፡- ያዘጋጃችሁትን የቢጋር ንድፍ መነሻ በማድረግ ተገቢውን ስርአተ-ነጥብ በመጠቀም አንቀፅ ጻፉ፡፡ የፃፋችሁትን ጽሁፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በየተራ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል አምስት ሰዋስው

### የተጸውዖና የወል ስም

የተጸውዖና የወል ስም

ማስታወሻ፡-

ሀ.የተጸውዖ ስም የምንለው ለአንድ ነገር ብቻ የሚውል መጠሪያ ወይም መታወቂያ በመሆን የሚያገለግል ቃል ነው፡፡

ምሳሌ፡- የሰው ስም፡- ስምኦን፣ዘመዴ ፣ያስሚን፣ ቤተልሔም ወዘተ.

የእፅዋት ስም፡- ዋንዛ፣ጽድ፣ዋርካ፣ ዝግባ ወዘተ .

የፍራፍሬ ስም፡- ሙዝ፣ ማንጎ፣ አቡካዶ፣ ብርቱካን ወዘተ.

የአትክልት ስም፡- ድንች፣ ካሮት፣ ቀይስር፣ጎመን ወዘተ.

ለ. የወል ስም የሚባለው ደግሞ አንድ አይነት የሆኑ ነገሮችበጋራየሚጠሩበት ስም(መጠሪያ) ነው፡፡

ምስሌ፡-ሰው፣እፅዋት፣ ተማሪ፣ገበሬ፣ ነጋዴ፣ መምህር፣ መሃንዲስ፣እንስሳት፣ዶክተር፣ መጓጓዣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**መልመጃ፡-7**

**፩፡- ከላይ በቀረበው ማስተዎሻ መሠረት ቀጥሎ የቀረቡትን ስሞች የተጸውዖና የወል ስም በማለት በምሳሌው መሰረት መድቡ።**

**ምሳሌ፡-ሀ. ወጣት፡-የወል ስም**

**ለ. ሴት፡-የወል ስም**

**ሐ. አለሙ፡- የተፀውዖ ስም**

**መ. ሀሊማ፡- የተፀውዖ ስም**

መሃመድ ፍየል በሬ ፖሊስ ትዝታ ሀና መኪና

ገበሬ ሀገሬ ተራራ ጥራጥሬ አዋሽ ሀይቅ ባህር ዛፍ

| ተ.ቁ | የተጸውዖ ስም | የወል ስም |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |

**፪፡- ከላይ ከተዘረዘሩት የስም አይነቶች ውጭ ሌሎች አምስት አምስት የተጸውዖና የወል ስሞችን በደብተራችሁ ፃፉና አረፍተ ነገር ስሩባቸው።**

**❖ ምዕላድ**

**ምዕላድ ትርጉም አዘል የሆነ የመጨረሻ ንዑስ ክፍል? ነው። የመጨረሻ የተባለበት ምክንያት አንድ ምዕላድ ወደሌላ አነስተኛ ትርጉም ያለው ክፍል**

ሊከፈል ስለማችል ነው፡፡ ምዕላድ ነፃና ጥገኛ በሚል በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ሀ. ነፃ ምዕላድ፡- ትርጉም ያለው ብቻውን መቆም የሚችል ቃል ነው፡፡

ምሳሌ፡- ተራራ፣ ቤት፣ሰው፣ ልጅ፣ ድንጋይ ወዘተ.

ለ. ጥገኛ ምዕላድ፡- ብቻውን መቆም ስለማይችል ወደ ነፃ ምዕላዶች ተጠግቶ በግራ ወይም በቀኝ እየገባ የራሱን ትርጉም የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ትርጉም የሚኖረው ሁልጊዜም በነፃ ምዕላዶች ላይ ሆኖ ሲገባ ብቻ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ስለ-፣ ወደ-፣ እንደ-ከ-፣የ-፣-ዎች፣-ኦች፣ወዘተ.

- **መልመጃ፡-8፡-** ከተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት በምሳሌው መሰረት ጥገኛ ምዕላዱን ከዋና ቃሉ ለይታችሁ አስቀምጡ

አስደነገጠ አስ-ደነገጠ

| ተ/ቁ | ቃል/ሀረግ | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|---|
| 1 | ስለሀገራችን | | |
| 2 | መምህራን | | |
| 3 | እየሔደች | | |
| 4 | ወደመፅሀፉ | | |
| 5 | ሰላማዊነታችን | | |
| 6 | ስለፍቅራቸው | | |
| 7 | ቤታችንን | | |
| 8 | ተማሪዎቹ | | |
| 9 | ግንባሬ | | |
| 10 | ተበላሁ | | |

## ማጠቃለያ

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ለቃላት ተመሳሳይና አውዳዊ ፍቺ ሰጥተናል፡፡ የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ማለት የቃሉ አቻ ፍቺ ሲሆን አውዳዊ ደግሞ ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ያለው አገባባዊ ፍቺ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ቢጋር በማዘጋጀት አንቀጽ ፅፋናል፡፡ አንቀጽ አንድን ሀሳብ ብቻ መነሻ አድርጎ በኃይለ ቃልና በመዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች የሚዋቀር ጽሁፍ መሆኑን ተረድተናል፡፡የተጸውኦ ስም የአንድ ነገር መጠሪያ መሆነኑን፣ የወል ስም ደግሞ አንድ አይነት የሆኑ ነገሮች የጋራ መጠሪያ እንደሆነአይተናል፡፡ በመጨረሻም የምዕላድን ምንነት፣የነፃና ጥገኛ ምዕላድ ማስታወሻ ጽፋችሁ ጥገኛ ምዕላድን ከዋና ቃል ለይተን አይተናል፡፡

### የክለሳ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን የማጠቃለያ ጥያቄዎች ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

1. ተማሪዎች የቃላትን ተመሳሳይና አውዳዊ ፍቺ ምንነትና ልዩነት ግለጹ ፡፡
2. ስለተጸውዖና የወል ስሞች የተረዳችሁትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡
3. የሚከተሉትን ቃላት ወደነፃና ጥገኛ ምዕላድ ተንትኑ

ሀ. በሬዎች ለ.መኪናችን ሐ.ደብተሩ መ. ተማሪዎቻችን

# ምዕራፍ ሁለት

## ታዋቂ አትሌቶች

ከምዕራፉ የሚጠበቅ ውጤት፡ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ ከቅጥያዎች ውስጥ ዋና ቃል ትለያላችሁ
- ✓ ቅጥያዎችን በማጣመር ቃላት ትመሰርታላችሁ፡፡
- ✓ የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ ዋናውን ሀሳብ ትገልፃላችሁ፡፡
- ✓ የስርዓተ ነጥቦችን ትርጉም ተረድታችሁ የንባብ ድምፀቱን በመጠበቅ ታነባላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## ‹‹ ኦሎፒክን በባዶ እግር ››



### ቅድመ ማዳመጥ

**መልመጃ፡-9**

**፩፡-ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ‹‹ኦሎምፒክን በባዶ እግር›› የሚለው ርዕስ ስለማን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ለ. በሃገራችን ካሉት ታዋቂ አትሌቶች መካከል ቢያንስ አራቱን በመጥቀስ ያስመዘገቧቸውን ድሎች ዘርዝሩ፡፡

### የማዳመጥ ሂደት

‹‹ኦሎፒክን በባዶ እግር›› በሚል የቀረበውን ትረካዊ ምንበብ የታሪኩን ቅደም ተከተል እየጠበቃችሁ አዳምጡ፡፡

## አዳምጦ መረዳት

**፩፡-ምንባቡን በጥሞና አዳምጣችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡**

1. አበበ ቢቂላ‹‹ኦሎምፒክን በባዶ እግር›› የተባለው ለምን ይመስላችኋል?
2. ሀገራቸውን ወክለው ወደሮም ያመሩት ኢታዮጵያውጣን ማን ማን ነበሩ?
3. አበበ ቢቂላ ለ1942 ዓ. ም ለሮም ኦሊፒክ ውድድር ለመመረጥ የቻለው በምን ምክንያት ነው?
4. ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ?
5. አበበ ቢቂላ የዓለምን ክብረ ወሰን ሰባብሮ ያሸነፈው በስንት ሰዓት ውስጥ ነበር?
6. ‹‹ እያሸነፈ ክብረ ወሰኖቹን በእጁ አስገባ›› የሚለው አባባል ምንን ይገልጻል?
7. ንጉሰ ነገሥቱ ለአበበ ቢቂላ የሸለሙት ምን ነበር?
   ሸ. የሮም ኦሎፒክ ሩጫን በባዶ እግሩ የሮጠው በምን ምክንያት ነበር?

**፫፡- ‹‹ኦሎምፒክን በባዶ እግር›› የሚለውን ምንባብ ታሪክ አስታውሱና ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁበየተራ ንግግር አድርጉ፡፡**

## ክፍል ሁለት፡- ማንበብ







## ‹‹ አንጸባራቂዋ እንስት››

### ቅድመ ንባብ

**መልመጃ፡-10**

**፩፡-ቅድመ-ንባብ መልመጃ**

1) አንፀባራቂዋ እንስት የሚለው ርዕስ ስለማን የሚገልፅ ይመላችኋል?
2) ስዕሉን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን እንደሚገልፅ ገምቱ፡፡

### የንባብ ሂደት

ቀጥሎ የቀረበውን ተራኪ ምንባብ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል እያስተዋላችሁ በለሆሳስ አንብቡ፡፡

ሩጫ ነፍሷ ነው፤ በህይወቷ ደስታ ይሰጣታል፤እንደ ስራ ሳይሆን እንደመዝናኛ ነው የምትቆጥረው፡፡ ‹‹ እሩጫ በቃኝ ፤ ከአሁን በኋላ አልሮጥም፣ ብየ ከቶውንም ላስብ አልችልም፤ አሸንፌ የወርቅ ሜዳሊያዎችን ማጥለቅና ብርታት የሚሰጠኝን የኢትዮጵያ ህዝብ ማስደሰት ታላቅ እርካታ ያጎናፅፉኛል›› በማለት ትናገራለች፡፡ የተወለደችው አርሲ በቆጂ ከተማ በ1977ዓ.ም ሲሆን አንድ ወንድና ሰባት ሴት ልጆችን ላፈሩት ወላጆቿ ሶስተኛ ልጅ ናት፡፡ ቤተሰቦቿ አርሶ አደር ስለነበሩ ከትምህርት ቤት መልስ በሥራ እያገዘች ነው ያደገችው፡፡

ሩጫ የጀመረችው በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስፖርት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ነው፡፡ አሰልጣኟ በጣም ጥሩ ተወዳዳሪ እንደምትሆን ዘወትር ይነግሯት ነበር፡፡ በሌላ በኩል ስለአትሌቲክስ በሚያቅና ሩጫን በሚያበረታታ ቤተሰብ ውስጥ መወለዷ እድለኛ አድርጓታል፡፡ በእሷ አካባቢ የሚኖሩ በርካታ ልጃገረዶች ሩጫ ለመለማመድና ለመወዳደር ቀርቶ ትምህርት ቤት ለመሄድም አይፈቀድላቸውም ነበር፡፡ እርሷ ግን ከእርሷ በፊት አትሌት የሆኑ የቤተሰብ አባላት ስለነበሩ ተቃውሞ አልገጠማትም፡፡ በተለይም ከሩጫ ልምምድ ስትመለስ

በቤት ውስጥ ስራ እንዳትጠመድ ከማድረግም በላይ በላቀ መንገድ ያበረታቷት ነበር፡፡

1. እስካሁን ካነበባችሁት ምን ቁም ነገር አገኛችሁ?
2. ከዚህ ቀጥሎ ያለው ፅሁፍ ስለምን የሚያትት ይመስላችኋል?

የመጀመሪያዋን የኦሎፒክ የወርቅ ሜዳሊያ ለአፍሪካና ለኢትዮጵያ ያበረከተችው የመጀመሪያዋ ሴት አትሌት ደራርቱ ቱሉ እና ለቤተሰቦቿ በሩጫ ፈር ቀዳጅ የሆነችው እጅጋየሁ ዲባባ ለእሷ አርያዎቿ ናቸው፡፡ ጥሩነሽ ዲባባ የመጀመሪያ ደረጃ ትህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ሰባተኛና ስምነተኛ ክፍል ለመማር ወደ አዲስ አበባ መጣች፡፡ ነገር ግን ምዝገባ አልፎ ስለነበረ በሁኔታው ብታዝንም ተመልሳ ወደ መጣችበት ቦታ መሄድን አልመረጠችም፡፡ ከዚህ ይልቅ በስፖርት ክለብ የምትታቀፍበትን ማፈላለግ ጀመረች፡፡እናም ታላቅ እህቷ ውጤታማ ወደሆነችበት የማረሚያ ቤቶች የስፖርት ክለብ መቀላቀል ቻለች፡፡ በፖሊስ ክለብ አባልነት ሀገሯን በመወከል የመጀመሪያዋን አለምአቀፍ ውድድር በቤልጂም በአስራ አምስት አመቷ በባዶ እግሯ በመሮጥ ‹‹ሀ›› ብላ ጀመረች ፡፡ ከዚያም በመቀጠል በአስራ ዘጠኝ አመቷ ፓሪስ ላይበተካሄደው ዘጠነኛው አለም አቀፍ (የIAAF) የአለም ሻምፒዮን ውድድር በአምስትሺ ሜትር ተወዳድራ ለሀገሯ ለመጀመሪያ ጊዜ የወርቅሜዳሊያ ማስመዝገብ ችላለች፡፡

ጥሩነሽ ሁሌም ማሸነፍን፣ጠንክሮ መስራትን ፣የቀደሙ ታታላላቆቿን አርዓያ በማድረግ ለታላቅ ስኬት እራሷን ያበቃች አትሌት ናት፡፡ ለአብነት ያህልም በ2000ዓ.ም የቤጅንግ ኦሎፒክ ውድድር ላይ በአምስት ሺ ሜትር እና በአስር ሺ ሜትር ተወዳድራ በሁለቱም ርቀቶች ድርብ ድል የወርቅ ሜዳሊያን ለሀገሯ አስገኝታለች፡፡ በዚህም ከጊዜ ወደ ጊዜ እራሷን እያሻሻለች በተወዳደረችባቸው የውድድር መድረኮች ሁሉ በርካታ ሜዳሊያዎችን ለራሷና ለሀገሯ ማስመዝገብ የቻለች ታሪክ የማይረሳት ሀገር ወዳድ አትሌት ናት ፡፡

ምንጭ፡- ‹‹ተምሳሌት መፅሀፍ ከገፅ122-123 ለ6ኛ ክፍል እንዲስማማ ተሸሽሎ የቀረበ››

## አንብቦ መረዳት

**፩፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃላችሁ ማብራሪያ ስጡ**

1. አትሌት ጥሩነሽ ዲባባ ለመጀመሪያ ጊዜየወርቅ ሜዳሊያ ያስመዘገበችበት ሀገር የት ነው?
2. ጥሩነሽ ዲባባ የተወለደችበት ልዩ ቦታ ማን ተብሎ ይጠራል?
3. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በአጭሩ ግለፁ ?
4. አትሌቷ ወደ ቤተሰቦቿ ተመልሳ ቢሆን ኖሮ ምን ይገጥማታል ብላችሁ ታስባላችሁ?
5. ተማሪዎች ከጥሩነሽ ዲባባ ህይወት ምን እንደተማራችሁ በቡድን ተወያይታችሁ ፅብረቃ አቅርቡ፡፡

**፫፡- ቀጥሎ ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. ክለብ - ቡድን፣ ስብስብ

ለ. ማጥለቅ- ማስገባት፣ መልበስ

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ደስታ | መ. አርዓያ | ሰ. እድለኛ |
| ለ. ብርታት | ሠ. አርሶአደር | ሸ. ተቃውሞ |
| ሐ. የላቀ | ረ. ዘወትር | ቀ. እርካታ |

፬:- ለሚከተሉት ቃልትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ

ምሳሌ:- 1. አብነት:- ለሌሎች ሰዎች አርዓያ መሆን

2. ተወዳዳሪ:- የተሻለ ሆኖ ለመገኘት የሚደረግ ፉክክር

ሀ. ልምድ
ለ. ስመ ጥር
ሐ. ክብረወሰን
መ. ተደናቂነት
ሠ. ኮከብ
ረ. ድርብ ድል
ሰ. ሜዳሊያ
ሸ. መድረክ

# ክፍል ሶስት:- ቃላት

## የቃላት ተመሳሳይ ፍቺ

መልመጃ:-11

፩:-በ‹‹ሀ›› ረድፍ የቀረቡትን ቃላት በ‹‹ለ›› ረድፍ ከተዘረዘሩት በፍች የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ::

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. ሙዳ | ሀ. ውለታ |
| 2. ረብ | ለ. ግምገማ |
| 3. ዛለ | ሐ. ብርድ |
| 4. ቆፈን | መ. የስጋ ቁራጭ |
| 5. በነቂስ | ሠ. ከተመ |
| 6. ወሮታ | ረ. ጥቅም |
| 7. ደራ | ሰ. ፌዝ |
| 8. ሰፈረ | ሸ. ደመቀ |
| 9. ቧልት | ቀ. በሙሉ |
| 10 ሂስ | በ. ደከመ |

**፱፡-የሚከተሉትን ቃላት በቀረበው ምሳሌ መሰረት ዋና ቃሉንና ቅጥያውን ለይታችሁ ፃፉ፡፡**

**ምሳሌ፡-** ሀ. ልጅነት=ልጅ-ነት

ለ. አይናማ=አይን-ኣማ

1. ከተወዳዳሪዎቹ
2. መረጣችሁ
3. ጓደኞቻቸውን
4. ውጤታማነታችን
5. ስኬታማነት
6. ሀገራችን
7. ወታደሮቻችን
8. ቤታቸውን
9. ሰዎቹ

**፲፡-ከዚህ ቀጥሎ ከ1-6 ለተዘረዘሩት ቃላት ተመሳሳይ ትርጉም የያዘውን ፊደል እየመረጣችሁ መልሱ፡፡**

1) ደባ ሀ. ደፈጠ ለ. በርኖስ ሐ. ካባ መ. ተንኮል
2) አያሌ ሀ. ጥቂት ለ. ትልቅ ሐ. ብዙ መ. ከባድ
3) ጎመጀ ሀ. ቋመጠ ለ. መታ ሐ. ጓጓ መ. ሀ እና ሐ
4) ማነፅ ሀ. ማቃናት ለ. መግራት ሐ. ማስተካከል መ. ሁሉም
5) ተግዳሮት ሀ. ችግር ለ. ደከመ ሐ. አረጀ መ. ፈራ
6) አለመ ሀ. ጎዳ ለ. አነጣጠረ ሐ.ቀመቀመ መ. በረበረ

**፬፡-ቀጥሎ ተነጣጥለው የቀረቡትን ቅጥያዎች በማገጣጠም ቃላት መስርቱ፡፡**

ሀ. ዘመን - ኣዊ - ነት

ለ. ክብር - ት

ሐ. ወጣት - ኡ

መ. ሴት - ዮ - ዋ

ሠ. ሽጥ - ኡ - ት

ረ. በ - ጥልቅ - ኧ - ት

ሰ. በ - አደገ - ቾ - በት

# ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

## አንቀጽ መፃፍ

❖ **አንቀጽ፡-** የሀሳብ ቁርኝት ያላቸው አረፍተ ነገሮች እርስ በእርስ ተገጣጥመው አንድን ነጠላ ሀሳብ ብቻ ለመግለፅ የሚያገለግል አነስተኛ የድረሰት ክፍል ነው፡፡ በአንድ አንቀፅ ውስጥ ሊነሳ የሚችለው ሀሳብ አንድ ብቻ ነው፡፡ ሌላ የተለየ ሀሳብ መግለፅ ካስፈለገ ሌላ አዲስ አንቀፅ መመስርተ ያስፈልጋል፡፡

አንቀፅ ሁለት መሰረታዊ አካላት አሉት፡፡እነሱም፡- ኃይለ ቃል ወይም ዋና ዓረፍተ አገር እና መዘርዝር ዓረፍተ ነገሮች ናቸው፡፡

1. **ኃይለ ቃል ወይም ዋና ዓረፍተ ነገር** የሚባለው አንቀጹ የሚያስተላልፈውን ሙሉ ሀሳብ የሚይዝ አንድ ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ በአንቀጽ ውስጥ ኃይለ ቃል በተለያየ ቦታ ላይ ሊገኛ ይችላል፡፡ ይኸውም በአንቀጽ መጀመሪያ፣ መካከል፣ መጨረሻ እና መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ነው፡፡ አንድ አንቀጽ ሊኖረው

የሚችለው ኃይለ ቃል አንድ ብቻ ነው፡፡

2. መዘርዝር ዓረፍተ ነገር ደግሞ በኃይለ ቃሉ መነሻነት የተለያዩ ምሳሌዎችንና መረጃዎችን በማቅረብ ዝርዝር ሀሳቡን ለማብራራት የሚጠቅም ነው፡፡

መልመጃ፡-12

፩፡-ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱን በመምረጥ በመረጣችሁት ርዕሰ ጉዳይ ቢጋር በማዘጋጀት ከግማሽ ገፅ ያልበለጠ ጽሁፍ ፃፉ፡፡

ሀ. የሰላም አስፈላጊነት ሐ. መልካም ስነ-ምግባር

ለ. ጠንካራ የስራ ባህል መ. ውጤታማነት

፪፡-ከላይ በተግባር አንድ የጻፋችሁትን አንቀጽ በክፍል ውስጥ ተራ በተራ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

፫፡-ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀፅ አንብባችሁ ሀይለቃሉን ለይታችሁ አውጡ፡፡

ትምህርት የችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው፡፡ ሰዎች የማያውቁትን የዚህን አለም ሚስጥር መረዳት እና መጠቀም የሚችሉበት በትምህርት ሀይል ነው፡፡የራስን ኑሮ ማሻሻል፣ህብረተሰቡን መምራት የሚቻለው በትምህርት ነው፡፡ ትምህርት የሰዎችን የአስተሳሰብ አድማስ የሚያሻሽልና የኑሮ ዘይቤውን ቀለል አድርጎ ለመኖር የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡ ትምህርት አዳዲስ አሰራርና ለውጥን ለማስፈን ሰላምና ፍትህን ለማምጣት የተሻለች አለምን ለመፍጠር አይነተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

# ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

## የወል ስሞች

**መልመጃ፡-13**

**፩፡- በሚከተሉትዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የወል ስሞች በምሳሌው መሰረት ለይታችሁ አውጡ፡፡**

ምሳሌ፡-

1. አትክልቶችን አዘውትሮ መመገብ ለጤና ጠቃሚ ነው፡፡ መልስ፡-አትክልቶችን
2. በኢትዮጵያ በርካታ ወራጅ ወንዞች አሉ፡፡ መልስ፡- ወንዞች

1) መሀመድ ከክፍሉ ተማሪዎች በቁመት ትልቁ ነው፡፡
2) እድር የሚመሰረተው በአንድ አካባቢ በሚኖሩ ሰዎች ነው፡፡
3) በመኪና መንገድ ላይ የሚገዙ እንስሳቶች በሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ መጠንቀቅ ይገባል፡፡
4) ትዕግስት የተለያዩ ቅርሶችን መጎብኘት ትወዳለች፡፡
5) በርሃማነትን ለመከላከል እፅዋትን መንከባከብ ተገቢ ነው፡፡
6) ተማሪዎቹ ለፈተና ዝግጁ ሆነዋል፡፡

፪፡-አምስት የወል ስሞችን በመጥቀስ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በእያንዳንዳቸው አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ምሳሌ፡- ቤት=ከሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ ቤት አንዱ ነው፡፡

ሰራዊት=ኢትዮጵያ በመልካም ስነ-ምግባር የታነፀ ሰራዊት ገንብታለች፡፡

፫፡-በምዕራፍ አንድ በተማራችሁት መሰረት ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የስም አይነቶች የወል ስሞችን ብቻ ለይታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

ሀ. ዓሳ
ለ. ልጅ
ሐ. ሰው
መ. ሀዋሳ
ሠ. ናሆም
ረ. ቅርስ
ሰ. ወንበር
ሸ አሊማ

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የቃላትን ተመሳሳይ ፍቺ ለማየት ሞክረናል።ተመሳሳይ ፍቺ ማለት ለአንድ ቃል አቻ ፍቺ መስጠት መሆኑን አይተናል። በመቀጠልም ዋና ቃልን ከቅጥያ እንደት መለየት እንደሚቻል ተመልክተናል። ዋና ቃል ማለት ብቻው ትርጉም የሚሰጥ እና ወደ አነስተኛ ትርጉም አዘል አሀድ መሸንሸን የማይችል ሲሆን ቅጥያ ማለት ደግሞ እራሱን ችሎ የማይቆም ነገር ግን ከዋና ቃል ጋር ሲጣመር ትርጉም የሚሰጥ እንደሆነ ተምረናል። ስለሆነም ዋና ቃልንና ቅጥያዎችን በማጣመር ቃላትን መስርተናል።

የአንቀጽ ክፍል ለይተን ርዕስ በመምረጥ አንቀጽ ለመጻፍ ሙከራ ያደረግን ሲሆን አንቀፅ አንድ ነጠላ ሀሳብ ብቻ የሚያስተላለፍ አነስተኛ የፅሑፍ ክፍል መሆኑን አይተናል። በመጨረሻም የወል ስሞችን ከሌሎች ስሞች ለይተን ለማሳየት ሞክረናል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የዋና ቃልና ቅጥያዎች ልዩነት እና አንድነት በቃል አብራሩ፡፡
2. ለሚከተሉት ቃልት መዝገበቃላዊ ፍቺ ስጡ

   ሀ. ኪነ- ጥበብ  ሐ. ፈርጥ

   ለ. ሚስጥር  መ. አንጋፋ
3. ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት ዋና ቃሉንና ቅጥያውን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

   ሀ. ቂመኛ  መ. ተራራማ

   ለ. ኢትዮጵያዊነታችንን  ሠ. ተማሪዎቻቸውን

   ሐ. መንገደኛ  ረ. አንደበታዊነታቸውን

# ምዕራፍ ሶስት

## ቃላዊ ግጥም

❖ ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡ከዚህትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

✓ ለአዳዲስ ቃላት ፍች በመስጠት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡

✓ ግጥም ፅፋችሁ በትክክል ታነባላችሁ፡፡

✓ ቅንፍንና እዝባርን በአረፍተ ነገር ውስጥ ትጠቀማላችሁ፡፡

✓ አዳዲስ ያወቃችሁትን ቃላት በመጠቀም ገላጭ ተራኪና ቃላዊ ግጥም በመጻፍ በጭክታ ታነባላችሁ

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## በእርሻ ጊዜ የሚገጠም ቃላዊ ግጥም



ስዕል ፡- በእርሻ ላይ ያሉ በሬዎች፣ ወንድና ሴት ስራ ሲሰሩ የሚያሳይ

### ቅድመ ማዳመጥ

መልመጃ፡-14

ʘ፡-መምህራችሁ በእርሻ ወቅት የሚነገርአንድ ቃላዊ ግጥም ያቀርቡላችኋል፡፡ቃላዊ ግጥሙን ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ አብራሩ፡፡

1. ቃላዊ ግጥም ማለት ምን ማለት ነው?
2. ከቀረበው ስዕል ምን ተረዳችሁ፡፡
3. የምታውቁትን ቃላዊ ግጥም አስታውሳችሁ በቃላችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

### የማዳመጥ ሂደት

፪፡-በእርሻ ስራ ላይ የሚቀርብ ቃላዊ ግጥም መምህራችሁ ሲያቀርቡላችሁ እናንተ በትክክል እያዳመጣችሁ አዳዲስ ቃላትን ማስታወሻ ያዙና ተወያዩባቸው፡፡

### አዳምጦ መረዳት

፫፡-የሚከተሉትን ያልተሟሉ ቃላዊ ግጥሞች መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ በጥሞና በማዳመጥ የጎደለውን ሀረግ በማሟላት በቃላችሁ አቅርቡ፡፡

ሀ. ሐምሌ ነሐሴ ያልተራበ ሰው ፣

ሞፈር ቀንበሩን______፡፡

ለ. ሚያዚያ ግው ሲል ግንቦት ሲያገሳ

____________ ጎድጓዳ ማሳ፡፡

ሐ. ሆይላል ገበሬ ፣

ሆ ይላል ገበሬ ፣

________________________፡፡

መ. በሬና ገበሬ ______________፡፡

እንዲያ ሰተት ብሎ ይጠመዳል እንጂ፡፡

**፬:-ካዳመጣችሁት ቃላዊ ግጥም የወጡ አዳዲስ ቃላትን በምሳሌው መሠረት ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው።**

**ምሳሌ:- ክምር**

**የእነ አቶ በላቸው የጤፍ ክምር በጣም ትልቅ ነው።**

**ሀ. ጆርጃራ** **መ. እርኩም**

**ለ. ቀንበር** **ሠ. ዲብ**

**ሐ. እረኛ** **ረ. ቀሚስ**

**፭:-ተማሪዎች መምህራችሁ ያቀረቡላችሁን የቃላዊ ግጥም አነባበብ ስልት ተከትላችሁ:-**

1. በመማሪያ መጽሀፋችሁ ውስጥ የቀረበውን ቃላዊ ግጥም አንብቡ።
2. ያነበባችሁትን ቃላዊ ግጥም ጭብጥ (ዋና መልእክት) እና መቼ እንደሚባል ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ።

**በሰብል ጥበቃ ጊዜ የሚዜም**

**ኧረ ተይ ዝንጀሮ ግፍ አትናገሪ፣**

**አሁን ትገኛለሽ ውድማ ስትጭሪ።**

**ኧረ ተይ ዝንጀሮ ልቤን ቀረጥሽው፣**

**ለፍቼ ለፍቼ ሰብሌን ጨረሽው።**

**ዝንጀሮ ታረቀች ምላ ተማምላ፣**

**ማሽላውን ትታ ገብሱን ልትበላ።**

ዝንጀሮ መንጀሮ፣

በበላሽ ቀበሮ፡፡

ዝንጀሮ ከመጣ ሰብሉን ለመብላት፣

በወንጭፍ ገባሁት ተመለስ በሉት፡፡

ተይ ተመለሽ ዝንጀሮ ተንኮል ያጠፋሻል፣

ነፍስሽን በጤና ብትይዥ ይሻልሻል፡፡

፮፡-ያዳመጣችሁትን ቃላዊ ግጥም ጭብጥ በቡድን በቡድን ተወያይታችሁ በተወካዮቻችሁ አማካኝነት በክፍል ውስጥ የቃል ንግግር አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሁለት፡- ማንበብ

### ቃላዊ ግጥም

#### ቅድመ ንባብ

መልመጃ፡-15

፩፡-ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩና ተገቢውን ማብራሪያ በቃላችሁ አቅርቡ፡፡

1. በአብዛኛው ከሚዘወተሩት የፍቅር ቃላዊ ግጥሞች መካከል የምታስታውሱትን በቃል አቅርቡ፡፡
2. በተለያዩ ክብረ በዓላት የሚዘወተሩ ባህላዊ ግጥሞች የሚኖራቸውን ማህበራዊ ፋይዳ በተመለከተ አብራሩ፡፡
3. የሙሾ እና የሰርግ ቃላዊ ግጥም ልዩነታቸው ምን ይመስላችኋል?

## የንባብ ሂደት

**፪፦ጥንድ ጥንድ በመሆን አንዳችሁ ስታነቡ ሌሎቻችሁ እያዳመጣችሁ የሀረግ አከፋፈልን፣ ዜማንና ድምፀትን መጠበቃችሁን እያረጋገጣችሁ አንብቡ፡፡**

ቃላዊ ግጥም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ወግና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያ ልዩ ልዩ ክስተቶች እና የህይዎት መልኮችመግለጫ ኪነ-ጥበብ ነው፡፡ ይህ ኪነ ጥበብ ማህበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያካበቱትና የሚያካብቱት ቅርስ ነው፡፡ቃላዊ ግጥም ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሮ ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅም ማንፀባረቂያ ነው፡፡ በተለይ ፊደል ቀርፀው በፅሁፍ በማይገለገሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ማንነት፣እምነት፣የኑሮ ዘይቤንና ፍልስፍናን እንዲሁም አጠቃላይ የአለም አመለካከትን ቀርፆ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

ቃላዊ ግጥም ህዝቦች ማንነታቸውን ይገልፁበታል፤ ወግና ልማዳቸውን አጠናክረው ያቆዩበታል ፤ሀዘን ደስታቸውን፣ምኞት ተስፋቸውን፣ ፍቅር ጥላቻቸውን፣ድል ሽንፈታቸውን፣ በአጠቃላይ የህይዎታቸውን መልኮች ያንፀባርቁበታል፡፡ቃላዊ ግጥም የማህበረሰቡ አንጡራ ሀብት ነው የሚባለውየልጆች ጨዋታ፣የሀዘን እንጉርጉሮ፣ልመና፣ፉከራና ቀረርቶ፣የክብረ በዓላት፣ የስራ፣ የፍቅር ግጥሞች አመንጭው እከሌ ነው ስለማይባል ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ አጠር ባለና ቁጥብ በሆነ መልክ ይቀርባል፡፡

1. ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት አንቀፆች ምን ተረዳችሁ?
2. የቃላዊ ግጥም አይነቶች ምን ምንይሆናሉ ብላችሁ ትገምታላችሁ?



## 1.ቀረርቶና ፉከራ

ቀረርቶ ወይም ፉከራ ወኔን ለመቀስቀስ የሚያገለግል ሲሆን ከዋኙም ህዝብ በተሰበሰበበት እየተንጎራደደ በወኔ ያቀርበዋል፡፡ ቀረርቶና ፉከራ በሚቀርብበት ጊዜ ሀይለኛ ስሜትና አካላዊ እንቅስቃሴን የሚጠይቅ በአቀንቃኝና በተቀባይ ይቀርባል፡፡

የሚከተሉትን የቀረርቶና የፉከራ ግጥሞች እንመልከት፡፡


**ፉከራ**

**ዘራፍ! ዘራፍ! ዘራፍ!**
**ልከህ ስደደኝ ቆላ ለቆላ**
**ክላሹን ላምጣው ጥሬ ሲቆላ**
**ዱብ ዱብ ባይ እንደበረዶ**
**በልጅነቱ በረሃ ለምዶ**
**መራዥ ተኳሹን እኛ ስናውቀው**
**ዝናር በቅፌን ምን አስጨነቀው**
**ፈሪ ጨነቀው ተርበደበደ**
**ጥይት ዘነበ እሳት ወረደ**
**እትትት….ዘራፍ!...አካኪ ዘራፍ!**

**ቀርረቶ**

**ሲያመኝ ውሎ ሲያመኝ ሊያድር ነወይ፣**
**ይኸ ሰርቶ መብላት ጤና ላይሆን ነወይ፡፡**
**የጠፋ መስኳችሁ እንዳትገቡበት፣**
**ተረከዝ የሚያወልቅ ረመጥ አለበት፡፡**
**አረጀ አሉ አረጀ አሉ፣**
**ተከዜ አረጀ አሉ ሸበት ቀላቀለ፣**
**አንድ ሰው ብቻውን ይሻገር ጀመረ፡፡**

## 2. በውቂያና አጨዳ የሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞች



በሰብል ስራ ላይ የሚገጠሙ ቃላዊ ግጥሞች ድካምን ለማስወገድ፣ወኔን ለመቀስቀስ፣ጀግናን ለማወደስ፣ሰነፍን ለመኮነን ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ ገበሬው ሲያርስ ፣ሲጎለጉል፣ ሲወቃ፣ሲያጭድ ወዘተ. የተለያዩ ቃላዊ ግጥሞችን ይጠቀማል፡፡

| የውቂያ ግጥም፡- | የአጨዳ ግጥም |
| --- | --- |
| በርዬ እሽሩሩ | ይችን ማጭዴን ሆዷን አሚታል፣ |
| በርዬ እሽሩሩ፣ | እየቆረጠ ያጋድማታል፡፡ |
| የበሬን ውለታ፣ | ማጭዴ ቁረጭ፣ |
| እንጫወት ማታ፣ | እንዳትበለጭ፡፡ |
| በሰፊ ገበታ፣ | |
| በዋንጫ ጋጋታ፡፡ | |
| በርዬ እኔና አንተ የወረድንበቱ፣ | |
| ከካራ ይብሳል የድንጋይ ስለቱ፡፡ | |
| አያ በሬ ሆይ አያ ጎኔ ሆይ፣ | |
| ሳሩንእየህና ገደሉን ሳታይ፡፡ | |

## 3. የሙሾ ቃላዊ ግጥሞች

ሙሾ ሰዎች የምድርን አለም በሚሰናበቱበት ጊዜ ዘመድ ወዳጅ በተሰበሰበበት ጊዜ ለሟቹቹ ያለንን ሁኔታደረት እየተመታ፣ እየተዘለለ የሚከወን ነው፡፡ ዋና አላማው የሀዘንን ስሜት እየፈጠሩ ስሜትን መቀስቀስ ሲሆን የሟቾችን ገድልና ታሪክ በታሪክነት ያስተላልፋል፡፡

እንጀራውን ጋግረሽ ከማን ጋር በላሽው፣
ደረት የሚመታ ጎረቤት ያጣሽው፡፡
የእናትና የልጅ መመሰጋገኛው፣
ገረገራግቢ ሲፈታ መጫኛው፡፡

በአጠቃላይ ቃላዊ ግጥም በአንድ ማህበረሰብ ላይ የደረሱ አስከፊ ሁኔታዎች፣ ማለትም የተፈጥሮ አደጋዎች፣ስደት፣ ራብ፣ ወረሽኝ፣ ጦርነትን ወይም መልካም አጋጣሚን በተለያየ መልኩ እያቀረበ ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል የስነ-ቃል ዘርፍ ነው።

ምንጭ፡- ዘሪሁን አስፋው የስነፅሑፍ መሰረታውያን 2004 ከገፅ 20-63

## አንብቦ መረዳት

፫፡-በምንባቡ መሰርት የሚከተሉትን ዓ.ነገሮች ትክክል ከሆኑ ‹‹ እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ ሐሰት›› በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ በጽሁፍ መልሱ።

ሀ. ቃላዊ ግጥሞች የአንድ ማህበረሰብ ወግና ባህል መገለጫ ናቸው።

ለ. የቃላዊ ግጥም ባለቤት ግለሰብ እንጅ ማህበረሰቡ ሊሆን አይችልም።

ሐ. ቃላዊ ግጥሞች በገጠሩ ማህበረሰብ ብቻ የሚነገሩ ናቸው።

መ. የስራ ቃላዊ ግጥሞች የተለዋጭነት ባህሪ አይታይባቸውም።

ሠ. ቃላዊ ግጥሞች የሚቀርቡት በትረካ ብቻ ነው ።

ረ. ቃላዊ ግጥም ከጽሁፋዊ ግጥም የሚያመሳስለው የጋራ ባህሪ አለው።

፬፡-ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት የተለያዩ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. አይኔን ግንባር ያርገው ብላችሁ አትማሉ፣
   ይቸግራል እና መሪ ማባበሉ። ይህ ቃላዊ ግጥም የ_________ ነው።
   ሀ. የሙሾግጥም ለ. የልመና ግጥም
   ሐ. የፉከራ ግጥም መ. የዘፈን ግጥም

2. እንጀራውን ጋግረሽ ከማን ጋር በላሽው፣
   ጠላውንስ ጠምቀሽ ከማን ጋር ጠጣሽው፣

ደረት የሚመታ ጎረቤት ያጣሽው፡፡ ይህ ቃላዊ ግጥም ለምን አይነት ሴት የተገጠመ ይመስላችኋል፡፡

ሀ. ደግ በመሆኗ ለቅሶዋ ለደመቀላት ሴት፡፡

ለ. ክፉ በመሆኗ ለቅሶዋ እንደ ነገሩ ለሆነላት ሴት፡፡

ሐ. ዘመድ አልባ ሆና አልቃሽ ላጣች ሴት፡፡

መ. ግጥሙ የሴትዮዋን ምንነት አይገልጽም፡፡

3. በበጋ እረስ ቢሉት ፀሐይን እየፈራ፣
   በሀምሌ እረስ ቢሉት ዝናብ እየፈራ፣
   ልጁ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ፡፡

የሚለው ቃላዊ ግጥም ለምን አይነት ሰው የሚገጠም ይመስላችኋል፡፡

ሀ. ለታታሪ ገበሬ

ሐ. ለብልጥ ገበሬ

ለ. ለሰነፍ ገበሬ

መ. ለሞኝ ገበሬ

4. ሚኒልክ ተወልዶ ባያነሳ ጋሻ፣
   ------------------------------፡፡ ለሁለተኛው ስንኝ የሚስማማው ሀሳብ የቱ ነው፡፡

   ሀ. ምን ይበጀው ነበር ይህን ጊዜ አበሻ

   ለ. ቀኝ ተገዝቶ ነበር ይህን ጊዜ አበሻ

   ሐ. ግብሩ እንቁላል ነበር ይህን ጊዜ አበሻ

   መ. የት ይገባ ነበር ይህንጊዜ አበሻ

5. ከደጅሽ ይቅበሩኝ በስንደዶ ምሰው፣
እንዳይቆረቁረኝ አንችን አንተርሰው፡፡ ይህ ቃላዊ ግጥም የሚያስተላልፈው መልእክት __________ ነው፡፡

ሀ. የሀዘን ሐ. የፍቅር

ለ. የምኞት መ. የብሶት

6. ከወደዱም አይቀር ይወዳሉ ቀይ፣
እንደ አደይ አበባ------------------፡፡ ግጥሙን ሊያሟላው የሚችለው ሀረግ የትኛው ነው፡፡

ሀ. የቀይ የቀይማ ሐ. ከሩቅ የሚታይ

ለ. አጭር የሚታይ መ. የጓደኛ ቀይ

7. ከዋኙ ሲያቀርብ ተደራሲው ‹‹ አሼ . . . ከዚያስ . . . ደግሞስ ›› በሚል የሚቀርብ የስነ ቃል አይነት የትኛው ነው ?

ሀ. እንቆቅልሽ ሐ. ተረት

ለ. የልምና ግጥም መ. የፍቅር ግጥም

ፏ፡-ቀጥሎ በገላጭና በተራኪ የቀረቡትን ሁለት አንቀፆች ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ በየተራ አንብቡ፡፡

ሀ. በጣት እየጠነቆሉ የማንበብ ሂደት በአብዛኛው የሚታየው በእድሜ ዝቅ በሚሉ ህፃናት ላይ ነው፡፡ሂደቱ በቶሎ ካልተገታ አብሮ ሊያድግ ይችላል፡፡ በጣት እየጠነቆሉ ማንበበብ በንባብ ሂደት ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ይህ አይነቱ ልምድ የንባብ ፍጥነትን በጣም ከመቀነሱም በተጨማሪ አድካሚ ነው፡፡ በጣት እየጠነቆሉ ማንበብ ለጀማሪ አንባቢዎች ጠቃሚ መሆኑ ባይካድም ውሎ አድሮ የንባብ ችሎታ ሲዳብር ካልተወገደ ግን ችግር ይፈጥል፡፡ ይህንን ልማድ ለማስቀረትም አንባቢዎች ከጣታቸው ይልቅ አይናቸው በተሻለ መንገድ ይህንን ተግባር ሊወጣ እንደሚችል

በተግባር በማለማመድ ቀስ በቀስ ችግሩ እንዲቀረፍ ማድረግ ይቻላል፡፡(አለም እሸቱ፣16፣1996፣ያልታተመ ፅሁፍ)

ለ. መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም አርበኞች ሁሉ በድል አድራጊነት ሲገቡ በላይ ዘለቀም ወደ አዲስ አበባ ተጠርተው የደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጣቸው፡፡ ዳሩ ግን በዙሪያቸው የተሰገሰጉት ባንዳዎች ‹‹አላሰራም›› ስላሏቸው ሸፍተው ጫካ ገቡ፡፡ በመሰሪ ጥላቶቻቸው አቀነባባሪነት በላይ እጃቸውን ቢሰጡ ምህረት እንደሚደረግላቸው ተደርጎ ስለቀረበ በላይ በተግባራቸው ተፀፅተው እጅቸውን ሰጡ፡፡ ሆኖም ግን ምህረት ሳይሆን ሞት ስለተፈረደባቸው በተወለዱ በ33ዓመታቸው ተሰቀሉ፡፡(ታሪኩ ፋንታዬ ፣አማርኛ ሁሉ ለሁሉ ከመለስተኛ እስከ ኮሌጅ ገጽ 168፡፡)

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### አዳዲስ ቃላት

መልመጃ፡-16

፩፡-በ‹‹ሀ›› ረድፍ ለቀረቡትቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍቻቸውን ከ‹‹ለ›› ረድፍ በመምረጥ በትክክል አዛምዱ፡፡

| «ሀ» | «ለ» |
|---|---|
| 1.ቅርብ | ሀ. ከባድ |
| 2.መቀላቀል | ለ. ቀነሰ |
| 3.በሽተኛ | ሐ. ጥቂት |
| 4.ጨመረ | መ.አፀዳ |
| 5.ቀላል | ሠ. ሩቅ |
| 6.ብዙ | ረ. በርካታ |
| 7.በከለ | ሰ. መለያየት |
| 8.ጥቂት | ሸ. ጤነኛ |

፪:-ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተቃራኒ ትርጉም ያላቸውን ፊደል ብቻ ምረጡ።

1. ላመ ሀ. ደቀቀ ለ. ተሰረቀ ሐ. ተሸረከተ መ. በተነ
2. ህቡዕ ሀ. ድብቅ ለ. ገሀድ ሐ. ስውር መ. የማይታይ
3. ሁከት ሀ. ረባሽ ለ. አምባጓሮ ሐ.ሰላም መ. ቂም
4. ጥቂት ሀ. ትንሽ ለ. ቅንጣት ሐ. ሰፊ መ. አያሌ
5. ቆንቋና ሀ. ስስታም ለ. ለጋስ ሐ. ንፉግ መ. ገብጋባ

## ክፍል አራት፡- ጽህፈት

ማስታወሻ፡-ቅንፍ ( ) እና እዝባር / ስርአተ ነጥቦች

ሀ. ቅንፍ( ) ፡- ቅንፍ ወይም የሚለውን ቃል ተክቶ በጽሁፍ ውስጥ ያገለግላል።

ምሳሌ፡- እንደ እሱ ያለ እንብርቱን የተተኮሰ (ሚስጥር የማይቋጥር ) አይቼ አላውቅም።

ለ. እዝባር / ፡- አፅሮተ ቃላትን ለመመስረት እንደ አንድ ነጥብ (ይዘት) እና ቀንና ዓመተ ምህረትንለመለየት ያገለግላል።

ምሳሌ፡- 20/11/2013ዓ/ም፣ዶ/ር ወዘተ.

መልመጃ፡-17

፩:-የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት በእዝባር አሳጥራችሁ ፃፉ።

ሀ. ጽሕፈት ቤት

ለ. ወይዘሮ

ሐ. ትምህርት ቤት

መ. የኢትዮጵያ ሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ጽፈት ቤት

ሠ ፍርድ ቤት

፪:- በሚከተሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ቅንፍን በተገቢው ቦታ በማስገባት አሳዩ፡፡

ሀ. በችግር ውስጥ ያሉ ሰዎችን ለመታደግ ለመርዳት ሁላችንም ኀላፊነት አለብን፡፡

ለ. በአሁኑ ወቅት ኮረና ኮቪድ19 በዓለም ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ነው፡፡

ሐ. ልጁ ወደዚህ ምድር ከመጣ ከተወለደ ጀምሮ ቤተሰቦቹ ችግር አጋጥሟቸው አያውቅም፡፡

መ.የአባይ የህዳሴ ግድብ የህልውናችን ጉዳይ ነው ፡፡

፫:-ተማሪዎች ከቀረበላችሁ ርእስ አንዱን መርጣችሁ ግጥም በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

ሀ. ህዳሴ ግድብ ለ. እርቅ ሐ. ኮቪድ19

መ. ድህነት ሠ. መጤ ባህል

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

የጊዜ ተውሳከ ግስ

**ማስታወሻ**

የጊዜ ተውሳከ ግስ አንድ ነገር መቼ እንደተከሰተ ወይም እንደሚከሰት ይገልጻል፡፡ በዚህም መቼ የሚለውን ጥያቄ ይመልሳል፡፡

ምሳሌ፡- ዛሬ ፣ በኋላ ፣ አሁን


**መልመጃ፡-18**

**፩፡-በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን የጊዜ ተውሳከ ግሶች ለይታችሁ ጻፉ፡፡**

1. አለሚቱ ባለፈው አመት ከአምስተኛ ክፍል አንደኛ ወጥታለች፡፡
2. ሀሚድ ትምህርት ቤት በጧት ይደርሳል፡፡
3. ወይዘሮ በለጡ ትናንት ህፃናትን ስለመልካም ስነ-ምግባር አስተማሩ፡፡
4. መገርሳ ዛሬ ጧት በቀጠሮው መሰረት ከቦታው ደረሰ፡፡
5. መቅደስና ሪሃና በሚቀጥለው ዓመት ወደ ሀዋሳ ለመሄድ ተስማሙ፡፡
6. ነብዩ ባለፈው ሳምንት ቤተሰቦቹን ጠይቆ ታመለሰ፡፡
7. ወታደር ዘወትር የሀገሩን ሰላም ለማስከበር ዘብ የቆመ ነው፡፡

**2፡- ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላትና ሀረጋት የጊዜ ተውሳከ ግስ የሆኑትን ለይታችሁ በቻርቱ ውስጥ ጻፉ፡፡**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወዲያውኑ | በመኪና አደጋ | አሁን | ወደ አዲስ አበባ |
| አሳዛኝ | ስለረበሹ | ጥሩ | ትምህርት ቤት |
| ዛሬ | ነገ | አስደሳች | ያለፈው ዓመት |



፫፡-የሚከተሉትን ተውሳከ ግሶችን በተገቢው ቦታ እያስገባችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡

ሀ. ሁል ጊዜ ሐ. ገና ሠ.ክፉኛ

ለ. አንዳንድ ጊዜ መ. ቶሎ

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ቃላዊ ግጥም ጽፈን ያነባበብ ስልትን ጠብቀን በማንበብ ያነበብነውን ግጥም ጭብጥ ተናግረናል፡፡ ቃላዊ ግጥም በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ፣አሁንም ያለ ወደፊትም የሚቀጥል የማህበረሰቡን አጠቃላይ ወግና ባህል የሚገልፅ እነደሆነ ተመልክተናል፡፡

ቅንፍ ወይም የሚለውን ቃል ተክቶ የሚገባ ሲሆን እዝባር ደግሞ ቃላትን አሳጥሮ ለመፃፍ የሚያገለግል የስርዓተ ነጥብ አይይነት እንደሆነ አይተናል፡፡ ስለሆነም ስርዓተ ነጥብን በዓረፍተ ነገር ውስጥ በተገቢው ቦታ ተጠቅመናል፡፡ አዳዲስ ቃላትን ተጠቅመን ዓረፍተ ነገር መስርተናል፤ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ሰጥተናል፡፡ በመጨረሻምየጊዜ ተውሳከ ግስ አንድ ነገር መቼ እንደተከሰተ ወይም እንደሚከሰት የሚገልፅ እንደሆነ አይተናል፡፡ ተውሳከ ግሶች ለይተን በዓረፍተ ነገር ውስጥ ተጠቅመናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድ ቃላዊ ግጥም ከመፅሄት፣ ከጋዜጣና ከመፅሃፍት ፈልጋችሁ በመፃፍ በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡
2. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡
   ሀ. እንከን ሐ. ቁንጠኛ
   ለ. በረረ መ. ዛበረ
3. ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡
   ሀ. ሞከከ ሐ.ጥቂት
   ለ. ወላንሳ መ. ብልጥ
4. ሶስት የጊዜ ተውሳከ ግስ ጽፋችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ዘመናዊ እርሻ

ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች:ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች:-

- ✓ አዳምጣችሁ በቃል ትመልሳላችሁ።
- ✓ አከራካሪ አንቀፅ ትጽፋላችሁ።
- ✓ ቃላትን በመገጣጠም ትርጉም ትሰጣላችሁ።
- ✓ የጊዜ ግስን ተጠቅማችሁ ዓረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ።

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## ድሮና ዘንድሮ






### ቅድመ ማዳመጥ

**መልመጃ፡-19**

**፩፡-ከላይ የቀረበውን ስዕል በመመልከት ቀጣዮቹን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ‹‹ ድሮና ዘንድሮ ›› የሚለው ርዕስ ስለምን የሚናገር ይመስላችኋል? እስቲ ተወያዩና ግምታችሁን ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡
2. በአካባቢያችሁ ከትንሽ ነገር ተነስቶ ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ታውቃላችሁ? ካለ ምን እንደሰሩና ምን ደረጃ ላይ እንደደረሱ ግለጹ፡፡

### የማዳመጥ ሂደት

**፪፡-‹‹ድሮና ዘንድሮ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ያነቡላችኋል፤ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦችን እየለያችሁ አዳምጡ፡፡**

## አዳምጦ መረዳት

**፫:- ምንባቡን እያዳመጣችሁ ባዶ ቦታውንአሟልታችሁ ጻፉ።**

1) እኔና እናቴ ከችግራችን የምንወጣበት __________ ብሩህ ሆኖ ታየኝ።
2) ችግር መፍትሄ ይወልዳል እንዲሉ ____________ከመስሪያ ቤት ስልክ ተደወለልኝ።
3) የወተት ምርቱም ከጊዜ ወደጊዜ መጠኑ _________ መጣ።
4) በአካባቢያችን ላሉ አትክልትና ፍራፍሬ መደብሮች ምርቶችን _______ ጀመርን።
5) በአነስተኛ ቦታና ጉልበት ብዙ ምርት ማስገኘት የሚያስችል ዘርፍ ነው።
6) እንደ ___________ተደስቼና ቦርቂ ሳይሆን በስቃይና በፈተና መግፋት ጀመርኩ።
7) ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እናቴን የማገዝ ሀላፊነቱ በኔ ________ ወደቀ።
8) ከእልት ፍጆታ የሚተርፈንን _______ ጀመርን።

**፬:- ቀጥሎ በቀረቡት ቃላትና ሀረጋት መብንባቡ መሰረት ዓረፍተ ነገር ስሩና ለመምህራችሁ አሳዩ።**

ሀ. መቸርቸር ሐ .መግፋት ሠ. የኑሮ ዘይቤ

ለ. ተሰናብቶን ሄደ መ. ግብዓት ረ. የእለት ፍጆታ

ተግባር-2፡- ከዝቅተኛ የገቢ መጠን ወደ ከፍተኛ ገቢ መጠን እንዴት ማደግ እንደሚቻል በቡድን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ሀሳብ በየተራ ንግግር አድርጉ፡፡

# ክፍል ሁለት፡- ማንበብ

## የከተማ ግብርና

### ቅድመ ንባብ

መልመጃ፡-20

ሀ፡-ቀጥለው የቀረቡትን ጥያቄዎች በቀደመ እውቀታችሁ መሰረት መልሷቸው፡፡

1. የከተማ ግብርና ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል ?
2. በእናንተ አካባቢ የሚከናወን የከተማ ግብርና አለ? ካለ ምን ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡
3. በከተማ የሚከናወን ግብርና ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?

### የንባብ ሂደት


ምንባቡን ድምፅ ሳታሰሙ እያነበባችሁ አዳዲስ ቃላትን በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

ከከተማ ግብርና የሚገኝ ምርት የምግብ ስርዓትን በማሳደግ ጤናማ ማህበረሰ ለመገንባት ዘርፈ ብዙ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ለዚህ እንደማሳያ ማህበረሰቡ በአነስተኛ ቦታ ዘመናዊ የግብርና ዘዴዎችን በመጠቀም ለጤና ጠቃሚ የሆኑ የግብርና ምርቶችን በማምረት ለዕለት ፍጆታ ማዋል ሲጀምር የምግብ ደህንነቱን ከመጠበቁም በተጨማሪ በምርቱ ላይ የሚኖረው እምነት ይጨምራል፡፡ይህም በቀላሉ በጥቂት ቦታ፣ብዙ የሰው ሃይል ሳያስፈልግ የከተማው ነዋሪ የአርሶ አደሩን እጅ ሳይጠብቅ የምግብ ዋስትናውን እንዲያረጋግጥ ያስችላል፡፡ይህም የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኝ በማድረግ ጤናማ ማህበረሰብ መፍጥር ያስችላል፡፡

ከነባሩ የዶሮ ዝርያዎች የተሻለ የምርት ልዩነት የሚሰጡ የዶሮ ዝርያዎችን ከአንድ የወተት ላም በቀን ሊገኝ የሚችልውን የወተት መጠን ማሳደግ የሚችሉ የላም ዝርያዎች እንዲሁም የተለያዩ የሰብል፣የአትክልትና ፍራፍሬ ቴክኖሎጅዎችን ወደ ተጠቃሚ ተሸጋግረው ማህበረሰቡ ውጤታማ ምርት ማምረት የሚያስችለውን አሰራር በመዘርጋት የምግብ ደህንነትን ለማስጠበቅ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም የማህበረሰቡ አካል የሆኑት በርካታ ሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚ የሚሆኑባቸው የሥራ እድሎችን ይፈጥራል፡፡ በከተማ አካባቢ የሚለሙ በርካታ የግብርና ዓይነቶች ቢኖሩም በእያንዳንዱ ግቢ ውስጥ በቀላሉ ሊመረቱ የሚችሉ የአትክልት ዓይነቶችማለትም ቲማቲም፣ ካሮት፣ ጥቅል ጎመን፣የሀበሻ ጎመን፣ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡


1. ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት ጽሁፍ ውስጥ ምን ተረዳችሁ?
2. ቀሪዉ የንባብ ክፍል ስለምን የሚገልጽ ይምስላችኋል?

**ቲማቲም፡-**



በሀገራችን በስፋት ከሚመረቱት የአትክልት ሰብሎች ውስጥ አንዱ ቲማቲም ነው፡፡ ቲማቲም የተመጣጠነ የምግብ ይዘት ያለው በተለይም ማዕድናትንና ቫታሚኖችን ከማስገኘቱም ባሻገር የአምራቹን ህብረተሰብ የነፍስ ወከፍ ገቢ በማሳደግ የስራ እድል ለመፍጠርና በተወሰነ ቦታ ላይ ብዙ ገቢ በማስገኘት ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያለው አትክልት ነው፡፡ ምርቱንም የቲማቲምድልህ፣ ጭማቂ፣ካችአፕ፣ቋንጣና የቲማቲም ዘቢብ በማዘጋጀት ለቤት ውስጥ ፍጆታ መጠቀም ይቻላል፡፡

**ጥቅል ጎመን፡-**



ጥቅል ጎመን በቀዝቃዛ አካባቢዎች የሚመረት የጓሮ አትክልት ሲሆን ከጥንት ጀምሮ ለሰው ልጅ በምግብነት ከታወቁት አትክልቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ጥቅል ጎመንበአነስተኛ ማሳ ላይ የሚመረት የተለያየ ቀለም ፣የራስ ቅርፅ፣ ለምግብነት የመድረሻ ጊዜ ያላቸው ዝርያዎች እንዳሉት ይታወቃል፡፡ በብዛት የሚታወቀው ግን አረንጓዴ ቀለምና ጠፍጣፋ ራስ ያለው ነው፡፡በቫይታሚን ኤ እና ሲ ምንጭነቱ የታወቀ ሲሆን ለምግብነትም በተለያየ መልኩ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

## የሀበሻ ጎመን



የሀበሻ ጎመን ከስኳር ድንችና ከድንች ቀጥሎ በኢትዮጵያ በአነስተኛ ቦታ የሚመረትና በስፋት የሚታወቅየጓሮ አትክልት ነው፡፡ ተቀቅሎ፣ተጠብሶና በክትፎ መልክ ተዘጋጅቶ ከአይብ ጋር ተቀላቅሎ ለምግብነት ይውላል፡፡ የሀበሻ ጎመን ከፍተኛ የቫይታሚን ሲ እና የሚኒራል መጠን በውስጡ ይዟል፡፡

## ሰላጣ



ሰላጣ ቅጠሉ በጥሬነት ከቲማቲም፣ ከቃሪያ ና ከቀይ ሽንኩርት ጋር ተቀላቅሎ በዳቦና በእንጀራ ተደርጎ ለምግብነት ይቀርባል፡፡ ከፍተኛ መጠን ያለው የቫይታሚን ኤ፣ሲ፣ ኬ እና ሚኒራል በውስጡ ይዟል፡፡

## ካሮት



ካሮት የቫይታሚን ኤ መጠኑ ከሌሎች አትክልቶች ይልቅ ከፍተኛ በመሆኑ

ካሮትንመመገብ የዐይንዳፍንት በሽታን ለመከላከል ይረዳል፡፡

በተጨማሪም የቫይታሚን ቢ መጠኑ ከፍተኛ ነው፡፡

በአጠቃላይ በከተማ ግብርና ህብረተሰቡን በማሳተፍ የጓሮ አትክልቶችን በአነስተኛ መሬት በመዝራት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ የጓሮ አትክልቶች የተለያየ የአካል ክፍሎቻቸው ለሰው ልጅምግብነት ሚውሉ ሲሆን እንደ አትክልቶች አይነት ቅጠሎቻቸው፣ሥሮቻቸው ፣ አበባዎቻቸውና ፍሬያቸው ሊበላ ይችላል፡፡ የጓሮ አትክልቶች የተለያየ አይነትና መጠን የምግብ ይዘት ያላቸው ሀይል ሰጭ፣ ሰውነት ገንቢእና በሽታ ተከላካይ ምግቦችናቸው፡፡ የጓሮ አትክልቶችን ለማምረት የዕለት ከዕለት ክትትል፣የአመራረት እውቀትና ክህሎትን የሚጠይቅ ስራ ነው፡፡ ሆኖም በተወሰነ ቦታ ላይ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ በመሆናቸው ጠቀሜታቸውየጎላ ነው፡፡

**ምንጭ፡-** በሴቭ ዘ ችልድረን፣በትምህርት ሚኒስተርና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ት/ቢሮ የጋራ ትብብር በ2008ዓ.ም ከተዘጋጀው አጋዥ መጽሐፍ ለ6ኛ ክፍል ማስተማሪያ ተስማምቶ የቀረበ

## አንብቦ መረዳት

**፩፡-**በሚከተሉት ቃላት በምንባቡ ውስጥና ከምንባቡ ውጪ ያላቸውን ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮችን ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- በርካታ፡-በምንባቡ መሰረት፡- ብዙ

ከምንባቡ ውጪ፡- በደስታ

ሀ. የጓሮ አትክልት ለጤና በርካታ ጠቀሜታ አለው፡፡

ለ. ባፊው ሳምንት የተመረቀችው ተማሪ የወርቅ ሜዳሊያዋን በርካታ ተቀበለች፡፡

ሀ. ክህሎት ሐ. ጥሬ ሠ. መቀላቀል

ለ. ማሳ መ. ዝርያዎች ረ. ፍጆታ

**፫:-ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል እየመረጣችሁ በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. ከሚከተሉት አንዱ ስራቸው ከሚበሉ አትክልቶች ይመደባል፡፡
   ሀ. የሀበሻ ጎመን ለ. ድንች
   ሐ. ጥቅል ጎመን መ. ቃሪያ
2. ሳይበስል የሚበላ አትክልት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሰላጣ ለ. ቆስጣ
   ሐ. ድንች መ. የሀበሻ ጎመን
3. ከሚከተሉት አንዱ ቅጠሉ ከሚበላ አትክልት ውስጥ ይመደባል፡፡
   ሀ. ካሮት ለ. ቃሪያ
   ሐ. ቆስጣ መ. ስኳር ድንች
4. ከነባሩ የዶሮ ዝርያየተሻለ ምርት የሚሰጥ ነው፡፡የተሰመረበት ቃል ፍቺ ------- ነው፡፡
   ሀ. ከቆየው ለ. ከአዲሱ
   ሐ. ከተለወጠው ሐ. ከተሸሻለው
5. የህብረተሰቡ አካል ለሆኑት የስራ እድል ይፈጥራል፡፡የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ሰውነት ለ. ክፍል
   ሐ. ዘመድ መ. ጓደኛ
6. በቀዝቃዛ ቦታ የሚመረት የጓሮ አትክልት የቱ ነው?
   ሀ. ቲማቲም ለ. ቃሪያ
   ሐ. ጥቅል ጎመን መ. ሰላጣ

7. የዐይን ዳፍንት በሽታ የሚከላከል አትክልት የሆነው?

ሀ. ካሮት ለ. ድንች

ሐ. ሰላጣ መ. ቲማቲም

8. ‹‹የነፍስ ወከፍ›› የሚለው ሀረግ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?

ሀ. ለጽድቅ ለ. ለቡድን

ሐ. ለእያንዳንዱ መ. ነፍስን የሚጎዳ

9. ከሚከተሉት አንዱ የአትክልት ዝርያ አይደለም፡፡

ሀ. ጥቅል ጎመን ለ. ሙዝ

ሐ. የሀበሻ ጎመን መ. ቃሪያ

10. የከተማግብርና ጠቀሜታ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ንጹህ ምግብ ማግኘት

ለ. የምግብ ፍላጎትን ማሟላት

ሐ. በቀላሉ የተመጣጠነ ምግብ ማምረት መቻል

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

ተግባር-3፡- በግቢያችሁ ወይም በአካባቢያችሁ የጓሮ አትክልቶችን አመራረትና ጠቀሜታ የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ በክፍል ውስጥ የቃል ዘገባ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ቃላትን በመገጣጠም ትርጉም መስጠት

መልመጃ፡-21

፩፡-የሚከተሉትን ትርጉም የማይሰጡ ቃላት በምሳሌው መሰርት ትርጉም በሚሰጥ መንገድ አዋቅራችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- ስፈረ=ፈረስ

በሰውሰባቸ=ሰበሰባቸው

ቤምትህትትር=ትምህርት ቤት

ሀ. ውትቀፅ መ. መልይለሳ ሰ. ክሳትይታ ተ. በንወር

ለ. ጥዶወየሮ ሠ. ቀልመለጠ ሽ. ተናፊ ቸ. ርባፀትገያህ

ሐ. ርንብሃ ረ. ዝማአል ቀ.ሀፅመፍ በ. ሲንየደያራተ

፪፡-ከዚህ በታች ባለው አንቀፅ ውስጥ ያሉትን አዳዲስ ቃላት አውጥታችሁ ትርጉማቸውን በቃላችሁ ተናገሩ፡፡

ወንጀል ሰላማዊ ኑሮን ይነቀንቃል፤ወንጀለኞች ኪስ ያወልቃሉ፤ቤት ይሰረስራሉ፤ በሚዛን ያብላሉ፤ አልፎ ተርፎ ጨለማን ተገን በማድረግ የሰውን ህይወት ይቆርጣሉ፡፡ እነዚህ አሜካላዊ እስካልተመነጠሩ ድረስ ሰላማዊ ኑሮ መጎሹ አይቀሬ ነው፡፡

(ሰለሞን ሐለፎም የድርሰት አፃፃፍ 1997፣193)

፫፡-ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ይሆናሉ ተብለው ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል ይበልጥ የሚስማማቸውን ምረጡ፡፡

1. ሰፈፍ ሀ.ዝቃጭ ለ. አተላ ሐ. ጥላይ መ. ለዛ
2. ቃና ሀ.ለዛ ለ. መዓዛ ሐ. ውበት መ. ዳና
3. የቀለም ቀንድ ሀ.ምሁር ለ. ብዕር ሐ. ዋንጫ መ. ቀንድ
4. ፅሞና ሀ.ትህትና ለ. ምር ሐ. ቀልድ መ. ተመስጦ
5. ራሮት ሀ.ርህራሄ ለ. ጥቁረት ሐ. ሮሮ መ. ስጋት
6. ማመንጨት ሀ.ማፍለቅ ለ. መቅዳት ሐ. መጥለፍ መ.መቀስቀስ
7. ደራ ሀ.ኮራ ለ. ሰፋ ሐ. ሞቀ መ. ተኮሰ

# ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

## አመዛዛኝ ፅሁፍ

መልመጃ፡-22

፩፡-የሚከተሉትን ተዘበራርቀው የቀረቡ ዓረፍተ ነገሮች አስተካክላችሁ አንድ አንቀጽ አዋቅራችሁ ጻፉ፡፡

ሀ.መንገደኞቹም ሩጫቸውን ትተው በቅርብ ወዳገኙት መጠለያ ተጠጉ፡፡

ለ. በጥፊ የሚመታው ይህ ስለታም ነፋስ አቧራ አስነስቶ እሰው አይን ውስጥ እየሞጀረ ያደናብራል፡፡

ሐ. የአዲስ አበባ ሰማይ በጥቁር የደመና ብርድ ልብስ ተጀቡኗል፡፡

መ. የሴቶችን ቀሚስ ወደላይ እየገለበ ይተናኮላል፡፡

ሠ. ብዙ ሳይቆይ ጠብ ያለህ በዳቦ የሚለው ዶፍ ዝናብ እየተንዠቀዠቀ ቁልቁል ወረደ፡፡

ረ. ጉርምርምታው ያላማራቸው መንገደኞች አህያ የማይችለውን ዝናብ ለማምለጥ ወደየቤታቸው በመሯሯጥ ላይ ናቸው፡፡

ሰ. ሀይለኛ ነፋስ ከዝናቡ ቀድሞ መንገደኞችን ማወክ ጀመረ፡፡

ሸ. ከባድ ዝናብ ያረገዘው ደመና አጣዳፊ ምጥ ይዞት በጣር ያጉረመርማል፡፡

፪፡-ከዚህ በታች የቀረቡትን አከራካሪ አንቀፆች መሰረት አድርጋችሁ ከሀ-መ ከተዘረዘሩት አከራካሪ ዓረፍተ ነገሮች አንዱን በመምረጥ አንድ አከራካሪ ጽሑፍ በደብተራችሁ ጻፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

ሀ. ንፅፅራዊ ስነ-ልሳን ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቋንቋዎችን በተነፃፅሮት የሚያጠና የስነ-ልሳን ዘርፍ ነው፡፡ ለተነፃፅሮት የሚቀርቡትም ቋንቋዎች ስርወ ግንዳቸው አንድ ወይም የተለያየ ሊሆን ይችላል፡፡ዘርፉ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቋንቋዎችን በድምፅ፣ በቃላት አገባብ እንዲሁም በአረፍተ ነገር አሰካክ ያላቸውን ዝምድና እና ልዩነት በማነፃፀር የሚያቀርብ ነው፡፡

(ተስፋየ ሸዋየ፣1981፣13)

ለ. … በምግብ በኩል የሚታየው የአካል ግንባታና ጥገና በመጠጥ በኩል ተቃራኒ ሆኖ ይታያል፡፡ መጠጥ በብዛትና በተከታታይ በተወሰደ ጊዜ እንደጉበት ፣ኩላሊት፣ ልብና የመሳሰሉትን የውስጥ አካላትን ለጉዳት ያጋልጣል፡፡ በእርግጥ ምግብም ቢሆን በልክና በተመጣጠነ ደረጃ ካልተወሰደ ሰውነትን ቅርፀቢስ ከማስመሰል አሳልፎ የተከማቸ ትርፍ ስብ በነርቮችና በደም ዝውውር ላይ ችግር ሊያመጣ ይችላል፡፡ ስናጠቃልለው ለሚበላ ነገር ቅድሚያ ሰጥተው የሚዋከቡትን ሰዎች ባህላችን አይደግፏቸውም፡፡ ስለሆነም ህብረተሰቡ ‹‹ሆዳም፣ስግብግብ፣አሳማ…›› እያለ ያጥላላቸዋል፡፡ መጠጥ ወዳጁንም ‹‹ፉቴ፣ ገልባጭ፣ አንቡላ፣ ሰካራም…›› በሚል የቅፅል ስም ይጠሯቸዋል፡፡ ያም ሆነ ይህ ምግብና መጠጥ ፈፅሞ ሊወዳደሩ አይችሉም፡፡ ( ታሪኩ ፈንታዬ፣2008፣173)

ሀ. ከቀደመውና ከአሁኑ ትውልድ ጠንካራ የሀገር ፍቅር ስሜት ያለው

የትኛው ነው?

ለ. በሰው ሀገር ሰርቶ ከመበልፅግና በሀገር ሰርቶ ከመበልፀግ የትኛው ይሻላል?

ሐ. ከእውቀትና ከገንዘብ የትኛው ይበልጣል?

መ. ጀግና ማነው? በጦርነት ተዋግቶ ያሸነፈ ወይስ ድህነትን ተዋግቶ ያሸነፈ?

ተግባር-3፡- ተማሪዎች አንድ ርዕስ መራጣችሁ አከራካሪ ጽሁፍ በማጋጀት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

## የጊዜ ግስ

➢ መልመጃ፡-23

፩፡-በሚከተሉትን ጥያቄዎች ውስጥ ያሉትን የጊዜ አይነቶች ለይታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- አክስቴ ወደሀገሯ ልትመለስ ነው፡፡ የወደፊት ጊዜ

አክስቴ ወደሀገሯ እየተመለሰች ነው፡፡ የአሁን ጊዜ

አክስቴ ወደሀገሯ ተመልሳለች፡፡ የሃላፊ ጊዜ

ሀ. ለጆሮ እንዲስማማ ተደርጎ የተዘጋጁ ዜማዎችን ለገበያ አቅርበዋል፡፡

ለ. ቃሎቿ የተዋቡ ይሁኑ እንጅ ስታወጣቸው በጭንቀት ነበር፡፡

ሐ. በአለማችን በአሁኑ ስዓት በረሃማነት እየተስፋፋ ነው፡፡

መ. አዲስ አበባ ወደፊት ምቹና ፅዱ እየሆነች ትሄዳለች፡፡

ሠ.እህቴ ነገ ከጎንድር ትመጣለች፡፡

ረ. ታናሽ ወንድሜየተወለደው ከዛሬ አስር አመት በፊት ነበር፡፡

ሰ. የውጭ ሀገር ጎብኚዎች ወደ ሀገራችን እየመጡ ነው፡፡

ሽ. የመንገድ ባለስልጣን የመንገድ ላይ ምልክቶችን ለመትከል እያሰበ ነው፡፡

**፪:-የሚከተሉትን ሰዋስዋዊ ስህተት የሚታይባቸው ዓረፍ ነገሮች አስተካክላችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. ሁኔታ አለፈ ፈተናውን በጥሩ፡፡

ፈተናውን በጥሩ ሁኔታ አለፈ፡፡

ለ. አስተማረች ልጇን ሙያ አስቴር፡፡

አስቴር ልጇን ሙያ አስተማረች፡፡

ሀ. ተወካያቸውን የክፍል መረጡ ተማሪዎቹ፡፡

ለ. ያስፈልጋል ተማሪዎችን ማበረታታት ጎበዝ፡፡

ሐ.መነሳት ሰው ማንኛውም አለበት ታጥቆ ለማስወገድድህነትን ፡፡

መ. ሄለን የተመሰገነች በስነ-ምግባሯ ናት፡፡

ሠ. ጉልበት አለበት ሁሉም ሰው የህፃናት መከላከል ብዝበዛን፡፡

ረ. ቴክኖሎጅ አለበት ትምህርት መደገፍ በሳይንስና፡፡

ሰ. ለማቅረብ አለበት አጥፊዎችን መተባበር ህብረተሰቡ ለህግ፡፡

ሸ. ባህላችን አረጋውያንን ይገባል ሊሆን መንከባበከብ፡፡

**፫:-የሚከተሉትን የጊዜ ተውሳከግሶች በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡**

ሀ. አምና

ለ. ባለፈው ሳምንት

ሐ. ከወር በኋላ

መ. የዛሬ አመት

ሠ. ሌሊት

ረ. ቶሎቶሎ

ሰ. አልፎ አልፎ

ሸ. በዚህ አመት

፬፡-ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት የአሁን ጊዜ፣የሀላፊ ጊዜና የወደፊት ጊዜ በማለት በሰንጠረዥ ውስጥ መድቡ፡፡

እየተማረ ነው     እየሰራ ነው     እየሰጠ ነው     ሰጥቷል

ይሰጣል     ይመጣል     ሰላም እየሰፈነ ነው     ሰብሯል

ያነባል     ሰላም ይሰፍናል     እየመጣ ነው     ይሰብራል     አንብቧል

ሰላም ሰፍኖ ነበር     መጥቷል     ተምሯል     ያነባል     እያነበበ ነው

| ተ/ቁ | የአሁን ጊዜ | የሀላፊ ጊዜ | የትንቢት ጊዜ |
|---|---|---|---|
| 1 | | | |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስር አከራካሪ አንቀጽ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ የሚመሳሰሉበት ወይም የሚለያዩበት ሀሳብ በማነጻጸር ወይም በማወዳደር የሚያቀርብ ጽሁፍእንደሆነ ተረድተናል፡፡ በዚሁ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የተፃፈ ፅሑፍ በማቅረብ በምሳሌው መሰርት አንቀፅ መፃፍ ችለናል፡፡

የተዘበራረቁ ፊደላትን አገጣጥመን ፍቺ ያላቸው ቃላትን መስርተናል፡፡ ከዓረፍተ ነገር ውስጥ የጊዜ አይነቶችን ለይተን ጽፈናል፡፡ የጊዜ አይነቶች ሶስት ሲሆኑ እነሱም የአሁን ጊዜ፣ የሃላፊ ጊዜና የትንቢት(የወደፊት ጊዘየ) እንደሆኑ አይተናል፡፡የጊዜ ተውሳከ ግሶችን በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የጊዜ አይነቶች የሚባሉት ምን ምን ናቸው?
2. አከራካሪ ጽሁፍ ምን አይነት ጽሁፍ እንደሆነ በቃል ግለጹ፡፡
3. በከተማ ግብርና ዙሪያ የቀረቡ መርሀ ግብሮችን ከቴሌቪዥን፣ከሬዲዮ ተከታትላችሁ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፤

# ምዕራፍ አምስት

## ቱሪዝም

❖ ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ ቃላትን በምእላድ ትከፋፍላላችሁ፡፡
- ✓ ለቃላት እማሪያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ በሀላፊ ጊዜ አንቀጽ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ቅድመ ግንድ ቅጥያዎችን ትለያላችሁ፡፡
- ✓ ራስን የመገምገሚያ ስልቶችን ተጠቅማችሁ ሥራችሁን ትመዝናላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## አካባቢያዊ የቱሪስት መስህቦች





ስዕል አባያና ጫሞ ሀይቆች

**ቅድመ ማዳመጥ፡-፩**

**መልመጃ፡- 24**

**ሀ.‹‹ አባያና ጫሞ ሀይቆች ›› በሚለው ርእስ የቀረበው ምንባብ ምን ምን ነገሮችን የሚያሳይ ይመስላችኋል?**
**ለ.ከዚህ በፊት የጎበኛችሁት ወይም ሽርሽር የሄዳችሁበት ቦታ ካለ ምን ምን ነገሮችን እንደተመለከታችሁ ዘርዝሩ፡፡**
**ሐ.የመጎብኘት እድል ቢሰጣችሁ የትኛውን ቦታ የምትመርጡ ይመስላችኋል?**

**የማዳመጥ ሂደት፡-፪**

‹‹አባያና ጫሞ ሀይቆች›› በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነብላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በመለየት በንቃት አዳምጡ፡፡

**አዳምጦ መረዳት**

**፫፡- በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ‹‹ እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ ሀሰት› በማለት መልሱ፡፡**

ሀ. ልዩ ልዩ መስህባዊ ስፍራዎች የአንድን ሀገር ታሪክና ባህል ባጭሩይገልጻሉ፡፡

ለ. የአባያ ሀይቅ ከወላይታ ሶዶ በስተምእራብ ይገኛል፡፡

ሐ. ‹‹ በአባያና ጫሞ ሀይቆች መካከል የሚገኝ የእግዜር ድልድይ ሰዉ ሰራሽ ነዉ፡፡

መ. አባያና ጫሞ ሀይቆች ለአርባ ምንጭ ልዩ ዉበት ናቸዉ፡፡

ሠ. አባያና ጫሞ ሀይቆችን የሚጎበኝ ሰው መንፈሱ ስለሚታደስ ለፈጠራ ስራ ይነቃቃል፡፡

ረ. ፡፡በሁለቱ ሀይቆች ዉስጥ የተለያዩ የባህር እንስሳት መኖራቸዉ ለአካባቢዉም ሆነ ለሀገሪቱ የሚሰጡት ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ የጎላ ነዉ፡፡

ሰ. የቱሪዝም ቦታዎችን መጠበቅ ያለብን ከሚሰጡት ጥቅም አኳያ ብቻ ነው፡፡

የቃላት ጥናት

፬፡- የሚከተሉትን ቃላትበምሳሌው መሰረት በምዕላድ ነጣጥላችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡- መስህቦቻችን፡- መስህብ - ኦች - ኣችን

ሀ. ሎጆችም ሐ. የሚመሳሰሉባቸዉ ሠ. መዳረሻነታቸዉን

ለ. ተመሳስሎዎች መ. መልክአ ምድራዊ ረ. መስህቦቻቸዉ

## ተግባር-አራት

ተማሪዎች ስለ አንድ የጉብኝት ቦታ ከሬዲዮ፣ከቴሌቪዥን አዳምጣችሁ ወይም ከጋዜጣ፣ከመጽሔት አንብባችሁ ወይም ከአዋቂ ሰዉ ያገኛችሁትን መረጃ በክፍል ውስጥ ንግግር አቅርቡ፡፡

# ክፍል ሁለት፡-ማንበብ

## አንድነት ፓርክ

### ቅድመ ንባብ

## መልመጃ፡- 25

፩፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በስዕሉ ላይ ተወያዩና የሚገልጸውን መልእክት በቃል ተናገሩ፡፡

ለ.‹‹ የአንድነት ፓርክ ›› የት የሚገኝ ይመስላችኋል?

ሐ. የአንድነት ፓርክ በውስጡ ምን ምን ነገሮችን ያካትታል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

## የንባብ ሂደት

ቀጣዩን ምንባብ ስታነቡ በእያንዳንዱ አንቀፅ መጨረሻ ቆም እያላችሁ የአንቀፁን መልዕክት በአዕምሮአችሁ እያጠቃለላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ በየግላችሁ አንብቡ፡፡

የአንድነት ፓርክ የሚገኝበት ታላቁ ቤተመንግስት የተቆረቆረው በ1878ዓ.ም ሲሆን የመሰረቱትም በወቅቱ የሸዋ ንጉስ የነበሩት ዳግማዊ አጤ ምኒልክና ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ ብጡል ነበሩ፡፡ የቤተ መንግስቱ አጠቃላይ ስፋት አርባ ሄክታር ነው፡፡ ቦታው ለቤተ መንግስትነት የተመረጠው ለፍልውሃ በነበረው ቅርበትና በወቅቱ ዙሪያውን ለመቆጣጠር የሚመች ከፍታ ቦታ በመሆኑ ነው፡፡ ፡፡

የአንድነት ፓርክ በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ ሀሳብ አመንጭነት ለፓርክነት የግንባታና የማደራጀት ስራው በ2010ዓ.ምተጀመረ፡፡ አዳዲስ የጉብኝት መስህብ የሆኑ ግንባታዎች የተካሄዱበት ስፍራ በሙሉ ቀደም ሲል ጥሻና ገደላማ ነበር፡፡ ታሪካዊ ህንጻዎችና አደባባዮች ታሪካቸውና ፋይዳቸው በምሁራን ተጠንቶ ለጉብኝት ምቹ ሆነው የተደራጁ ዘመናዊ የቱሪስት መዳረሻዎች ናቸው፡፡

የአንድነት ፓርክ የጉብኝት መዳረሻዎች

አንድነት ፓርክ በውስጡ ስድስት ዋና ዋና የቱሪዝም መስህቦች አሉት ከመግቢያው ጀምሮ የምናገኛቸው እነዚህ የአንድነት ፓርክ ክፍሎች የጥቁር አንበሳ ዋሻ፣ የአገር በቀል ዕፅዋት መገኛ ቦታ፣ የክልል እልፍኞች፣ የአረንጓዴ ስፍራ፣ የአንድነት መካነ እንስሳት፣ የቤተ መንግስቱ ታሪካዊ ህንፃዎችና አውደ ርዕዮቻቸው ይጠቀሳሉ፡፡ ከታሪካዊ ህንፃዎቹ በስተቀር አምስቱ የጉብኝት መዳረሻዎች በአዲስ መልክ የተገነቡ የቱሪስት ስፍራዎች ናቸው፡፡

1. ከላይ ካነበባችኋቸው አንቀጾች ምን ተረዳችሁ?
2. ቀጣዩ የምንባብ ክፍል ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?

ታላቁ ቤተ መንግስት የአጤ ምኒልክ ቤተ መንግስት ተብሎም ይታወቃል፡፡ ይህ ቤተ መንግስት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ አገራዊና አህጉራዊ ፋይዳ ያላቸው ሁነቶች የተፈፀመበት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከ1880ዎቹ ጀምሮ የተገነቡ የነገስታት መኖሪያና ጽህፈት ቤቶች በዋነኛነት በዚህ ውስጥ የሚካተቱ ሲሆን የነበሩበትን ይዞታቸዉን ሳይለቁ እድሳት ተደርጎላቸዋል፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱ የሆነው የአጤ ምኒልክ የግብር አዳራሽ ሲሆን ንጉሱ በዚህ አዳራሽ እንግዶቻቸውን ያስተናግዱ እንደነበር ታውቋል፡፡ በዚህ ስፍራ መጀመሪያ የምናገኘው የፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ዲናግዴን (አባ መላ) መኖሪያ ነው፡፡ ቀጥሎም የአጤምኒልክ ባለአንድ ፎቅ መኖሪያና ጽህፈት ቤት ያለ ሲሆን የህንፃው በሮች በእንጨት የተሰሩና በሚያምር መልኩ የአበባና የሀረግ ጌጥ የተፈለፈለበት ናቸው፡፡ ይህ ቤት ከሁለት ሌሎች ቦታዎች ጋር በድልድይ ይገናኛል፡፡ አንደኛው በሰሜናዊ አቅጣጫ የአጤምኒልክ የፀሎት ቤትና የሥዕል ቤት ሲሆን እንቁላል ቤት በመባል ይጠራል፡፡ በሌላ በኩል አጤምኒልክ ከጦር መኮንኖቻቸው ጋር የሚገኛኙበት ክፍል ይገኛል፡፡ በወቅቱ የጦር ሚኒስትር የነበሩት ፊትአውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ዲናግዴ እንደ ቢሮ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

ሌላው ደግሞ የዘውድ ቤት ሲሆን በአጤ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ነገስታትንና ዲፕሎማቶችን ከተለያዩ ሀገራት ተቀብለው ያስተናግዱበት ነበር፡፡

ከእነዚህም መካከል በ1956 የዩጎዝላቪያው ፕሬዝደንት ቲቶ፣በ1965 ንግስት ኤልሳቤጥ 2ኛ፣ በ1966 የፈረንሳዩ ፕሬዝደንት ቻርልስ ደጎል ይገኙበታል፡፡ ሌላኛው ከአጤ ምኒልክ ቤት ጋር በድልድይ የሚገናኘው የእቴጌ ጣይቱ ቤት ነው፡፡ ይህ ቤት ከቤተ መንግስቱ በምስራቃዊ አቅጣጫ የሚገኝ ባለአንድ ፎቅ ህንፃ ነው፡፡ በምድር ቤት የዙፋን ግብር ቤት ይገኛል፡፡ የነገስታቱ መመገቢያ አዳራሽ ሲሆን ንጉሳዊ ቤተሰቦች ምግብ የሚመገቡበት ክፍል ነበር፡፡ ይህ ቤት በደርግ ጊዜ የደርግ ምክር ቤት መሰብሰቢያ በመሆን አገልግሏል፡፡



## የሀገር በቀል እፅዋት

በሀገር በቀል የዕጽዋት ጉብኝት መዳረሻ፣ለመድሃኒት፣ ለምግብና ለውበት አገልግሎት የሚውሉ ዕጽዋትን ይጎበኛሉ፡፡ከነዚህም መካከል ጤናአዳም፣ኮሰረት፣ ፌጦ፣በሶብላ፣ዝግባ፣ዋንዛ ወዘተ. ይገኛሉ፡፡ በእጅ በተጠረቡ ድንገዮች የተሰሩ ካቦች፣ መተላለፊያ መንገዶችና የጭቃ ቤትም በዚሁ ስፍራ ይገኛል፡፡

## የጥቁር አንበሳ መካነ እንስሳት




በዚህ የጉብኝት መዳረሻ ጎብኝዎች 175 ሜትር እርዝመት ባለው ዋሻ ውስጥ ሆነውና በዙሪያው እየተዘዋወሩ በዋናነት የባሌና የዴዴሳ ዝርያ የሆነውን ባለ ጥቁር ጎፈር አንበሳ ይመለከታሉ፡፡

## የክልል እልፍኞች



በአንድነት ፓርክ ውስጥ ከሚገኙ የጉብኝት መዳረሻዎች መካከል አንዱ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ውስጥ ያሉ የክልል እልፍኞች የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ እልፍኞቹ የየክልሎቹን ተፈጥሯዊ፣ ባህላዊ እና ታሪካዊ መስህቦች

በጥቂቱ ለጎብኝዎቹ ያስተዋውቃሉ፡፡ እልፍኞቹ ስለክልሎቹ መሰረታዊ መረጃ በተንቀሳቃሽ ምስል፣በሥነ-ስዕል እና በሌሎች የባህል ውጤቶች በጥቂቱ የሚያቀርቡ ናቸው፡፡ አሠራራቸውም በዘመናዊ የኪነ-ህንፃ ጥበብ የተቃኘ እና በጎብኝዎቹ ላይ የብሩህ ተስፋ ስሜት እንዲፈጠር የታሰበ ነው፡፡

**የአረንጓዴ ስፍራ**



ይህ ቦታ ጎብኝዎች በእግር ጉዞ ወይም በጉዞ አጋዥ መሳሪያዎች የሚንሸራሸሩበት እና ከከፍታ ዙሪያ ገባውን የሚቃኙበት ነው፡፡ የአዲስ አበባ ከተማን ከፊል ገጽታ ቁልቁል ለመመልከት ምቹ የሆነ ነው፡፡ በአረንጓዴ ስፍራው ልዩ ልዩተፈጥሯዊ መስህቦች፣ሀገራዊ ሀብቶችና መገለጫዎች የሚያንፀባርቁ የጥበብ ስራዎች ተካተዋል፡፡

## የአንድነት መካነ እንስሳት




**በዚህ የእንስሳት ስፍራ ሰው ሰራሽ የባህር እንስሳት መኖሪያ ገንዳን (አኳርያም) ሳይጨምር ዝርያቸው ወደ 30 አይነት ብዛታቸው ደግሞ 220 ገደማ የሆነ በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳት የሚኖሩበት ስፍራ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል ቀጭኔ፣ አቦ ሸማኔ፣ ሚርካት፣ ኢምፓላ እና ልዩልዩ አዕዋፋት ይገኙበታል፡፡**

**በአጠቃላይ የአንድነት ፓርክ አሁን ባለው ቁመና የበርካታ ጎብኚዎችን ቀልብ የሚስብ ከመሆኑም በተጨማሪ ለሀገራችን ከፍተኛ የገቢ ምንጭ በመሆን የሚያገለግል ፓርክ ነው፡፡**

**ምንጭ አንድነት ፓርክን በተመለከተ ከተዘጋጁ ጽሁፎች ውስጥ ለማስተማሪያነት በሚያመች መልኩ የተወሰደ**

## አንብቦ መረዳት

**2፡- ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት የምርጫ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ በደብተራችሁ ጻፉ።**

1. ለቱሪዝም እድገት አስተዋፅዖ የሌለው የቱ ነው?

ሀ. ጎብኚዎች ባህላችንን እንዲያከብሩ ማድረግ

ለ. የራሳችንን ባህል መጠበቅ።

ሐ. ማህበረሰቡን ስለቱሪዝም ጥቅም ማስተማር

መ. ለቅርሶች ትኩረት መንፈግ

2. ‹‹ የግብር አዳራሽ ›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ግብር የሚከፈልበት ቦታ ለ. የነገስታት የምግብ አዳራሽ

ሐ.የስብሰባ አዳራሽ መ. ቤተ መንግስት

3. ‹‹ዙሪያ ገባውን›› የሚለው ሐረግ የሚያስተላልፈው መልዕክት

ሀ. የሚወጣ የሚገባውን ለ. የሚሽከረከረውን

ሐ. አካባቢውን መ. ዙሪያ መዞርን

4. የአንድነት ፓርክ በውስጡ ስንት የቱሪዝም ዋና ዋና መስህቦች አሉት?

ሀ. አራት ለ. አምስት

ሐ. ስምንት መ. ስድስት

5. የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ከምሰጡት አስተዋፅዖ አንዱ ያልሆነዉ።

ሀ. ለውጭ ምንዛሬ ማስገኛ ለ. ለጥናትና ምርምር

ሐ. ለእውቀትና ለመዝናናት መ. ድንበር ለማስከበር

6. ‹‹ አንድነት ፓርክ ›› የሚለው ርዕስ ምንን ያመለክታል?

ሀ. ነጠላ ቁጥርን ለ. በብዙነት ውስጥ ያለ አንድነትን

ሐ. መረዳዳትን መ. ተመሳሳይነትን

7. ኢትዮጵያ በዩኒስኮ ካስመዘገበቻቸው ቅርሶች መካከል የማይካተተው_____ ነው፡፡

ሀ. የሀረር ግንብ ለ. የአፄ ፋሲል ቤተመንግሰት

ሐ. የአንድነት ፓርክ መ. ኤርታሌ

፫፡- በምንባቡ መሰረት የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆኑ ደግሞ ‹‹ሀሰት›› በማለት በቃላችሁ መልሱ፡፡

ሀ. የክልል እልፍኞች የየክልሉን ባህል በተወሰነ መልኩ ይገልጻሉ፡፡

ለ. የአገር በቀል ዕጽዋት ተብለው የሚታወቁት ለምግብና ለመድሐኒትነት የሚሆኑ ናቸው፡፡

ሐ. የቤተመንግስቱ አጠቃላይ ስፋት አርባ ሄክትር መሬት ነው፡፡

መ. ታላቁ ቤተመንግስትን የመሰረቱት አፄ ኃ/ስላሴና እቴጌ መነን ናቸው፡፡

ሠ. ባለ ጥቁር ጎፈር አንበሳ ያለበት ዋሻ ርዝመት 175 ሜትር ነው፡፡

፬፡- ተማሪዎች ምንባቡን በትክክል በድጋሚ አንብቡና ዋናውን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በተራ በተራ በቃል አብራሩላቸው፡፡

# ክፍል ሶስት ቃላት

## እሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

ማስታወሻ

ቃላት እማሬያዊና ፍካሪያዊ ፍቺ ይዘው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ በዚህም የተነሳ አንድ ቃል በተለያየ መንገድ ሊተረጎም ይችላል፡፡

**ሀ. እማሬያዊ ፍቺ፡-**

የአንድ ቃል የመጀመሪያ ቀጥተኛ ፍቺ ወይም የመዝገበ ቃላዊ ፍቺ ነው፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. መሬት - ምድር

ለ. ዱባ- ተቀቅሎ የሚበላ ትልቅ ፍሬ

ሐ. ቤት - ከተለያዩ ግብዓቶች የተሰራ የሰው ልጅ መጠለያ

**ለ. ፍካሪያዊ ፍቺ**

አንድ ቃል ከመዝገበ ቃላዊ ፍች በተጨማሪ ሌላ ተደራቢ ፍቺ ሊኖረው ይችላል፡፡ አንድ ቃል በቀጥታ ከሚኖረው ፍቺ ባሻገር የሚሰጠው ሚስጥራዊ ፍቺ ፍካሬያዊ ፍቺ ይባላል፡፡ ፍካሬያዊ ፍች ብዙውን ጊዜ የሚመሰረትው በንፅፅር ላይ ነው፡፡ ንፅፅሩም ከአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ልማድ፣እምነትና አተያይ ጋር የሚቆራኝ ነው፡፡ምሳሌ፡-ሀ. ፍየል- ለፍላፊ

ለ. መሬት- ቻይ፣ ታጋሽ

ሐ.ዱባ- ወፍራም

መ. ቤት - ትዳር / የዘር ሀረግ

መልመጃ፡-26

፩፡- የሚከተሉትንቃላትና ሀረጋትበተሰጠው ምሳሌ መሰረት እምሬያዊ ፍቻቸውን በደብተራችሁ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ ፡- ዝግባ- በጣም ረጅም የሆነ የዛፍ አይነት

ድንጋይ- ለተለያየ ግንባታ የሚውል ግዑዝ ነገር

ሀ. ቁራ

ለ. ሙጫ

ሐ. ሚጥሚጣ

መ. ምስጥ

ሠ. ንብ

ረ. ብርቱካን

ሰ. ነፋስ

ሸ. እርጎ

2፡- የሚከተሉትን ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ፍካሬያዊ ፍች በመስጠት በደብተራችሁ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ምላጭ- መሰሪ

መሰላል- ረጅም

ሀ. ጥይት

ለ. እሳት

ሐ. ወንፊት

መ. ጽጌረዳ

ሠ. ፈረስ

ረ. ጉልቻ

፫፡- ተማሪዎች አምስት ቃላትን ፈልጋችሁ እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

## በሃላፊ ጊዜ አንቀፅ መፃፍ

**መልመጃ፡-27**

**፩፡- ከዚህ በታች በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ባለፈው ሳምንት ያከናወናችሁትን ድርጊትበሃላፊ ጊዜ የተመሰረተ አንቀፅ  በደብተራችሁ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡**

**ምሳሌ፡-**

**ጎጃም ዳሞት አውራጃ ውስጥ ማንኩሳ በምትባል አገር ቦጋለ መብራቱ የሚባሉ ብዙ ዘመን በብቸኝነት የሚኖሩ ሰው ነበሩ፡፡ቦጋለ መብራቱ ከድሀ ቤተሰብ የተወለዱ በዚያውም ላይ ድሆች ወላጆቻቸው ገና በህፃንነታቸው ሞተውባቸው ድህነት ሲያንገላታቸው ያደጉ ነበሩ፡፡ ትንሽ ከፍ እንዳሉ መጀመሪያ የፍየልና የጥጃ እረኝነት እየተቀጠሩ በኋላም እጃቸው እርፍ ለመጨበጥ ያክል መበርታት ሲጀምር ግብርና እየተቀጠሩ ይኖሩ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ እኩል እድሜያቸውን ካሳለፉና የሚስት ማግባት ፍላጎታቸው እየቀነሰ ከሄደ በኋላ በጎልማሳነታቸው ጉልበታም ወዲያው ጤናማ በመሆናቸው ረዳት ሳይፈልጉ ራሳቸውን ረድተው ለመኖር ቢችሉም ሚስት ካላገቡ እድሜያቸው እየገፋ አቅማቸው እየቀነሰ ሲሄዱ ረዳት የሚያጡ መሆናቸውን ወላጆቻቸው አጥብቀው ስለመከሯቸው ከዚያው ከማንኩሳ ውድነሽ በጣሙ የሚባሉትን ሴት አገቡ፡፡** (ሀዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብር 1996፣12)፡፡

**፪፡- ከላይ በመልመጃ አንድ ላይ በሃላፊ ጊዜ ተመስርታችሁ የፃፋችሁትን አንቀፅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ካነበባችሁ በኋላ ሌሎች ተማሪዎች ሲያነቡ ከራሳችሁ ስራ ጋር እያነጻጸራችሁ ጽሁፋችሁን ገምግሙ፡፡**

፫፡- ‹‹ሰላም ለሰው ልጆች አስፈላጊ ነው›› በሚለው ሀይለቃል አንድ አንቀፅ ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

# ክፍል አምሰት ሰዋስው

## ቅድመ ግንድና ድህረ ግንድ ቅጥያ

**መልመጃ፡- 28**

**፩፡- የሚከተሉትን ቃላትና ሐረጋት ምሳሌውን መሠረት በማድረግ በዋና ቃሉ ላይ ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን እያጣመራችሁ ጻፉ፡፡**

ምሳሌ፡- ወንበር - ኦች ,ወንበሮች

መጣ-ኣችሁ መጣችሁ

ጫማ - ዎች ጫማዎች

ሀ. ደብተር - ኣችሁ

ለ. ገበሬ - ዎች

ሐ. መከረ - ኣት

መ. ተከሰተ - ኧች

ሠ. መምህር - ኦች

ረ. ትምህርት - ኣችሁ

ሰ. መጽሐፍ - ኡ - ን

ሸ. ንብረት -ኣቸው - ን

፪፡- በሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት ውስጥ ያሉትን ቅድመ ግንድ ቅጥያዎችን በመነጠል በደብተራችሁ ጻፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ከቤት ከ - ቤት ፣. ስለሄደ ስለ - ሄደ

ሀ. እንደወረደ

ለ. ስለፍቅር

መ. የነጀማልሰ.

ሠ. ወደመስኮት

ሰ. ከአዲስ አበባ

ሸ. አስነሳ

ሐ. የመቅደስ ረ. በህብረተሰብ

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ቅድመ አምድ ቅጥያ ከዋና ቃል ቀድሞ የሚገባ እንደሆነና ድህረ አምድ ደግሞ ከዋና ቃል በኂላ የሚጨመር መሆኑን ተምረናል፡፡የቃላት እማሬያዊ ፍቺ ማለት የቃላት ቀጥተኛ ፍቺ ሲሆን ፍካሬያዊ ፍቺ ደግሞ ቃላት በቀጥጣ ከሚኖራቸው ፍቺ ባለፈ ያላቸውን ድብቅ ወይም ስውር ፍቺ እንደሆነ ማየት ችለናል፡፡ በመሆኑም ለቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ መስጠት ችለናል፡፡ የሃላፊ ጊዜ የሚባለው አንድ የተፈጸመ ድርጊት በጊዜ ቅደም ተከተል መተረክ መሆኑን ተገንዝበን የሃላፊ ጊዜ ጽሁፍ ጽፈናል፡፡ እንዲሁም ያነበብነውን ጽሁፍ ጭብጥ ( ዋና መልእክት ) ማብራራት ችለናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ምንነት በቃላችሁ አብራሩ፡፡
2. የቅድመና ድህረ አምድ ቅጥያዎችን ምንነት በምሳሌአስደግፋችሁ ጻፉ
3. የጊዜ አይነቶችን በመዘርዘር ለእያንዳንዳቸው ምሳሌ ስጡ
4. የሚከተሉትን ቃላት በነፃና ጥገኛ ምዕላድ በመለየት አስቀምጡ

   ሀ. ስኣቶቻችንሐ.ወንድሞቻቸው

   ለ. በቴሌቪዥናቸው መ. ምንባብአችሁን

# ምዕራፍ ስድስት

## አደንዛዥ ዕፆች

❖ ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- ✓ ካዳመጣችሁት ምንባብ የመረዳት ጥያቄዎችን ትመልሳላችሁ
- ✓ ተገቢውን የአነባበብ ስልት ተከትላችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ✓ መረጃ ሰጪ ፅሁፎችን ትለያላችሁ፡፡
- ✓ አዳዲስ ቃላትን ከአገባቡ በመነሳት ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ✓ አንድን ሀሳብ ለመግለጽ መሸጋገሪያ ቃላትን ትጠቀማላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

‹‹ሰካራሙ ተበጀ››



## ቅድመ ማዳመጥ

**መልመጃ፡- 29**

**፩፡-ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት ለሚከተሉት ቁልፍ ቃላት በቃል ፍቺ ስጡ**

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ገድል | ሐ. ድብርት | ሠ. አደንዛዥ ዕፅ |
| ለ. ሱስ | መ. ጠንቅ | ረ. መደንዘዝ |

## የማዳመጥ ሂደት

‹‹ሰካራሙ ተበጀ›› በሚል ርእስ በገላጭ መልክ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ የፅሁፉን መልዕክት ለመረዳት በትኩረት አዳምጡ

**አዳምጦ መረዳት**

**፪፡- ምንባብቡን ካዳመጣችሁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻቹሁ አቅርቡ፡፡**

ሀ. ሱስ ምንድን ነው?

ለ. ሰዎች ወደተለያዩ ሱሶች የሚገቡት ለምን ይመስላችኋል?

ሐ. ‹‹ ከጠርሙስ ጋር ካልተገናኝ አይኑ አይገለጥም›› ሲል ምን ማለቱ ነው?

መ. ‹‹ የሚያላክኩበት ›› የሚለው ሐረግ ምንን ይገልጻል?

ሠ. የምንባቡን ጭብጥ (መልእክት)ከግል ህይወታችሁ ጋር በማገናኘት ተወያዩ፡፡

**፫፡- የሚከተሉትን ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

ሀ. አድሮ ቃሪያ

መ. ማህበርተኛ

ለ. ከድጡ ወደ ማጡ

ሠ. ግብረ ገብ

ሰ. የተመሰቃቀለ

ሐ. ሰርጉጀዋለሁ

ረ. የደበዘዘ

ሸ. መሳለቂያ

**ተግባር-5፡- የአልኮል መጠጥ በቤተሰብ ላይ የሚያመጣውን አሉታዊ ተፅዕኖ በቡድን ተወያዩና በክፍ ውስጥ በንግግር አቅርቡ፡፡**

# ክፍል ሁለት፡- ማንበብ

‹‹ጫትና መዘዙ››

## ቅድመንባብ



I. መልመጃ፡-30

**ቅድመ ንባብ፡-፩**

ሀ. የጫት ሱስ ምን ጉዳት ያስከትላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?

ለ. በተለያየ ሱስ ምክንያት ያጋጠማችሁ ችግር ካለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ግለጹላቸው፡፡

ሐ. ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ ተገቢውን የአነባበብ ስልት ተከትላችሁ ድምፅ ሳታሰሙ አንብቡ፡፡

## የንባብ ሂደት

ከዚህ በታች የቀረበውን ምንባብ በምክንያትና በውጤት እያስተሳሰራችሁ ድምፅ ሳታሰሙ በግል አንብቡ፡፡

በሀገራችን በተለያዩ አደንዛዥ ዕፆች የሚጠቁ ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ካሉት በርካታ የአደንዛዥ እፅ አይነቶች ውስጥ ደግሞ ጫት አንዱ ነው፡፡ በየአካባቢው የጫት ምርቶች ከሌሎች የሰብል አይነቶች ባልተናነሰ መልኩ በመጠን እየበዛ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምርቱን ከአምራቾች ተቀብሎ ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጩ ነጋዴዎችበዚሁ ልክ ተስፋፍተዋል፡፡ በትምህርት ተቋማት አካባቢ ሳይቀር ትኩስ ጫት እናቀርባለን የሚሉ ማስታወቂያዎች ይስታዋላሉ፡፡ ይህም ለአደንዛዥ ዕፅ መስፋፋት የራሱ የሆነ አስተዋፆ አለው፡፡

ጫት መቃም በማህበራዊ ህይወት፣ በምጣኔ ሀብትና በጤና ላይ ከፍተኛ ኪሳራ ያስከትላል፡፡ ጫት መቃም የሚያዘወትሩ ግለሰቦች ለከፍተኛ የጤና መታወክ ይዳረጋሉ፡፡ የስራ ጊዜያቸውን ጫት በመቃም የሚያሳልፉና ገንዘባቸውን ለጫት መግዣና መሰል ፍጆታ ስለሚያውሉ ለችግር ይጋለጣሉ፡፡ ማህበራዊ ህይወታቸው የላላ ይሆናል፡፡ የጥሩ ስነ-ምግባር ባህሪ ባለቤት ቢሆኑም እንኳበማህበራዊ ህይወታቸው ተቀባይነት የላቸውም፡፡

በጫት መቃም የተጠመደ ሰው በጤናው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይፈጥርበታል፡፡ አደንዛዥ ዕፁ በአዕምሮ ላይ ለጊዘ የመነቃቃትና የደስታ ስሜት ቢያጎናፅፍም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደከፍተኛ ድብርት፣መረበሽ፣መጨነቅና አለመረጋጋትን ይፈጥራል፡፡ ሞልተው የነበሩ ተስፋዎች አንደጉም ተነው ይጠፋሉ፡፡ ቀስ በቀስም የሆድና የአንጀት ድርቀትን ያስከትላል፡፡የምግብ ፍላጎትን በመቀነስ በተህዋሲያን አማካይነት የሚተላለፉ በሽታዎችን የመከላከል አቅምን ያሳንሳል፡፡

1. ተማሪዎች ንባባችሁን ገታ በማድረግ ከላይ ከቀረቡት አንቀጾች ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ?
2. ከዚህ ቀጥሎ ያሉት አንቀጾች ስለምን የሚገልፁ ይመስላችኋል?

በጫት ሱስ መጠመድ ለራስ ብቻ ሳይሆን መዘዙ ለቤተሰብም ጭምር ነው፡፡ጫት ከሚቅሙ እናቶች የሚወለዱ ህፃናትበቂ ጡት ስለማያገኙ እድገታቸው ይቀጭጫል፡፡ በሌላ መልኩ በቤተሰቡ በሚፈጥረው አለመረጋጋት በልጆች ላይ ስነ-ልቦናዊ ጫና ይፈጥራል፡፡ ጫት በሚቃምበት ጊዜ ከሱስ ጋር ግንኙነት ያላቸው ነገሮች፤እንደ ስኳር፣ለውዝና ጣፋጭ መጠጦች በዋናነት አብረው ሲወሰዱ ይሰወተዋላል፡፡እነዚህ ነገሮች ከጫት ሱስ ጋርየሚወሰዱነገሮች ሲሆኑ ለተጨማሪ በሽታ መንስዔ ይሆናሉ፡፡ ጫት መቃም፣ ሲጋራ ማጨስ፣አሽሽ መውሰድና አልኮል መጠጣት ለድርብርብ በሽታና ጥንቃቄ ለጎደለው የግብረ ስጋ ግኝኙነት ይዳርጋል፡፡

ጫት መቃም የጤና ጠንቅ ከመሆኑ ባሻገር ምጣኔ ሀብትን ያናጋል፡፡የሚቅሙ ሰዎች በየጊዜው ለጫት መግዣ ብዙ ገንዘብ ያወጣሉ፡፡ የስራ ጊዚያቸውን በመቃም ስለሚያሳልፉገቢያቸው ይቀንሳል፡፡ በዚህ የተነሳ ቤተሰብን ለመምራት ይቸገራሉ፡፡ በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ማለትም በደስታ፣ በሀዘን፣በስራና በተለያዩ ሁኔታዎች ግንኙነቶችን ያደበዝዛል፡፡ የማህበራዊ ግንኙነት ክብርን ይቀንሳል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ አደንዛዥ እፅ የተለከፈ ሰው ለጤና፣ ለማህበራዊ ህይወት፣ለምጣኔ ሀብት እና ለመሳሰሉት ውስብስብ ችግሮችይጋለጣል፡፡የስራ ባህልን በመጉዳት ለጥገኝነት ይዳርዳል፡፡ስለሆነም ሁሉም ዜጋ አደንዛዥ እፆች ጎጂ መሆናቸውን አውቆ ግላዊ ነፃነቱን ለሱስ አሳልፎ ላለመስጠት መጠንቀቅ ይገባዋል፡፡

ምንጭ (ከቀድሞው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለክፍሉ በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

## አንብቦ መረዳት

**፩፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆነ‹‹እውነት›› ስህተት ከሆነ ደግሞ‹‹ሀሰት››**

በማለት በቃል መልሱ፡፡

ሀ. በሀገራችን በተለያዩ አደንዛዥ እፆች የሚጠቁ ሰዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቷል፡፡

ለ. ጫት መቃም በምጣኔ ሀብት እንጂ በጤና ላይ ጉዳት አያስከትልም፡፡

ሐ. በተለያዩ አደንዛዥ እፆች መጠመድ መዘዙ ከራስ አለፎ ለቤተሰብና ለሀገር ይተርፋል፡፡

መ. የአደንዛዥ እፆችን ዝውውር የመከላከሉ ሀላፊነት የሁሉም ዜጎች ነው

ሠ. አደንዛዥ እፆች ለድብርትና ለመረበሽ ይዳርጋሉ፡፡

ረ. ጫት አዕምሮን ስለሚያነቃቃ ጠቀሜታዉ ከፍተኛ ነው፡፡

ሰ. የጫት ሱስ ያለባቸው ሰዎች ጥሩ ስነ ምግባር ቢኖራቸውም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸውም፡፡

**፫፡-በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡-ሀ. በትምህርት ተቋማት አካባቢ ሳይቀር ትኩስ ጫት እናቀርባለን የሚሉ ሰዎች ቁጥር እየበዛ ነው ፡፡

ያልጠወለገ ( ተቆርጦ ያልቆየ )

ለ. የጫት ነጋዴዎች መበራከት ለአደንዛዥ እፅ መስፋፋት የራሱ የሆነ አስተዋፅዖ አለው፡፡

ተጽእኖ (አበርክቶ)

1. በጫት ሱስ መጠመድ በማህበራዊ ህይወትና በምጣኔ ሀብት ላይ<u>ኪሳራ</u> ያስከትላል፡፡

2. የስራ ጊዜያቸውን በሱስ የሚያሳልፉ ሰዎች ማህበራዊ ህይወታቸው <u>የላላ</u> ይሆናል፡፡

3. በጫት መቃም የተጠመዱ ሰዎች በጤናቸው ላይ <u>አሉታዊ</u> ተፅዕኖ ይፈጠርባቸዋል፡፡

4. በተለያዩ አደንዛዥ እፆች መጠመድ <u>መዘዙ</u> ለቤተሰብና ለሀገርም ጭምር ነው፡፡

5. በበቂ ሁኔታ ተጠብቀውያላደጉ ህፃናት እድገታቸው <u>ይቀጭጫል</u>፡፡

6.ለደባል ሱስ መጋለጥ <u>ለድርብርብ</u> በሽታና ለኤች አይ ቪ ያጋልጣል፡፡

**፬፡- በ ‹‹ሀ›› ምድብ ስር ለቀረቡት ቃላት ከ ‹‹ለ›› ረድፍ በፍች የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. መጠመድ | ሀ. መታመም |
| 2. መታወክ | ለ. ራስን አለመቻል |
| 3. ድብርት | ሐ. ምክንያት |
| 4. መንስኤ | መ. ድባቴ |
| 5. ጥገኝነት | ሠ.መያዝ |
| | ረ. እንቅልፍ ሰ. ቅስቀሳ |

# ክፍል ሶስት ቃላት

## የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ

**መልመጃ፡-31**

**፩፡- የሚከተሉትን ቃላት እማሬያዊ ፍቺ የሚያሳዩ አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ምሳሌ፡- ኮሮሪማ    አልማዝ በርበሬ ለማዘጋጀት ኮሮሪማ ገዛች፡፡

ምስጥ    ለአጥር የተተከለዉን እንጨት ምስጥ በልቶታል፡፡

ሀ. ሙቅ    ሐ.እሾህ    ሠ. ወንበር

ለ. ጨፌ    መ. ኩባያ    ረ. ወለላ

**፪፡-የሚከተሉትን ቃላት በተሰጠው ምሳሌ መሰረት ፍካሬያዊ ፍች የሚያሳዩ ዓረፍተ ነገሮች ስሩባቸው፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. ቆቅ    ዘመናይ ቆቅ ናት፡፡

ለ. እሳት    የሱፍ በትምህርቱ እሳት ነው፡፡

ሀ. ባህር    መ. እርግብ.    ሰ. ግስላ

ለ. ነቀዝ    ሠ. አንበሳ    ሸ ወርቅ

ሐ. አሳማ    ረ. ጎተራ    ቀ.ጥላሸት

**፫፡-በሚከተሉት ቃላት በምሳሌው መሰረት እማሪያዊና ፍካሬያዊ ፍች ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡- ጉቶ፡- እማሬያዊ ፍችው የእንጨት ተቆርጦ ከስር የሚቀረው አካል ሲሆን፣ፍካሬያዊ ፍችው አጭር

ሀ. እስስት መ. ቁልፍ ረ. ማር

ለ. ምሰሶ ሠ.ኩራዝ ሸ. ተልባ

ሐ. ቋንጣ

**፬፡- በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን አዳዲስ ቃላት በምሳሌው መሰረት አውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡- ሀ. የግል ንፅህናን አለመጠበቅ ለተስቦ በሽታ ያጋልጣል፡፡ ለተላላፊ በሽታ

ለ.ትናንት ሲያሽከረክር የነበረው ሹፌር መንገዱን ስቶ ማጥ ውስጥ ገባ፡፡ ረግረግ ቦታ(አረንቋ)

1. የቁጠባ ባህል ማሳደግ የህይወት መድህን ነው ፡፡

2. ከግብረገብነት ይልቅ ለንዋይ መሯሯጥ የስልጣኔ መገለጫ አይደለም፡፡፡

3. የከተማው ማህበረሰብ አካባቢውን ለማፅዳት በነቂስ ወጣ፡፡

4.ደራሲው የጀመረውን የስነ-ፅሁፍ ስራ ባለፈው ሳምንት ቋጨ፡፡

5. በሀገራችን የሚስተዋሉ ህፀፆችን የማስተካከሉ ድርሻ የሁላችንም መሆን አለበት፡፡

6. ከትከሻዋ በታች ወርዶ የሚዘናፈለው ዞማ ፀጉሯ ውበቷን አጉልቶታል፡፡

ክፍል አራት ጽሕፈት

ጅምር አንቀፆችን መጨረስ

መልመጃ፡- 32

፡-የሚከተሉትን ተጀምረው ያልተጠናቀቁ አንቀጾች አሟልታችሁ በደብተራችሁ ፃፉና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ሀ. ልጅቱ ልቅም ያለች ቆንጆ ናት፡፡ ጫማ የላትም ነገር ግን እግሯ እንሶስላ የሞቀች ይመስላል፡፡ ፀጉሯ ሽቶና ዘይት ነክቶት አያውቅም፤ በሳሙና ለመታጠብ እንኳን እድል አላገኘም፤ሆኖም እየተዘናፈለ ወርዶ የተከበረውን ትከሻዋን አጥለቅልቆታል፡፡መዘናፈሉም መልሰው መላልሰው ያጠፉት ይመስላል፡፡ አይኖቿ ኩል አያውቁም ነገር ግን . . . ፡፡ (ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፣2008 ገፅ307)

ለ. የሾላ ወተት ፋብሪካ የሚሸጠው ወተት ህዝብ ዘንድ ከመድረሱ በፊት ብዙ ሂደቶችን ማለፍ አለበት፡፡ በመጀመሪያ ወተቱ በፋብሪካው ውስጥ ካሉ ላሞችና በአዲስ አበባና በዙሪያዋ ካሉ ገበሬዎች ይገዛል፡፡ ይህ የተገዛ ወተት በትላልቅ የብረት ጋኖች ተሞልቶ በተሽከርካሪ ተጭኖ ፋብሪካው ዘንድ ይደርሳል፡፡ ፋብሪካው ተቀብሎ እየመዘነ ወደ ማፍያ ጋን ውስጥ ይገለብጣል፡፡ ጋኑ ወተቱን በ100 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ያፈላና ወደ ሁለተኛው ማሽን በትላልቅ ቱቦ ያስተላልፈዋል፡፡ ሁለተኛው ማሽን በ22 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ እንደገና ያፈላና ወተቱ ውስጥ ያለውን ክሬም ይለያል፡፡ ከዚያም….፡፡(ደረጀ ገብሬ፣1996 ገፅ164)

፪፡- ከላይ ከቀረቡት ያልተሟሉ ሁለት አንቀጾች መካከል መረጃ ሰጭ የሆነው የትኛው ነው? ለመልሳችሁ ምክንያት ስጡ፡፡

፡፡፫፡- ቀጥሎ ባለው አንቀጽ ውስጥ ያሉትን መሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን ለይታችሁ በደብተራችሁ ጻፉ፡፡

ምንም እንኳን የሰላም መስፈን ለሰው ልጆች ህልውና አስፈላጊ መሆኑ ባያጠያይቅም በአንፃሩ ደግሞ ሁከትና ብጥብጥ የሚናፍቁ ሰዎች መኖራቸው የሚካድ አይደለም፡፡ የነዚህ ሰዎች አይናቸው መልካም ነገርን ማየት፣ጆሯቸው ቸር ወሬ መስማት አይፈልግም፡፡ ይህ ደግሞ ያለምክንያት አይደለም፡፡ ‹‹የገበያ ግርግር ለሌባ ይመቻል›› እንዲሉ እነዚህ ሰዎች ሰላማዊ በሆነ መንገድ ሰርተው ከማግኘት ይልቅ በግርግር መሃል በአቋራጭ መክበር ስለሚፈልጉ ነው፡፡ስለዚህ የዘወትር ምኞታቸው ስለሰላም ሳይሆን ስለብጥብጥና ሁከት ነው፡፡ይሁን እንጅ በአቋራጭ ያገኙት ገንዘብ ሰላም እየነሳ እንደ አንበሳ ሲያስበረግጋቸው፣ እንደ ቆቅ ሲያስደነብራቸው ይስተዋላሉ፡፡ ምክንያቱም ‹‹ከመቀመጫዉ ላይ ቁስል ያለበት ውሻ እንደልቡ አይጮህም›› እነደሚባለው እያንዳንዱ እርምጃቸው በስጋትና በጥርጣሬ የተሞላ ነው፡፡(ታለጌታ ይመር ፣2007፣ ከገፅ 171-172)

፬፦ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን አያያዥ ቃላትቀጥሎ በቀረበው ባዶ ቦታ ውስጥ በማስገባት አንቀፁ የተስተካከለ የሀሳብ ፍሰት እንዲኖረው አድርጉ፡፡

| | |
|---|---|
| ነገር ግን | ይሆን ዘንድ |
| ስለዚህ | ያለምክንያት |
| ቢሆንም | እርግጥ ነው |
| እና | |

ሰው ከተሰማራ እንደየስሜቱ በዋለበት ስፍራ አይቀርም ማፍራቱ የተባለው--1-- አይደለም፡፡የሰው ልጁ በስራው ደስተኛ----2---- ውጤታማ----3---- እንደፍላጎቱ መሰማራትአለበት፡፡----4---- የእለት ጉርሱን ላለማጣት ሲል እየመረረው-----5----

ሊሰራ ይችላል፡፡----6---- ስራውን የሚሰራው ያለፍላጎት በመሆኑውጤቱ አመርቂ አይሆንም፡፡----7---- ያለፍላጎት መኖር ብቻ ሳይሆን ችሎታም ትልቅ ድርሻ አለው፡፡

# ክፍል አምስት ሰዋስው

## ተውላጠ ስም

ማስታወሻ፡-

ተውላጠ ስም ስምን ተክቶ በመግባት የስምን ተግባር የሚፈጽም የስም ክፍል ነው፡፡ ነጠላና ብዙ ቁጥር አመልካች ተብሎ ሊከፈል ይችላል፡፡ ምሳሌ ፡- እሱ ፣ እናንተ ፣ እኛ

መልመጃ፡- 33

ሀ፡- የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ስሞችንና ተውላጠ ስሞችን ለይታችሁ በደብተራችሁ ፃፉ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. አስቴር | ሠ. ናትናኤል | ቀ. እሱ |
| ለ. ሀሰን | ረ. አንቺ | በ. እኔ |
| ሐ. እሷ | ሰ. ኤደን | ተ. እናንተ |
| መ. እኛ | ሸ. አንተ | ቸ.እነሱ |

| ተ/ቁ | ስም | ተውላጠ ስም |
|---|---|---|
| 1 | ሀሰን | እሱ |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |

| 6 | | |
|---|---|---|

፪፡- ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ በተውላጠ ስም ስር የመደባችኋቸውን ስሞች በመጠቀም አረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ምሳሌ፡- እሱ ነገ ከባህርዳር ወደ አዲስ አበባ ይገባል፡፡

እሷ ዛሬ ከዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ትቀበላለች፡፡

፫፡- ተስማሚ ተውላጠ ስሞችን በክፍት ቦታው በማስገባት ዓረፍተ ነገሩን አሟሉ፡፡

ሀ. ---------እና -------- ተባብረው ቢሰሩ ኑሯቸውን ማሸነፍ ይችላሉ፡፡፡

ለ. -------በትምህርቷ ጎበዝ ልጅ ናት፡፡

ሐ.--------መፅሀፍ ማንበብ የእለት ከዕለት ስራው ነው፡፡

መ.-------ኢትዮጵያን በጣም ይወዳሉ፡፡

ሠ. ---------በህይወቴ ስንፍናን አልወድም፡፡

ረ.----------ለምን ትምህርት ቤት ለመምጣት ታረፍዳለህ?

ሰ. --------ከሌሎች ተማሪዎች በስ-ነምግባር የተመሰከረላችሁ ናችሁ፡፡

፬፡- በተሰጠው ምሳሌ መሰረት በሚከተሉት ስሞች ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

ምሳሌ፡- ዕፅዋት- ዕፅዋት የፀሐይ ብርሃንን ተጠቅመው ምግባቸውን ያዘጋጃሉ፡፡

ብዕር -የሚፅፍበት ብዕር ደማቅ ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ሠዓት | መ አዲስ አበባ | ሰ.ጠረጴዛ |
| ለ. አባይ | ሠ. እንስሳት | ሸ. ወረቀት |

ሐ. መስኮት ረ. እንጀራ ቀ. አሳ

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስር የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች የተመለከትን ሲሆን እማሬያዊ ፍች ቃላት የሚኖራቸው ቀጥተኛ ፍች ሲሆን ፍካሬያዊ ደግሞ ቃላት ከቀጥተኛ ፍቻቸው ባሻገር የሚኖራቸው ሚስጥራዊ ፍቺ እንደሆነ ለማየት ሞክረናል፡፡በሌላ በኩል አውዳዊ ፍች ስንል ቃላት በተለያየ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ሲገቡ የሚሰጡት ፍች መሆኑን አይተናል ፡፡አያያዥ ቃላትን በተገቢው ቦታ በማስገባት አንቀጽን አሟልተን ጽፈናል፡፡ አያያዝ ቃላት የፅሁፍ ትስስር እንዲኖር የሚያደርጉ ናቸው፡፡በመጨረሻም የስምና የተውላጠ ስምን ምንነት በማየት በዓረፍተ ነበር ውስጥ በተገቢው ቦታ በማስገባት ተጠቅመናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. በሚከተሉት ቃላት ዓረፍተ ነገር ሰርታችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

   ሀ. አወቀ ሐ. አጠበች ሠ. ሰጠ

   ለ. መጡ መ. ተደሰተች ረ. በላሁ

2. የስምና የተውላጠ ስም ምንነት፣ አንድነትንና ልዩነታቸውን በቃል አብራሩ፡፡
3. በጽሁፍ ውስጥ አያያዥ ቃላት ምን አይነት ጥቅም እንዳላቸው ግለጹ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት


## የጥላቻ ንግግር

❖ ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ ሚቀርብላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ ትመልሳላችሁ
- ✓ መግባባትና አለመግባባትን የሚገልፁ ሀሳቦችን ታቀርባላችሁ
- ✓ ምንባቡን በማንበብ የጥላቻ ንግግር እንዴት እንደሚወገድ ትገልፃላችሁ
- ✓ ቀላልና ዉስብስብ አረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ
- ✓ ቅፅሎችን በመለየት ትጠቀማላችሁ
- ✓ የጥላቻ ንግግርን እንዴት መከላከል እንደሚቻል ትገልፃላችሁ
- ✓ ‹‹እናን›› እና ‹‹ነገር ግንን›› ተጠቅማችሁ ነጠላና ውስብስብ አረፍተ ነገሮችን ትመሰርታላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## ‹‹ የጥላቻ ንግግርና የሚያስከትለው ጉዳት ››



### ቅድመ ማዳመጥ

**መልመጃ፡-34**

**ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች፡-፩**

**ሀ. ምስሉና ርዕሱ ምን አይነት ቁርኝት ያላቸው ይመስላችኋል?**

**ለ. ርዕሱን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለ ምን እንደሚናገር ገምቱ፡፡**

### የማዳመጥ ሂደት

**‹‹ የጥላቻ ንግግርና የሚያስከትለው ጉዳት›› በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ መምህራችሁ ሲያነብላችሁ በትኩረት አዳምጡ፡፡**

## አዳምጦ መረዳት

**፩፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት እውነት ወይም ሐሰት በማለት በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. በሩዋንዳ የዘር ጭፍጨፋ የተሳተፉት ባለስልጣናት ብቻ ነበሩ፡፡

ለ. በጥላቻ ንግግር የተነሳ በዓለም ላይ ብዙ እልቂቶች ተከስተዋል፡፡

ሐ. የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት በት/ቤት መከላከል ይቻላል፡፡

መ. በማህበራዊ ገጽ የሚሰራጩ አግላይ መረጃዎች ከጥላቻ ንግግር አይመደቡም፡፡

ሠ. የሩዋንዳ ጭፍጨፋ የተተገበረው በቱትሲ ጎሳዎች ላይ ነበር፡፡

ረ. የጥላቻ ንግግር በሰዎች ላይ አሉታዊ አስተሳሰብ ያሳድራል፡፡

**፫፡-በሚከተሉትቃላት አገባባዊ ፍች የሚያሳይ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

- ምሳሌ 1፡- ግጭት

  ሰዎች በጥላቻ ንግግር ሰበብ ወደ ግጭት መግባት የለባቸውም፡፡

- ምሳሌ 2፡ ፋይዳ

  ለሀገር ፋይዳ ያለው ነገር ለማበርከት መተባበር ያስፈልጋል፡፡

ሀ. መናጃ ሐ. ማፈንገጥ ሠ. ማጎልበት ሰ. ገደብ

ለ. ትስስር መ. ጥላቻ ረ. ማግለል ሸ. በእንዝህላልነት

**መልመጃ 35**

**ከዚህ በታች ከተጠቀሱት ርዕሶች መካከል አንዱን መርጣችሁ በመዘጋጀት ንግግርአቅርቡ፡፡**

**ሀ. የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት እንዴት ሊስፋፋ ይችላል?**

**ለ. ህግ በማውጣት ብቻ የጥላቻ ንግግርን መከላከል የሚቻል ይመስላችኋል?**

**በምክንያት አስደግፋችሁ አብራሩ፡፡**

**ሐ. በጥላቻ ንግግርና በሐሰተኛ መረጃ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?**

## ክፍል ሁለት፡- ማንበብ

**‹‹የጥላቻ ንግግር››**




**በሚዲያ የጥላቻ ንግግር የሚያቀርብ ሰው ይኖራል ሌሎች አድማጮች መስማት አለመፈለጋቸውን የሚያሳይ ስዕል ይገባል**

## ቅድመ ንባብ

**መልመጃ፡-36**

**ሀ. የጥላቻ ንግግር ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?በምን ምክንያት ሊፈጠር ይችላል?**

**ለ. በማህበረሰቡ ላይ ምን ጉዳት ያስከትላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?**

**ሐ. መገለጫዎቹ ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ?**

## የንብብ ሂደት

ቀጥሎ የቀረበውን ምንባብ በየተራ እየወጣችሁ ድምፃችሁን ከፍ በማድረግ በትክክል አንብቡ

የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጨት ውጤታቸው ተመሳሳይ ቢሆንም አካሄዳቸው ግን የተለያየ ነው፡፡ የጥላቻ ንግግርን ምንነት በተመለከተ ቁርጥ ያለና ወጥ ብያኔ የለውም፡፡ ይሁን እንጅ በርካታ ብያኔዎች የሚጋሯቸው ነጥቦች አሉ፡፡ ማንኛውም የዘር ጥላቻን፣ የሌላ ሀገር ዜጋን ወይም ስደተኛን በጭፍኑ መጥላት፣ትዕግስት አልባ አግላይና ሌሎች ሰበብ እየፈለጉ መገለል እንዲደርስባቸው የሚሰብኩ፣ የሚያሰራጩ፣የሚያነሳሱ፣ የሚያበረታቱገለፃዎች፣ ፅሁፎች፣ ምስሎችና ስዕሎች፣ ቅርፃቅርፃች በሙሉ የጥላቻ ንግግር ይሰኛል፡፡ የጥላቻ ንግግር እጅግ ብዙ የሆኑ በጎ እሴቶችን የመናጃ መንገድ ነው፡፡ ጥላቻ ላይ የተመሰረቱ ወንጀሎችን መጥሪያም ነው፡፡ አድሎና መገለልን ያስከትላል፡፡ የአንድን ወገን አባላት፣የሀይማኖት ተከታዮች፣ስደተኞችንና ሌሎች ቡድኖችን ያለምንም ተጨባጭ ምክንያት በጭፍኑ እንዲጠሉ መንገድ ይከፍታል፡፡

1. ታሪኩን ከማንበባችሁ በፊት የሰጣችሁት ግምት ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ለምን? የምንባቡ የእስካሁን ክፍል ምን ምን ነጥቦችን አንስቷል?
2. ቀጣዩ የምንባብ ክፍል ምን ሀሳብ የሚያነሳ ይመስላችኋል?

ሐሰተኛ መረጃ የመረጃውን ሐሰተኝነት ወይም እውነተኛነት ለማጣራት በቂ ጥረት ሳይደረግ የሚሰራጭ ሲሆን ሁከት፣ ግጭትና ጥቃት እንዲደርስ የሚያደርግ ተግባር ነው። የሀሰተኛ መረጃ ህዝብን፣ ሃይማኖትን፣ ዘርን፣ ፆታን፣ አካል ጉዳተኝነትን ወይም ሌሎች በህግ የተጠበቁ ልዩነቶችን መሰረት በማድረግ የሚፈጸም የማግለልና መድሎ የመፍጠር ሁኔታንም ጭምር ያካተተ ተግባር ነው። የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት በሚከናወንበት ጊዜ በግለሰብ፣ በቡድን፣ በንብረትና በህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል።

የጥላቻና ሀሰተኛ ንግግር ሆን ተብሎ፣ ታስቦበት ወይም በእንዝህላልነት የሚሰራጭ ንግግር ሲሆን በሕግ መከልከልና መቆጣጠር አስፈላጊ ነው። የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ለማህበራዊ ግንኙነት፣ ለፖለቲካ መረጋጋት፣ ለሃገራዊ አንድነት፣ ለሰብአዊ ክብር፣ ለብዝሃነትና ለእኩልነት ጠንቅ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። በመሆኑም በመሰረታዊ የሰው ልጅ መብት ላይ የሚጣሉ ገደቦች በሕግ መደንገግ አለባቸው። ኢትዮጵያም በዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ውስጥ ተቀባይነት ያለውን ዓላማ ለማሳካት አስፈላጊ የሆኑ፣ተመጣጣኝና በልኩ የተበጀ የጥላቻና የሀሰተኛ ንግግር አዋጅ ደንግጋለች።

የጥላቻ ወይም ሀሰተኛ ንግግር በተለያዩ የህትመትና የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አማካኝነት የሚተላለፍ ነው። የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት በማናቸውም የመረጃ ማሰራጫ መንገዶችና ስልቶች አማካኝነት ለበርካታ ሰዎች እንዲደርስ ማድረግ ነው።ሰዎች መረጃን በማህበራዊ መገናኛ ብዙሃን መልዕክት ለመለዋወጥ፤ትስስርን ለማዳበር፤ ሀሳብን ለመጋራት የምንጠቀምበት በበይነ መረብ (ኢንተርኔት) አማካኝነት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች መረጃ የሚደርስበት ዘዴ ነው።

ይህ ተግባር መረጃ የመጋራት ተግባር እውቀትን፣ ክህሎትንና ልዩ ልዩ ቴክኖሎጅዎችን ለመረዳት ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ በተቃራኒው ከማህበረሰቡ እምነትና እሴት ያፈነገጡ፣እኩይ ነገሮችን ለማጉላት፣በመረጃና በማስረጃ ያልተጣሩ ነገሮችን ለማሰራጨት፣ በሰዎች መካከል ልዩነትን ለመፍጠር ሆን ተብሎ በሚሰራበት ጊዜ መጠራጠርን ይፈጥራል፡፡

ሰዎች ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ መብታቸውን ሲጠቀሙ ግጭት የሚቀሰቅስ፣ ሕዝብን፤ ሃይማኖትን፤ዘርን፣ ጾታን እና አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥላቻ ከሚያስፋፋ ንግግር እንዲቆጠቡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ መቻቻልን፣ መተማመን፣ መከባበርና መግባባትን ማበረታታትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማጎልበት የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃዎችን ስርጭት ለመቆጣጠር ጠቀሜታቸው ከፍተኛ ነው፡፡

የጥላቻ እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን የመከላከል ሀላፊነት የሁሉም ሰው ድርሻ ነው፡፡ ማንኛውም ሰው በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚዲያዎችና መሰል ዘዴዎች አማካኝነት በጽሁፍ፣ በስዕል፣ በድምጽ ወይም በተንቀሳቃሽ ምስል ማሰራጨት በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ በአንፃሩ ትምህርታዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምር፣ ትክክለኛ እና እውነተኛ የዜና ዘገባ፣ የፖለቲካ ትንታኔ ወይም ትችት፣ ልዩ ልዩ ኪነ-ጥበባዊ ትወናዎችና ፅሁፎች፣ የሃይማኖታዊ አስተምህሮቶች፣ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ምክክሮችና ውይይቶች ወዘተ እንደ ጥላቻ እና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት ተደርገው አይወሰዱም፡፡

ማንኛውም ሰው ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቱን ተጠቅሞ የተከለከለውን የጥላቻ ንግግር በማድረግ ለግጭትና ለብጥብጥ ምክንያት የሚሆን ከሆነ በአዋጅ አንቀፅ 4 መሰረት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና ከ፪ሺ ያልበለጠ የገንዘብ መቀጮ የሚቀጣ ይሆናል፡፡

በጥላቻ ንግግር ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ አመት እስከአምስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል፡፡ በአዋጅ አንቀፅ ፭ መሰረት ክልከላ የተደረገበትን ተግባር የፈጸመ እንደሆነ ደግሞ እስከአንድ ዓመት በሚደርስ በቀላል እስራት ወይም ከብር ፶ሺ ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል፡፡ የጥላቻ ንግግር ወይም የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ወንጀሉ የተፈጸመው ከአምስት ሺ በላይ  ተከታይ ባለው የማህበራዊ ሚዲያ፣ በሬዲዮና በቴሌቪዥን እንዲሁም በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ውጤት ከሆነ ግን ቅጣቱ እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት እና ከብር ፻ሺ ያልበለጠ መቀጮ የሚያስቀጣ ይሆናል፡፡

ሐሰተኛ መረጃ በመሰራጨቱ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ ከሆነ፣እና ሁከት ወይም ግጭት ከተከሰተ ከሁለት እስከአምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ያስቀጣል ፡፡

በጥላቻ ንግግር ወይም በሐሰተኛ መረጃ ወንጀል መፈጸም ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት ያልተፈጸመ ወይም ያልተሞከረ ከሆነ፣ ግን ሁከት ወይም ግጭት ያልተከሰተ እንደሆነ እና ጥፋተኛውን ለማረም የተሻለ ነው ብሎ ሲያምን ፍርድ ቤቱ በእስራት ምትክ የግዴታ የማህበረሰብ አገልግሎት ስራን በአማራጭ ቅጣትነት ሊወስን ይችላል፡፡

ምንጭ (የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ 26ኛ አመት ቁጥር 26 ገፅ 12339 መጋቢት 14 ቀን 2012 ዓ.ም መሰረት ተደርጎ ለማስተማር ተሸሽሎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

**፩፦የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ትክክል ከሆኑ‹‹እውነት›› ትክክል ካልሆኑ ‹‹ ሐሰት›› በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ በፅሁፍ መልሱ፡፡**

ሀ. ሐሰተኛ መረጃ ማለት በቂ ማጣራት ሳይደረግበት የሚተላለፍ መረጃ ነው፡፡

ለ. የጥላቻ ንግግር ማግለልና መድሎን ያጠቃልላል፡፡

ሐ. ሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ተመሳሳይ ትርጉም አላቸው፡፡

መ. የጥላቻ ንግግር በሕይወትና በንብረት ላይ ጉዳት ያስከትላል፡፡

ሠ. ለሐሰተኛ መረጃ ስርጭት መገናኛ ብዙሃን ድርሻ የላቸውም፡፡

ረ. የጥላቻ ንግግር በማሕበረሰቡ ላይ ችግር አያስከትልም፡፡

ሰ. የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን መከላከል የፍርድ ቤት ድርሻ ነው፡፡

ሸ. መቻቻልና መከባበርን ማዳበር የጥላቻ ንግግርን ለማስወገድ ይጠቅማል፡፡

፪፦ የሚከተሉትን ቃላት ከመዝገበ ቃላት ፍቻቸውን ፈልጋችሁ በደብተራችሁ ፃፉ

ሀ. አብነት ሐ. ምናብ ሠ. ሙስና ሰ. ዳጎሰ ቀ. አጥቢያ

ለ. ደባ መ. ለበጣ ረ. ሰርግና ምላሽ ሸ. አጤነ

# ክፍል ሶስት፡- ቃላት

## የቃላት አገባባዊ ፍቺ

**መልመጃ፡-37**

**፩፡- በ‹‹ሀ››ስር ለቀረቡት ቃላት በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘሩት በፍቺ ተመሳሳይ የሚሆኑትን እየመረጣችሁ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የውሃ ሽታ | ሀ.አንድነት |
| 2. ህብር | ለ. ግምገማ |
| 3. ቃል አባይ | ሐ. ብርድ |
| 4. ቆፈን | መ. ዋሾ |
| 5. ሂስ | ሠ. ደብዛው የጠፋ |
| | ረ. ወንዝ |
| | ሰ. ግለሰብ |

**፪፡- ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ እየሰጣችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ሀ. ስኬት ሐ. ቆረጠ ሠ. መዘርጋት

ለ. አንጋፋ መ. መዋለል ረ. ታታሪ

# ክፍል አራት ጽሕፈት

## አመሳስሎ መፃፍ

**መልመጃ፡-38**

**፩፡-የሚከተሉትን አረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሰረት ሀቅና የግል አስተያየት በማለት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

**ምሳሌ፡-**

- ባልና ሚስቱ የታረቁት በሀገር ሽማግሌዎች ሳይሆን አልቀረም፡፡ የግል አስተያየት ላይ የተመሰረተ
- ተማሪው ያስመዘገበው ውጤትወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ አያሸጋግረውም፡፡ በሀቅ ላይ የተመሰረተ

ሀ. ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡት ተማሪዎች ሽልማት ተሰጣቸው፡፡

ለ. ዘመናችን ሳይንስና ቴክኖሎጅ እየተስፋፋ የመጣበት ዘመን ነው፡፡

ሐ. ሁሉም ጎበዝ ተማሪዎች በስነ- ምግባራቸው የተመሰገኑ ናቸው፡፡

መ. ሰርግ መደገሱን የተወችው ገንዘብ ስለቸገራት ሳይሆን አይቀርም፡፡

ሠ. ህፃናት በስነ- ምግባር ታንፀው ማደግ አለባቸው፡፡

ረ. በወጣትነት ዘመን ትዳር መያዝ ለድህነት ያጋልጣል፡፡

ሰ.ሁሉም ቋንቋ የተናጋሪዎችን ባህልና ወግ በመግለፅ ረገድ እኩል ናቸው፡፡

ሸ. የኑሮ ውድነት በቀጣይ አመት መሻሻሉ አይቀሬ ነው፡፡

ቀ.ህፃናት እስከ ስድስት ወር ድረስ የእናት ጡት ቢጠቡ ለጤናቸው ተስማሚ ነው፡፡

በ. የሕዳሴ ግድብ ከሀገራችን አልፎ ለጎረቤት ሀገሮች የሚሰጠው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው፡፡

ተ. አገር በቀል እዉቀት በቅጡ ቢጠና ከዘመናዊዉ ሳይንስ ሳይሻል አይቀርም፡፡

ቸ. የእጅ ንጽህና በመጠበቅ፡ ርቀትን በመጠበቅና ጭንብል በመጠቀም የኮሮናን በሽታን መከላከል ይቻላል

፪፡- ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀፅ በትክክል አንብባችሁ ተመሳሳይ ፅሁፍ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

የክረምት ወቅት ነው፡፡ ዝናቡ ያዝ ለቀቅ እያደረገ ሲያስቸግር ውሏል፡፡ ፀሐይም በተራዋ ብቅ ጥልቅ እያለች ቆይታ በመካከሉ ጭርሱን ተሸሽጋለች፡፤ ወጨፎ ያዘለው ነፋስም ደረስ መለስ እያለ ሰው ማወኩን ተያይዞታል፡፡ ወደ ሀገሯ ለመሄድ ያሰበችው መንገደኛዋ አስቻጋሪ በረሃ በጠራራ ፀሐይ ከማቋረጥ በጠፍ ጨረቃ መጓዝ እንደሚሻል ሲያወሩ ሰምታለች፡፡ በየስራው ቦታ ደፋ ቀና ስትል ኖራ ባጠራቀመችው ገንዘብ የገዛችውን አዲስ ልብስ ለብሳ በቄንጠኛ አረማመድ ሰበርሰካ እያለች ጉዞዋን ቀጠለች፡፡ እስከ ውድቅት ከተጓዘች በኋላ ቅስፍ የሚያደርግ ውጋት ስለተሰማት እርምጃዋን ቀነሰች፡፡ የልብ ትርታዋ ጨምሯል፡፡ትንፋሿ በዝቷል፡፡ ድካሙ ልቧን ፍስስ እያደረገ ስላስቸገራት ትንፋሿን ለመሰብሰብ አረፍ አለች፡፡ ትንፋሿ መለስ ሲል ቀና ብላ ብታይ የክረምት ሌሊት አይመስልም፡፡ ከዳር እስከ ዳር ፍንጥቅጥቅ ያሉት ከዋክብት ለዚያ ድቅድቅ ጨለማ ፀዳል ሰጥተውታል፡፡ ባጠራቀመችው አዲስ ጉልበት ዳገቱን ጨርሳ አውላላ ሜዳ ላይ ደረሰች፡፡ ወዲያው ከየት እንደመጡ ሳይታወቅ ለቁጥር የሚያዳግቱ አውሬዎች ከበቧት፡፡በድንጋጤ ላብ አጥምቋት ብንን ብትል ለካስ ይሔ ሁሉ በህልሟ ኖሯል፡፡ምንጭ፡-(ከአስረኛ ክፍል አማርኛ የተማሪው መፅ"ሀፍ የተወሰደ 2004፣5-6)

# ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

## ቀላልና ዉስብስብ አረፍተ ነገር መለየት

**መልመጃ፡-፴፰**

**፩፡-ቀጥለው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች በምሳሌው መሰረት ቀላል ወይም ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በማለት ለይታችሁ አሳዩ፡፡**

ሀ.ሀያት እና መአዛ ትረካ ይወዳሉ፡፡ ቀላል ዐረፍተ ነገር

ለ.ናትናኤል ያነበበውን መፅሀፍ ለወንድሙ መለሰ፡፡ውስብስብ ዐረፍተ ነገር

ሀ. አስናቀችና ዘሪቱ እህትማማቾች ናቸው፡፡

ለ. የአየር ባየር ንግድ መነገድ ሀገርንና ወገንን ይጎዳል፡፡

ሐ. ተማሪዎቹ ወደ ሰባተኛ ክፍል ተዘዋወሩ፡፡

መ. ሀዲስ አለማየሁ የፍቅር እስከ መቃብር ደራሲ ናቸው፡፡

ሠ. በበዓላት ጊዜ አዳዲስ ልብሶችን መልበስ እወዳለሁ፡፡

ረ. ሰውን ያለጥፋቱ መጉዳት ህሊናን ያደማል፡፡

ሰ. መምህሮቻችን በስነ-ምግባራቸው የተመሰገኑ ናቸው፡፡

ሸ. አለሙ ለእናቱ ውሃ ቀዳ፡፡

ቀ.ኳስ መጫወት እውዳለሁ ግን እንድጫወት አይፈቀድልኝም፡፡

በ. መሀመድ በሚገባ ጊዜውን ከፋፍሎ ስለሚያጠና ፈተናውን አለፈ፡፡

**፪፡-ቀጥሎ በቀረቡትዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ያሉትን ግሶች በምሳሌው መሰረት ለዩና በደብተራችሁ ፃፉ፡፡**

**ምሳሌ፡-**

**ፍቅርተ ጓደኛዋ ያቀበለቻትን ኳስ መታች፡፡ አቀበለቻት፣መታች**

**የጓሮ አትክልት በመሸጥ ቤታቸውን አሳመሩ፡፡ በመሸጥ፣ አሳመሩ**

**ሀ. መአዛ አባቷ ስለመጡ ተቀበለቻቸው፡፡**

**ለ. ያሲን ከተቀመጠበት ፈጥኖና በርግጎ ተነሳ፡፡**

**ሐ. አዛውንቶቹ በጥምቀት በዓል በርኖስ ለብሰዋል፡፡**

**መ.አያቴ የገዙት መኪና በጣም ያምራል፡፡**

**ሠ.ከትምህርት ቤት ሲመለስ የደንብ ልብሱን ቀየረ፡፡**

**ረ. የሞት አደጋ ሲያጋጥም የሟች ቤተሰብን ማፅናናት ያስፈልጋል፡**

**፫፡- (እና) እና (ነገር ግን) የሚሉትን አያያዥ ቃላት በመጠቀም በምሳሌው መሰረት ስምንት ውስብስብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡**

**ምሳሌ፡-**

**ሀ. ፋልታሞ እና ብርብርሳ ያነበቡትን ታሪክ ለክፍል ጓደኞቻቸው ነገሯቸው፡፡**

**ለ. ያች ልጅ ጎበዝ ተማሪ ናት ነገር ግን መቅረት ታበዛለች፡፡**

፬፡-ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቅፅሎች በተሰጠው ምሳሌ መሰረት የአይነት፣ የባህሪና የመጠን አመልካች እያላችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ መድቡ፡፡

ሰነፍ በጎ ሞኝ ሆዳም ሰማያዊ

አጭር ረጅም ደንዳና ሮዝ ቀያይ

ንቁ ግዙፍ አረንጓዴ ጠባብ

| ተ/ቁ | አይነት አመልካች ቅፅል | ባህሪ አመልካች ቅፅል | መጠን አመልካች ቅፅል |
|---|---|---|---|
| 1 | ቢጫ | ሩህሩህ | ቀጭን |
| 2 | | | |
| 3 | | | |
| 4 | | | |
| 5 | | | |

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ሀቅና የግል አስተያየት ምንነት ለማየት ሞክረናል፡፡ ሀቅ የሚባለው በእውነታ ላይ የተመሰረተ ሲሆን የግል አስተያየት ደግሞ በየግለሰቡ አመለካከት የሚወሰንና የሚሰነዘር ሀሳብ እንደሆነ አይተናል፡፡ ቅፅል ከስም በፊት እየገባ ስሙን ከአይነት ፣ ከመጠንና ከባህሪ አንፃር የሚገልጽ መሆኑን ተምረናል፡፡ እና፣ ነገር ግን የተባሉትን አያያዥ ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ በማስገባት ተጠቅመናል፡፡ የጥላቻ ንግግር ምንነትና ጉዳት ተረድተን መከላከልና ማስወገድ የሚቻልበትን መንገድ ግንዛቤ አግኝተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የሐሰተኛ መረጃና የጥላቻ ንግግር ያላቸውን ግንኙነት አብራሩና እንዴት መከላከል እንደሚቻል ተወያዩ፡፡
2. እና፣ ነገር ግን በሚሉት አያያዥ ቃላት አራት ዓረፍተ ነገር ሰርታችሁ አሳዩ፡፡
3. ሀቅ እና የግል አስተያየት ምንነትና ልዩነት አብራርታችሁ ተናገሩ፡፡
4.

# ምዕራፍ ስምንት

## ኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ በኢትዮጵያ

❖ **ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-**

- ✓ የሚቀርቡ ጽሁፎችን አዳምጣችሁ ትመልሳላችሁ፡፡
- ✓ በሂደት ባለብዙ ቅጥያ ምዕላዶችን ታነባላችሁ፡፡
- ✓ ቃላትንና ሃረጋትን ነጣጥላችሁና አጣምራችሁ ታነባላችሁ
- ✓ የራሳችሁን አመለካከት ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ የድርሰት ክፍሎችን ትገልፃላችሁ፡፡
- ✓ ለምዕላዶች ትርጉም ትሰጣላችሁ፡፡

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

‹‹ ጠርጥር በገንፎ ዉስጥ አለ ስንጥር ››





## ቅድመ ማዳመጥ

መልመጃ፡-39

፩፡-ምንባቡን ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ‹‹ ጠርጥር በገንፎ ዉስጥ አለ ስንጥር›› የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?

ለ. ርዕሱን ተመልክታችሁ ምንባቡ ስለምን ሊገልጽ እንደሚችል ገምቱ፡፡

ሐ. ማንኛውም ሰው ወደችግር እንዳይገባ አስቀድሞ ምን ማድረግ አለበት ብላችሁ ታስበባላችሁ?

**የማዳመጥ ሂደት**

‹‹ጠርጥር በገንፎ ዉስጥ አለ ስንጥር›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ተራኪ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ የድርጊት ቅደም ተከተሉን ጠብቃችሁ አዳምጡ፡፡

**አዳምጦ መናገር**

**፩፡-የሚከተሉትን ቃላት ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረትበቃል ፍቺ ስጡ፡፡**

ሀ. ጠቃሚ መ. ተጋላጭሰ. አገገመ

ለ. እጣ ፋንታ ሠ. መረጋጋት ሸ. ትርፍ

ሐ. ስላፈራሁ ረ.ምክር ቀ.ማቋረጥ

**፫፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ ሀሳባችሁን በቃል አቅርቡ፡፡**

ሀ. በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ኤድስ እንዴት ይተላለፋል?

ለ. እራሳችንን ከበሽታውእንዴት መከላከል እንችላለን?

ሐ. የኤድስ በሽታ ከሌሎች በሽታዎች ጋር ያለውን ግንኙነት አስረዱ፡፡

ሠ. እናንተ ስለኤድስ መማራችሁ ምን ጠቀሜታ አለው?

ረ. ከባለታሪኩ ምን ተረዳችሁ? እናንተ ባለታሪኩ ብትሆኑ ምን ታደርጉ ነበር?

፬፡-ለኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑት ወንዶች ናቸው ወይስ ሴቶች? በሚለው ርእስ ላይ ተወያዩና ንግግር አድርጉ፡፡

# ክፍል ሁለት፡- ማንበብ

## የኤች አይቪ ኤድስ ተፅዕኖ



### ቅድመ ንባብ

**የቀደመ እዉቀትን መቀስቀስ**

መልመጃ፡- 40

ሀ. ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቀዎች በቃል መልሱ

1. ሰዎች ስለኤች አይቪኤድስ በግልጽ አለመወያየታቸው ምን ጉዳት ያስከትላል?
2. ቫይረሱ በዋናነት የሚተላለፍባቸው መንገዶች ምን ምን ናቸው?
3. ወጣቶችን ለበሽታው ተጋላጭ የሚያደርጉ ምክንያች ምንድን ናቸዉ?

## የንባብ ሂደት

ቀጥሎ ‹‹የኤች አይ ቪ ኤድስ ተፅዕኖ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ የሀሳቦችን ምክንያትና ውጤት ግንኙነት በማስተዋል በለሆሳስ አንብቡ፡፡

የኤች አይ ቪ ኤድስ ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ችግሮችን እያስከተለ ይገኛል፡፡የማህበረሰቡ ጤናና ምጣኔ ሃብት ላይ የሚያሳድረውም ተፅዕኖ ቀላል አይደለም፡፡ በተለይም በወጣቶችና በጎልማሶች ላይ ያለው ስርጭት የጎላ ነው፡፡ የተማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በበሽታው እየተጠቁ በሚመጡበት ወቅት ደግሞ በሀገር ላይ የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት ያጋጥማል፡፡

በዚህም በሀገር እድገት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትላል፡፡ የቫይረሱ መስፋፋት

የምጣኔ ሀብትና የጤና ችግር ከማስከተሉም በተጨማሪ የሀገርን የህዝብ ስብጥር ያዛባል፡፡በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ ኤች ኤ ቪ ኤድስ ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰባቸውየማህበረሰብ ክፍሎች ከ15-49 የዕድሜ ክልል ያሉት ናቸው፡፡ በዚህ ዕድሜ ክልል የሚገኙት ደግሞ አምራች ዜጎች ናቸው፡፡ ማምረት የማይችሉት የሚያድጉ ህፃናትና አረጋዊያን የሚደገፉት በነዚህ አምራች ክፍሎች ነው፡፡ ወጣቶችና ጎልማሶች በቫይረሱ እየተጠቁ ከሄዱ ደግሞ ህፃናትና አረጋዊያን ያላሳዳጊና ያለጧሪ ይቀራሉ፡፡ በዚህም በሀገር ምጣኔ ሀብት ላይ ከፍተኛ ቀውስ ያስከትላል፡፡በተጨማሪም የቫይረሱ ስርጭት መስፋፋት ሆስፒታሎችና ለሎች የጠና ተቐማት በኤድስ ህሙማን እንዲጨናነቁ በማድረግ የጤና አግልግሎት ላይ ችግር ይፈጥራል፡፡ በዚህ ምክንያት በሚሊዮን የሚገመት ገንዘብ ኤች አይ ቪ ኤድስን በሚመለከት ለሚያዙ መርሃ ግብሮች እንደሚወጣ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህ ገንዘብ ለሌሎች የልማት ስራዎች ቢውል ኖሮ በህዝብ ህይወት ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሊያመጣ ይችል ነበር፡፡

1. እስካሁን ካነበባችሁት ምንባበ ምን ተረዳችሁ? ቀሪው የፅሁፍ ክፍል ስለምን የሚገልፅ ይመስላችኋል?

ኤች አይ ቪ ኤድስ ዜጎችን ለእንግልትና ለስቃይ ዳርጓል፡፡ በሺ የሚቆጠሩ ህፃናት ያለወላጅ ቀርተዋል፡፡ ይህም ለመንግስትና ለማህበረሰቡ አስቸጋሪ ፈተና ሆኗል፡፡ ወላጆቻቸው የሞቱባቸው ወጣት ሴቶች እራሳቸውን፣ ታናናሽ ወንድሞቻቸውንና እህቶቻቸውን ለመርዳት ሲሉ ለጎዳና ህይወትና ሴተኛ አዳሪነት ተዳርገዋል፡፡ ወንዶችም ቢሆኑ የጎዳና ተዳዳሪ ሆነዋል፡፡ በኤች አይ ቪየተያዙ ሰዎችም በተለያዩ በሽታዎች ስለሚጠቁና ቶሎም ስለማይድኑ ከስራ ይቀራሉ፡፡ በስራ ላይ ያላቸው ውጤታማነት ከዕለት ወደ ዕለት እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ይህ ደግሞ በግለሰብ ህይወት ላይ አሉታዊ የሆነ ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ተፅዕኖ ያስከትላል፡፡

ኤች አይ ቪ ኤድስ ያለባቸው ሰዎች ከጤናቸው መታወክ በተጨማሪ የሚደርስባቸው የስነ- ልቦና ጫና ቀላል አይደለም፡፡ ዛሬም ቢሆን በበሽታው የተያዙ ሰዎችን የማግለሉ ችግር ሙሉ በሙሉ ያልተቀረፈ በመሆኑ ህሙማን ቫይረሱ በደማቸው መኖሩ ከተረጋገጠ ማህበራዊ ግንኙነታቸው እንደወትሮው ላይቀጥል ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት የኤድስ ህሙማን የስነ-ልቦና ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ በተለይም በገጠር የሚኖሩ ሰዎች በሌላ በሽታ ለተያዙ ሰዎች የሚደረገው ድጋፍና ክትትል አይነት ለኤድስ ህሙማንም ስለማይደረግ ለኤች አይ ቪ ኤድስ ታማሚዎች ችግሩ እጥፍ ድርብ ነው፡፡ ይህ በራሱ በሽታውን ሊያባብሰው ይችላል፡፡

በአጠቃላይኤች አይ ቪ ኤድስ በሀገር በማህበረሰብና በግለሰብ ዘንድ ከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ያስከትላል፡፡ ስለዚህ በበሽታው ከመያዝ በፊት እራስን መጠበቅ፣ ከተያዙም በኋላ ወደሌሎች እንዳይተላለፍ የድርሻን ለመወጣት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

(ስ.ት.ዝ.ጥ.ም.ኢ፡፡ 1995 የኤች አይ ቪ ኤድስ ት/ት ገፅ 29-31 ለስድስተኛ ክፍል በሚመጥን መልኩ ተሻሽሎ የተወሰደ)

አንብቦ መረዳት

ለ. ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ስጡ፡፡

ሀ. መታወክ ሐ. መስፋፋት ሠ.እንግልት ሰ. ጫና

ለ. መሰልጠን መ. ቀውስ ረ. ደጋፊ ቀ. ስነ ልቦና

መልመጃ ፵፪

ሐ. በሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት በፍቺ የሚተካቸውን ቃላትና ሀረጋት እያስገባችሁ ፃፉ፡፡

ምሳለ ፡- የእንክብካበ ጉድለት በሽታን *ሊያባብስ* ይችላል፡፡ እንዲከፋ

ሀ. የህሙማን <u>መጠን</u> በየዓመቱ እየጨመረ ነው፡፡

ለ. ኢትዮጵያ ኤች አይ ቪ ኤድስ በፍጥነት <u>ከሚተላለፍባቸው</u> ሀገራት አንዷ ናት፡፡

ሐ. በቫይረሱ <u>ተጠቂ</u> ከሆኑ ሰዎች ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ለበሽታ ያጋልጣል፡፡

መ. በርካታ ወጣቶች የአደንዛዥ <u>ዕጽ</u> ከተጠቀሙ እራሳቸውን መቆጣጠር

ያቅታቸዋል፡፡

ሠ. የጤና <u>ተቋማት</u>ለበሽታው ተጠቂዎች ተገቢውን እገዛ ማድረግ

አለባቸው፡፡

ረ. ቫይረሱ <u>በአይን የማይታይ</u> ተህዋስ ነው፡፡

**መ.ኤች አይቪ ኤድስ የሚተላለፍባቸውንና የማይተላለፍባቸውን መንገዶች በቡድን በመወያየት ቀጥሎ በተሰጠው ሰንጠረዥ ወስጥ ፃፉ፡፡**

| ተ/ቁ | የሚተላለፍባቸው መንገዶች | የማይተላለፍባቸው መንገዶች |
|---|---|---|
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |

**ሠ.ቀጥሎ የቀረበዉን ግጥም አንብባችሁ ከስሩ ያሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡**

በመልካም አመለካከት

በእዉቀት በክህሎት

በትምህርት በልጽጎ

ሁለንተናዉ አድጎ

ስብእናዉ የተሟላ

አስተሳሰቡ የሰላ

እንድትሆን ጠንክር

ልጄ በርታ ተማር

ከበቀለ ሙዳ (ዲመትኮ)

1. ስብእና ምንድን ነዉ?
2. ስብእና እንዴት ያድጋል?
3. በርትቶ የተማረ ምን ይሆናል?
4. ‹ሁለንተና› እንዴት ይገለጻል?
5. የግጥሙ ቁልፍ መልእክት ምንድነዉ?
6. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት?
7. ስንኞቹ በሀረግ የተከፋፈሉ ናቸዉ? ለምን?

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### የቃላት ተቃራኒ ፍቺ

መልመጃ፡- 41

ፃ፡-በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጎች በ‹‹ለ›› ስር ከቀረቡት ውስጥ ተቃራኒ የሚሆኑትን በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ጣፋጭ | ሀ. መሞቅ |
| 2. ጠቃሚ | ለ. አዝናኝ |
| 3. መበርታት | ሐ. መንቃት |
| 4. መደባለቅ | መ. መለያየት |
| 5. መብረድ | ሠ. መራራ |
| 6. ማጥቃት | ረ. መዘንጋት |
| 7. መፍዘዝ | ሰ. ጎጂ |
| 8. ማባባስ | ሸ. መከላከል |
| 9. መጠንቀቅ | ቀ. ማሻሻል |
| 10. አሰቃቂ | በ. መድከም |

ተ. አስፈላጊ

ቸ. ድብርት

**፪:-ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ልዩ የሆነውን ቃል እየመረጣችሁ በደብተራችሁ ጻፉ።**

1. ሀ. አከናወነ ለ. ሰራ ሐ. ፈፀመ መ. ተወ
2. ሀ. ተደነቀ ለ. ተሸለመ ሐ. ተጠላ መ. ተመሰገነ
3. ሀ. አሯሯጥ ለ. አሰዳደር ሐ. አወቃቀር መ. አደራደር
4. ሀ. ዘገየ ለ. ፈጠነ ሐ. ቀለጠፈ መ. ሮጠ
5. ሀ. ወገን ለ. ዘመድ ሐ. ቤተሰብ መ. ጎረቤት
6. ሀ. ተበከለ ለ. ደፈረሰ ሐ. ጠራ መ. ቆሸሸ
7. ሀ. ማጥፋት ለ. ማልማት ሐ. ማበልጸግ መ. ማዳበር
8. ሀ. መበርገግ ለ. መሸበር ሐ. መደንበር መ. መዝናናት
9. ሀ. ጎጂ ለ. ጠቃሚ ሐ. አስፈላጊ መ.ወሳኝ
10. ሀ. መናደድ ለ. መደሰት ሐ. መበሳጨት መ.መቆጣት

**፫:-የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት ቀጥለው በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ አስገቡ።**

መንገድ ቆረጥ ቆረጥ መቋጫው ጥርግርግ በተረጋጋ መንፈስ

ምናቡ ጥቅልል ብርድ ብርድ ዘመም ጥንካሬ

ሀ. የዛሬ ጠዋቱ የከበደ እናት ቁጣ አየለን በ-----------እየታየው ስራ አላሰራ አለው።

ለ. ልትወድቅ የደረሰች ------------ያለች ጎጆ ውስጥ ሲያጠና ያድራል።

ሐ. ካፊያ ስለመታኝ ---------------አለኝ፡፡

መ. መድሐኒት ወስጄ ስለነበር ሆዴን-------------ያደርገኛል፡፡

ሠ. በየትኛውም ደረጃ የሚሰጥ ትምህርት---------------ፈተና ነው፡፡

ረ. የእሷ ችግር ከፊቴ ድቅን እያለ ስራዬን ------------መስራት አልቻልኩም፡፡

ሰ. ሰላምን በተለያየ --------------ማየት ይቻላል፡፡

ሸ. ማርን አዘውትሮ መብላት ለሰውነት ----------------ይጠቅማል፡፡

ቀ. ልጁ የቀረበለትን ምግብ ---------------አድርጎ በላ፡፡

በ. ዉሻው ስለበረደው ---------------ብሎ ተኝቷል፡፡

# ክፍል አራት ጽሕፈት

## የድርሰት ክፍሎች

### ማስታወሻ፡-

### የክርክር ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያ

ክርክር ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ጎራ ለይተው የሚያካሂዱት የሀሳብ ፍጭት ወይም ሙግት ነው፡፡እንደዚህ አይነት የሀሳብ ፍጭት በሚከናወንበት ጊዜ አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን የራሱን አመለካከት በሌሎች ላይ እንደፈለገው ከመጫን መቆጠብ ይኖርበታል፡፡

የክርክር አተገባበር መርሆዎች

ሀ. ግልፅነት ያልተለየው አቀራረብ

ለ. በመረጃ ላይ የተመሰረተ አቀራረብ

ሐ. ስሜታዊነትን ማስወገድ

መ. እርግጠኛ ሆኖ ማቅረብ

ሀ. የክርክር ዝግጅት

- የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳይ መምረጥ
- ርዕሱን በሚመለከት ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች መረጃ መሰብሰብ
- ከተሰበሰበው መረጃ ጠቃሚ የሆኑትን ብቻ መምረጥ
- ለአድማጮች ክርክሩን ከማቅረብ በፊት በቂ ልምምድ ማድረግ
- ለክርክር ከመቅረብ በፊት መልካም ስነ ምግባርተጎናጽፎ መገኘት

ለ. የክርክር አአቀራረብ

- ራስንና የመከራከሪያ ርዕሰ ጉዳይን ለአድማጮች ማስተዋወቅ
- ፍሬ ሀሳቦችን በቅደም ተከተል ማቅረብ
- ክርክሩን ረጋ ባለ መንፈስ ማቅረብ
- ተቃራኒ ቡድን የሚያነሳውን ሀሳብ በማስታወሻ በመያዝ በመረጃ አስደግፎ ሀሳቡን በሀሳብ መርታት
- ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ አለማድረግ
- ክርክርን ከአድማጮች ችሎታ ጋር መጥኖ ማቅረብ
- ለክርክር  የተመደበውን ጊዜ ማክበር
- የክርክሩ ሂደት ከርዕሰ ጉዳዩ እንዳይወጣ መጠንቀቅ
- የዳኞችን ውሳኔ በፀጋ መቀበል
- ክርክር ሲጠናቀቅ ታዳሚዎችን ማመስገን፡፡

ምንጭ (ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ፣1999-438)

**መልመጃ፡- 42**

**፩፡- ከዚህ በታች ከቀረቡት  ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን መርጣችሁ የክርክር መመሪያን ተከትላችሁ በክፍል ውስጥ ክርክር አቅርቡ፡፡**

**ሀ. የሕዝብ ቁጥር መጨመር ከሃገር እድገት ጋር በተያያዘ ጎጂ ነው ወይስ ጠቃሚ**

**ለ. የኮሮና ቫይረስን መከላለል ይቻላል ወይስ አይቻልም፡፡**

**ሐ. ለአንድ ሀገር እድገት መሰረቱ እርሻ ወይስ ኢንዱስትሪ፡፡**

**፪፡-በምሳሌ የቀረበውን ጽሁፍ አንብባችሁ ከስር ከቀረቡት ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ መግቢያ፣ሀተታና መደምደሚ ያለው ጽሑፍ አዘጋጅታችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡**

**ምሳሌ፡-**

**ደን የዛሬውና የነገው ትውልድ የጋራ ሀብት ነው፡፡ በሁሉም ህብረተሰብ ዘንድ ትኩረት ካልተሰጠው ወደፊት የማንወጣው ችግር ውስጥ ልንወድቅ እንችላለን፡፡ደኖቻችንን መጠበቅና መንከባከብ አለብን ስንል የሚሰጡንን ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ዛፎች አንዳንዶቹ አበባቸዉ ለዉበት ፍሬያቸው ለምግብነት፣ እንጨታቸው ለማገዶና ለቤት መስሪያ፣ ስሮቻቸው ለአፈር ጥበቃ፣ ደኑ ለዱር እንስሳትና እአዋፋት መጠለያ፣ ቅጠሎቻቸው ለመድሃኒትና ለእንስሳት መኖ ይውላል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲዘንብና የአካባቢውን የአየር ንብረት  እንዲጠበቅ  ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡ የምንተነፍሰውንም ንፁህ አየር ይለግሱናል፡፡**

በአጠቃላይ በተፈጥሮም ሆነ በሰው ሰራሽ መንገድ የበቀሉ ዛፎችን በአግባቡ በመንከባከብና በመጠበቅ ከሚሰጡን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች በተጨማሪ የተፈጥሮ ስነ ምህዳር ሚዛንም እንዲጠበቅ ማድረግ ይገባል።

ሀ. ፍትህ

መ. የትራፊክ አደጋ

ለ. ያየር ንብረት

ሠ.የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ

ሐ. መቻቻል

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ሳቢና ኢሳቢ ግስ

መልመጃ፡-43

፩፡-ከሚከተሉት ግሶች መካከል ሳቢ ግስ የሆኑትን ብቻ ለዩ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰቀለ | ሰጠ | መገበ | አዘነ |
| ሰበረ | ሄደ | አነበበ | ላከ |
| በጠሰ | ሸጠ | ቀደደ | ጨለመ |
| ሆነ | ለበሰ | | |

፪፡-ከሚከተሉት ግሶች መካከል ኢሳቢ ግስ የሆኑትን ብቻ ለዩ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፈነዳ | ዘለለ | ቀጠነ | ቀበጠ | ደመቀ |
| ነደደ | ደረሰ | አየለ | ወፈረ | አለቀሰ |
| ገዛ | ደከመ | ሳቀ | አኮረፈ | |

## ፫፡-የሚከተሉትን ምዕላዶች ነጣጥላችሁ በመፃፍ አንብቡ፡፡

ሀ. ገጠመኞቻቸውን	ረ. ወዳጅነታቸውን

ለ. በስነምግባራቸው	ሰ.መስጊዱን

ሐ. ቤተክርስቲያናት	ሸ. ቅርንጫፎቻቸው

መ. ወራሾቻቸውን	ቀ. ልጆቻቸውን

ሠ. አላፊነቶቻቸውን	በ. በሚዛናዊነታቸው

## ፬፡-የሚከተሉትን ምዕላዶች አጣምራችሁ በመፃፍ አንብቡ፡፡

ሀ. ትምህርት-ቤት-ኦች-ን	ረ.ጓደኛ-ነት-ኣቸው- ም

ለ. በሬ-ዎች-ኣቸው-ን	ሰ. ከ-እንቅስቃሴ-ኣቸው

ሐ. መቆጣጠር-ኢያ-ዎች-ኡ-ን	ሸ. አገልግሎት-ኣቸው-ን

መ. አሳሳ-ብ-ኢ-ነት-ኡ-ን	ቀ.አስ-ተማር,ኢ-ነት-ኣቸው-ን

ሠ. እ-ሰራ-ብ-ኧት-ኣል-ኧሁ	በ.ማህበር-ኧ-ሰብ-አዊ-ነት-ኣችሁ-ን

## ማጠቃለያ

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ የድርሰት ክፍሎችን አይተናል፡፡ የድርሰት ክፍሎች የሚባሉት መግቢያ፣ ሐተታና መደምደሚያ መሆናቸው፣መግቢያ ለሐተታ ሀሳቡ እንደመንደርደሪያ ሆኖ የሚገባ፣ ሐተታ የጽሁፉ አጠቃላይ ሀሳብ በዝርዝር የሚቀርብበት ሲሆን መደምደሚያ ደግሞ ሐተታው ላይ የቀረበው ሀሳብ ጠቅለል ተደርጎ ባጭሩ የሚገለጽበት ክፍል መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የክርክር መመሪያ የዝግጅት እና አቀራረብ ጊዜ በማለት ለይተን መመሪያውን ተከትለን ክርክር አካሂደናል፡፡ ሳቢ(ተሻጋሪ) እና ኢሳቢ ( ኢተሻጋሪ) ግሶችን ለማየት ሞክረናል፡፡ ሳቢ ግስ ከተሳቢ ስም ጋር ሆኖ የሚዋቀርና ድርጊት ፈፃሚና ተቀባይ ያለው ሲሆን ኢሳቢ ግስ ግን ድርጊቱ በባለቤቱ ላይ የሚፈጸም መሆኑን ተምናል፡፡ ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይተንና አጣምረን በመጻፍ አንብበናል፡፡ ለቃላት ተቃራኒ ፍቺ ሰጥተናል፡፡ ዓረፍተ ነገሮችን የሚያሟሉ ቃላትን በማስገባት አስተካክለን ጽፈናል፡፡ ከተዘረዘሩ ቃላት ውስጥ በፍቺ ልዩ የሆነውን ለይተን አሳይተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የድርሰት ክፍሎችን ጠቅሳችሁ ለእያንዳንዱ ማብራሪያ ስጡ፡፡
2. የተሳቢና ኢተሳቢ ግስ ምንነት፣ አንድነትና ልዩነት ግለጹ፡፡
3. የቅድመና ድህረ ክርክር ተግባራት ዘርዝሩ፡፡
4. ሶስት ተሳቢና ሶስት ኢተሳቢ ግሶችን ጽፋችሁ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ባህላዊ ክንዋኔዎች

❖ ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ✓ መምህሩ የሚያነብላችሁን ምንባብ አዳምጣችሁ ትመልሳላችሁ
- ✓ የተስማማችሁበትን ሀሳብ ታቀርባላችሁ
- ✓ አጫጭር ምንባብ አንብባችሁ ወደ ሰንጠረዥ ትቀይራላችሁ
- ✓ በቃል የሚነበብላችሁን በትክክል ትጽፋላችሁ
- ✓ ከርዕሱ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ትጽፋላችሁ
- ✓ የስርዓተ ነጥቦችን አነባበብ ጠብቃችሁ ታነባላችሁ

# ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት



### ቅድመ ማዳመጥ

**መልመጃ:- 44**

**ሀ. በአካባቢያችሁ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች አሉ? ካሉ የምታውቁትን ተናገሩ?**

**ለ.ባህላዊ የዳኝነት ስርዓት እንዴት ይካሄዳል?**

**ሐ. ምስሉን ተመልክታችሁ የተረዳችሁትን ተናገሩ?**

## የማዳመጥ ሂደት

‹‹ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች›› በሚል ርዕስ የቀረበውን መረጃ ሰጪ ምንባብ መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን እየለያችሁ በጥሞና አዳምጡ፡፡

## አዳምጦ መናገር

**፩፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት በቃላችሁ መልሱ፡፡**

ሀ. በፍርድ ቤት የወንጀል ምርመራና በአውጫጭኝ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምን ይመስላችሁዋል

ለ. ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች እንደየማህበረሰቡ የተለያዩ ናቸው ሲባል ምን ማለት ነው?

ሐ. ሰዎች ጥፋት ፈጽመው በሽምግልና ቢዳኙ በህግ የሚፀና ይመስላችኋል?

መ. ሽምግልና ለመከወን በእድሜ የገፉ ሰዎች የሚመረጡት ለምንድን ነው?

ሠ. የዘመድ ዳኝነት፣ሽምግልና እና አፈርሳታ ሰላም እንዲሰፍን ጉልህ አስተዋፆ አላቸው ሲባል እንዴት ይገለፃል ?

**፫፡-ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ተመሳሳይ ፍቺ ፃፉ፡፡**

ሀ. ማስተናበር

ለ. አለመግባባቶች

ሐ. እርቅ

መ. ይረግባሉ

ሠ. ክረት

ረ. ሚዛናዊነት

ሰ. ተደማጭነት

ሸ. ፈንጠር ብለው

ቀ. አውጫጭኝ

፫፦በቡድን ሆናችሁ በትምህርት ቤታችሁ የሚፈጠሩ ችግሮችን እንዴት እንደሚፈቱ የስነዜጋና ስነ-ምግባር ክበብ ተጠሪዎችን በመጠየቅ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ በቃላችሁ አቅርቡ።

፬፦ተማሪዎች፤- መምህራችሁ የሚያነቡላችሁን ቅደም ተከተላቸውን ያልጠበቁ ቃላትና ሀረጋት አዳምጡና አስተካክላችሁ ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

## ክፍል ሁለት፦ ማንበብ

ድግስ



**ቅድመ ንባብ**

**የቀደመ እዉቀትን መቀስቀስ**

መልመጃ፦-45

፩፦የሚከተሉትን የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በቃላችሁ መልሱ።

ሀ. በቤታችሁ ድግስ የሚዘጋጀው በምን በምን አጋጣሚዎች ነው?

ለ. በአካባቢያችሁ ወይም በቤተሰባችሁ በድግስ ሰበብ ያጋጠመ ችግር ካለ ጥቀሱና የተወሰደውን የመፍትሄ ሀሳብ ተናገሩ።

ሐ. ድግስ ከመደገሳችን በፊት አስቀድመን ምን ምን ነገሮችን ታሳቢ ማድረግ ይኖርብናል?

**የንባብ ሂደት**

ድግስ በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በለሆሳስ እያነበባችሁ ግልፅ ያልሆኑ ቃላትና ሀረጋት ሲያጋጥማችሁ በማስታወሻ ጻፉ።

ድግስ በበዓላትና በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚደረግ ዝግጅት ነው። በሀገራችን በበዓላት ምክንያት ደግሶ ወዳጅ ዘመድን ሰብስቦ ማብላትና ማጠጣት ሲወርድ ሲወራረድ የመጣ ልማድ ነው። የክርስትና እምነት ተከታዮች በእንቁጣጣሽ፣ በገና፣ በፋሲካና በመሳሰሉት፣ የእስልምና እምነት ደግሞ በአረፋ፣በመውሊድና በሌሎች በዓላት ወቅት ቤታቸውን ለየት አድርገዉ ያስዉባሉ። ሰርግ፣ተዝካር፣ ሰደቃ መሰል ባህሎችም እንዲሁ ብዙዎችን ድል ያለ ድግስ ሲጠይቁ የቆዩ ናቸው። በሹመትና በምርቃት ጊዜም ብዙ ሰዎች ድግስ አዘጋጅተው ከመሰሎቻቸው ጋር መደሰት የተለመደ ነገር እያደረጉት ቆይተዋል።

እነዚህና ሌሎችም ድግሶች ከዓላማዎቻቸው አንፃር ሲታዩ ሊደገፉ የሚችሉ ናቸው። ምክንያቱም ህዝባችን አብሮ በመኖር፣በመብላትና በመጠጣት አልፎም በእንግዳ ተቀባይነቱ ከሌላው የሚለይበትን ልማድ ያሳያሉ። ከዚህ ባሻገር ግን ድግሶቻችን ከሚያስከትሉት ጫና አንፃር ሲገመገሙ የሚነቀፉበት ብዙ ገፅታዎች ይታይባቸዋል።

1. ተማሪዎች እስካሁን ካነበባችሁት አንቀጽ ምን ተረዳችሁ?

2. አቅምን ያላገናዘበ ድግስ መደገስ ምን ምን ችግሮችን ይፈጥራል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ድግስ የሚደግሰው የተረፈውና ሀብት ያለው ብቻ አይደለም። የሌለውም ተበድሮና ተለቅቶ ያደርገዋል። ከወር እስከ ወር ቆሎ፣ቂጣ፣ጎመን እየተበላ፣ በጠፋም ቀን እንዲያው እየተዋለና እየታደረ በተኖረበት ቤት ሁሉ በበዓላት ዋዜማ ብዙ ነገሮች ይታሰባሉ። እንጀራ፣ ዳቦ፣ ሽንኩርት፣ቅመማ ቅመም፣ቅቤ፣ዶሮ፣በግ፣ቅርጫ ስጋ ወዘተ. የግድ አስፈላጊ ነገሮች ሆነው ይገኛሉ። በሰርግና በሌሎች ባህላዊ አጋጣሚዎችም ጊዜ ብዙ ሰዎች ከአቅማቸው በላይ ሲያስቡና ሲያደርጉ ይታያሉ። ድርጊታቸው የሚያስከትለው ችግር ከእነርሱም ተሰውሮባቸው ሳይሆን በይሉኝታና ከማን አንሼ በሚል ስሜት ተነድተው ባልፈለጉት ጣጣ ውስጥ ይዘፈቃሉ። በቀላል ወጪ ከዳሩ ወይም ካገቡ የሚሰነዘርባቸውን ትችት እየፈሩና የተናቁ እየመሰላቸው ያላቸውን አሟጠው ይደግሳሉ። ጥሎሽና ቀለበቱ፣በቤት ውስጥ የሚዘጋጀው ምግብና መጠጡ፣የእቃ ውሰቱ፣ ሽርሽሩና ጓዙ ወዘተ.አግቢዎችና ዳሪዎች ተጨንቀው የሚያደርጓቸው፣ሌሎችም እያለሙ የሚባንኑባቸው ቀልብ የሚነሱ፣ ስጋ የሚጨርሱ ነገሮች ናቸው።

ይህ ለሁሉም አይቻልም፤ የሚቻልም ቢሆን ለውድድር ካልሆነ በስተቀር አስፈላጊነቱና ጠቃሚነቱ እምብዛም አይደለም። ካቅሙ በላይ የደገሰ ወገን በድግሱ ሳቢያ ከሚመጣው ችግር በቀላሉ ሊላቀቅ አይችልም። ከተረፈው በስተቀር አለው የሚባለው እራሱ የአለውን አሟጥጦ ስለሚደግስ እንደገና መቋቋም ያዳግተዋል። በዚህ ምክንያት ቀጣይ ኑሮውን በሚገባ መምራት አይችልም። ሳይኖረው ተበድሮ የደገሰ እዳውን መክፈል ስለማይችል ያልጠበቀው ጉዳት ይደርስበታል።ይህንን በመሰለ ምክንያት በእዳ ተይዘው ቤተሰቦቻቸውን ጥለው የጠፉ ጥቂት አይደሉም።

ድግስ በሰለጠነውም ዓለም ቢሆን ጭራሹንም የቀረ ነገር ባለመሆኑ አያስፈልግምና አይኑር ማለት አይቻልም፡፡ የማያስፈልገውና ሊኖርም የማይገባው ድግስ ሊያስከትል የሚችል ችግር ነው፡፡ ችግሩ እንዲቀር ችግሩን የሚያመጣ አደጋገስ መቅረት አለበት፡፡ በይሉኝታና ከማን አንሸ በሚል ስሜት ዉጠቱ ድካም፣ኪሳራና እዳ ከሆነው የድግስ ልማድና ባህል ለመላቀቅ ሁሉም በግሉና በጋራ ሊወስን ይገባል፡፡

(አማርኛ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል 1997፣55-56 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## አንብቦ መረዳት

**፩፡-በምንባቡ መሰረት ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

ሀ. ሰዎች በበዓላት ጊዜ ቤታቸውን ለየት ያደርጉታል ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ.ሰዎች ሳይተርፋቸው ተቸግረው የሚደግሱት በምን ምክንያት ይመስላችኋል?

ሐ. ከአቅም በላይ መደገስ የሚያስከትላቸው ችግሮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

መ.ችግሩ እንዲቀር ችግሩን የወለደው የድግስ ሥርዓት መቅረት አለበት የሚለው አገላለፅ ምን ማለት ነው፡፡

ሠ. የምንባቡዋና መልዕክት ምንድን ነው?

**፫፡-በ‹‹ሀ›› ስር ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት በፍች የሚስማሙትን ከ‹‹ለ›› ስር በመምረጥ አዛምዱ፡፡**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ድል ያለ | ሀ. ተገፋፍተው |
| 2. ሲወርድ ሲወራረድ | ለ. ይገባሉ |
| 3. ይዘፈቃሉ | ሐ. ችግር |

4. ጥሎሽ መ. የሞቀ

5. ተነድተው ሠ. የማጫ ስጦታ

6. ጣጣ ረ. ተያይዞ የመጣ

**፬:-በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. በአጠቃላይ ድግስ መደገስ የሚደገፍበት ምክንያት ምንድን ነው?
   ሀ. ምንም አይነት ጉዳትስለሌለው
   ለ. ማህበራዊ ግንኙነትን ስለሚያናጋ
   ሐ. ማህበራዊ ግንኙነትን ስለሚያሳድግ
   መ. ሽልማት ስለሚያስገኝ
2. አንዳንድ ሰዎች ያላቸውን አሟጠውና ተበድረው የሚደግሱት ለምንድን ነው?
   ሀ. የተናቁ ስለሚመስላቸው ለ. አስደሳች በመሆኑ
   ሐ. መልካም ባህል በመሆኑ መ. ትልቅ ትርፍ ስለሚያስገኝ
3. እንደምንባቡ አገላለጽ ሰው ቀጣይ ኑሮውን መምራት የሚያዳግተው ምን ሲሆን ነው?
   ሀ. ድግስ ሳይደግስ ሲቀር ለ. በአቅሙ ልክ ሲደግስ
   ሐ. በጣም ደስ ሲለው መ. ችግሩን መቋቋም ሲያቅተው
4. ድግስ አስፈላጊ የማይሆነው መቼ ነው?
   ሀ. በአቅም ልክ ሲደገስ ለ. ቤተሰብ ሲቀራረብበት
   ሐ. ከእዳ ነፃ ሲሆን መ. ከአቅም በላይ ለሆነ ወጪ ከዳረገ

5. ሰዎች ከአቅም በላይ መደገስ የሚያመጣው ጣጣ ተሰውሮባቸው ሳይሆን ከማን አንሽ በማለት ችግር ውስጥ ይገባሉ፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ-----------ነው፡፡

ሀ. ግልፅ ሆኖላቸው ለ. ተረድተውት

ሐ. ሳይረዱት ቀርተው መ. መረዳት ሳይፈልጉ

6. ‹‹ቀልብ የሚነሳ፣ ስጋ የሚጨርስ›› ሲባል ምን ማለት ነው?

ሀ. የሚያከሳ ለ. የሚያስደስት

ሐ. ማራኪ የሆኑ መ. በጣም የሚያስጨንቅ

7. እንደምንባቡ ሀሳብ ድግስ የሚነቀፈው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. ያለውን አሟጦ መደገሱ ለ. ማህበራዊ ግንኙነትን ስለሚቀንስ

ሐ. ከትርፍ መደገሱ መ. እንግዳ ተቀባይ አለማድረጉ

8. በድግስ ሰበብ ከሚመጣ ችግር መላቀቅ እንደማይቻል የሚገልፀው አንቀጽ

ሀ. አንቀጽ አንድ ለ. አንቀጽ ሁለት

ሐ. አንቀጽ አራት መ. አንቀጽ አምስት

፫፡- ካነበባችሁት ምንባብ ርዕስ ጋር የተያያዘ አጭር አንቀጽ ጽፋችሁ በክፍል ውስጥ አንብቡ፡፡

## ክፍል ሶስት ቃላት

### የቃላት መጥበቅና መላላት

መልመጃ፡- 46

፩፡-ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች በምሳሌው መሰረት ፍቻቸውን በደብተራችሁ በመፃፍ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ደሙ ፈላ፡- ተናደደ፣ተቆጣ

ልቡ ተነሳ፡- ለመሄድ ተቻኮለ

ሀ.ሆዱን ሰጠ　　　መ. ቃሉን ሰጠ

ለ.ሀሳቡን ጣለ　　　ሠ. ጆሮ ሰጠኝ

ሐ. ነብር ሆነ　　　ረ. መንታ ልብ

**፪፡-የሚከተሉትን ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚኖራቸውን ፍቺ በዓረፍተ ነገር ውስጥ አሳዩ፡፡**

**ምሳሌ**፡- መመገብ

የተመጣጠነ ምግብ መመገብ ለጤንነት አስፈላጊ ነው፡፡ ሲጠብቅ

ህፃናትን በሰዓቱ መመገብ ለእድገታቸው ወሳኝ ነው፡፡ ሲላላ

ሀ. ወተት　　　መ. ለጋ

ለ. መዳር　　　ሠ. ሳለ

ሐ. መማር　　　ረ. አያት

**፫፡-የሚከተሉትን ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚኖራቸውን አውዳዊ ፍች አሳዩ፡፡**

ሀ. ማቋረጥ　　　ሐ. ቅርብ　　　ሠ. መቋቋም

ለ. ከፍተኛ　　　መ. መቀላቀል　　　ረ. መጨመር

# ክፍል አራት ጽሕፈት

## የሥርዐተ ነጥብ ምንነት

**መልመጃ፡- 47**

**፩፦ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀጽ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ ጠብቃችሁ አንብቡ፡፡**

ዘነበ ፈረሱን ጭኖ ለመሄድ በሚዘጋጅበት ጊዜ አንድ ሰው ካዳራሹ ወጥቶ ወደርሱ ቀረበና ‹‹ሰዓቱ ያንተ ነው፤በልዩ ተሸንፏል›› አለው፡፡ ይህን እንዳወቀ፣ ወዲያው የፀፀት ስሜት ተሰማው፡፡ በዚህ ወቅት ስለወንድሙ እንጅ ስለሰዓቱ አላሰበም ነበር፡፡ ‹‹ወደቤቱ ልሂድ? ወይስ ልቅር?›› እያለ ግራ ተጋብቶ ቆመ፡፡ የጨረታው ታዳሚዎች ካዳራሹ ወጡ፤በልዩም በመካከላቸው ነበር፡፡ ወንድሙ ለመሄድተዘጋጅቶ ባየው ጊዜ፣ሀሳቡን እንደለወጠ ተረዳና፣‹‹ስለሰዓቱ አመሰግንሃለሁ ዘነበ፣ከእንግዲህ በኋላ ወንድምህ አንተን እየተከተለ የሚሄድበትን ጊዜ ደግመህ አታየውም!›› በማለት፣ ጮሆ ተናገረ፡፡ ‹‹አንተም! ሁለተኛ እኔ ላንተ እሰራ የነበረውን ሁሉ ፈፅሞ ደግመህ አታየውም!›› ብሎ ሲመልስለት፣ ነብር ሆኖ ነበር፡፡ ወዲያውም ፈረሱ ላይ እመር ብሎ ወጥቶ እየጋለበ ሄደ፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ ሁለቱም ከአባታቸው ጋር አብረው ይኖሩበት የነበረውን ቤት እግራቸው እረግጦት አያውቅም፡፡

(በዓለም የታወቁ አጫጭር ልቦለዶች፣ትርጉም አምሳሉ አክሊሉ፣1981

**፪፡-ከላይ የቀረበውን አንቀፅ በድጋሚ አንብባችሁ ፅሁፉ የሚያስተላልፈውን መልዕክት በቡድን ተወያዩና አጭር ንግግር አድርጉ።**

**፫፡-ከዚህ በታች የቀረበውን አንቀፅ በትክልል በማንበብ ተገቢውን ስርዓተ ነጥብ በባዶ ቦታው ውስጥ አስገብታቸሁ ፃፉ።**

በጣሊያን ወረራ ዘመን ለሀገራቸው ነፃነት ከተዋደቁት በርካታ ወጣቶች ውስጥ አንዱ ዘርጋ ናጂ ነበር-----1---- ዘርጋ ናጂ ቁመቱ ረጅም ----2---አጥንቶቹ ሰፋፊ ------3-----መልኩ ቀይ-----4-----ፀጉሩ ከልክ በላይ አድጎ በሶስትዮሽ የተሸረበ ነበር----5-----ያፀጉሩ በጀርባውና በትከሻው ላይ ተንዠርግጎ ወርዶ ሲታይ ልዩ ግርማ ያጎናፅፈዋል------6-----ዘርጋ ጢም አልባ ሲሆን ጠቅላላ ገፅታው የሰው አይን የሚማርክ ሽበላ ----7-----ቆንጆ-----7----ነበር-------8------ዘርጋ አራት አመታት ያህል በዋሻና በጫካ ውስጥ ሲኖር ሹሩባው በወገቡ ከታጠቀው የቆዳ ዝናር በታች ወርዶ ይታይ ነበር-----9----በጎታ ገበያም ሆነ በሌሎች ስፍራዎች አጋጥሟት ያየችው ሴት ሁሉ------10----አይኔ ይፍሰስልህ-----10----ሳትል አታልፍም ነበር።

(አለም እሸቱ፣አለማዩ ነሪን በመጥቀስ፣1999-24)

**፬፡-በ‹‹ሀ›› ስር የቀረቡትን የስርዓተ ነጥብ አይነቶች በ‹‹ለ›› ስር ከተዘረዘተሩት የስርዓተ ነጥብ አገልግሎት ጋር የሚስማሙትን በመምረጥ አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ትምህርተ ጥቅስ | ሀ. ተቆርጦ የቀረ ሀሳብ መኖሩን ለማመልከት |
| 2. ነጠላ ሰረዝ | ለ.እራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ሀሳቦችን ለመለየት |
| 3. ድርብ ሰረዝ | ሐ. ከሌላ ሰው የተወሰደ ሃሳብ መኖሩን ለማመልከት |
| 4. ትምህርተ ስላቅ | መ.ሀይለኛ ስሜቶችን ለመግለፅ ያገለግላል |
| 5. ቃል አጋኖ | ሠ. ተከታታይነት ያላቸውን ሀሳቦች ለመለየ |
| 6. ነጠብጣብ | ረ. ማሾፍን፣ ማሽማጠጥን፣ ለመግለፅ |

**፳፡-ከዚህ በታች ያለውን ምንባብ በትክክል ካነበባችሁ በኋላ ወደ ሰንጠረዥ ቀይራችሁ ፃፉ፡፡**

**የደን ስርጭት በኢትዮጵያ በስኩዌር ኪሎ ሜትር ከ1973-1990**

በሀገራችን ኢትዮጵያ ከ1973-1990 ዓ.ም ባሉት አመታት ውስጥ የደን ስርጭቱ እየቀነሰ እንደመጣ ማየት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ከ1973-1976ዓ.ም ጥቅጥቅ ደን 30243 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 2.64% በመቶኛ የነበረው ከ1986-1990ዓ.ም ወደ 2346 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና ወደ 0.2% ቀንሷል፡፡ በመጠኑ የተመናመነ ደን ደግሞ ከ1973-1976 ዓ.ም 14158 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 1.24% በመቶኛ የነበረው ከ1986-1990ዓ.ም ወደ 7466 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 0.65% በመቶኛ ቀንሷል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ የተመናመነ ደን ከ1973-1976 ዓ.ም 10009 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 0.87% በመቶኛ የነበረው ከ1986-1990 ዓ.ም ባለው ጊዜ 45055 ስኩየር ኪሎ ሜትር ስፋትና 3.93% በመቶኛ ማደግ ችሏል፡፡ ከዚህ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ጥቅጥቅ ደንና በመጠኑ የተመናመነ ደን ቁጥሩ እየቀነሰ የመጣ ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ የተመናመነው ደን እየተሻሻለ የመጣ መሆኑ ነው፡፡(የብዝሃ ህይወት ሀብት በኢትዮጵያ 1998

**፯፦ከዚህ በታች በምሳሌነት የቀረበውን የማመልከቻ ደብዳቤ መሰረት በማድረግ የተማሪ ስነ ምግባር ችግር መኖሩን የሚገልፅ ማመልከቻ ደብዳቤ ለትምህርት ቤታችሁ አስተዳደር በመፃፍ በክፍል ውስጥ አቅርቡ፡፡**

**ምሳሌ፡-** **ቀን 12/02/2014ዓ.ም**

**ለዲላ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት**

**ዲላ**

**ጉዳዩ፡-ውጤት እንዲስተካከልልኝ ስለመጠየቅ ይመለከታል፡፡**

**ከላይ በእርዕሱ ለመግለፅ እንደተሞከረው እኔ ተማሪ ዳንቾ አያኖ የዲላ 1ኛ ደረጃ የ6ኛ ክፍል ተማሪ መሆኔ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም የ1ኛው ወሰነ ትምህርት አጠቃላይ ውጤት ድምር ስለተሳሳተብኝ ሁለተኛ ደረጃ መውጣት ስችል አምስተኛ ስለወጣሁ ትምህርት ቤቱ ትክክለኛ ውጤቴን አይቶ እንዲያስተካክልልኝ ስል በትህትና አመለክታለሁ፡፡**

**ከሰላምታ ጋር**

**ፊርማ--------**

**ዳንቾ አያኖ**

# ክፍል አምስት ሰዋስው

## የሃላፊ ጊዜ

**መልመጃ፡- 48**

**፩፡-ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በሃላፊ ጊዜ የተመሰረቱትን ለይታችሁ አውጡ፡፡**

ሀ. ልጁ የተዋሰውን መጽሐፍ ባለፈው ሳምንት መለሰ፡፡

ለ. ደራሲው ጥሩ የልቦለድ መጽሐፍ ለመፃፍ እያሰበ ነው፡፡

ሐ. ጎበዙ ተማሪ አንደኛ ለመውጣት ጥረት እያደረገ ነው፡፡

መ. ባለፈው ዓመት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ተቆፍሮ ነበር፡፡

ሠ. እንግዳው ትናንት ማታ ወደ ሀገሩ ተመለሰ፡፡

ረ. ጨዋታውን ፊት ለፊት ተቀምጬ ለመመልከት ወስኛለሁ፡፡

ሰ. ባለፈው ዓመት ውድድሩን ያሸነፈው የኔ ፈረስ ነበር፡፡

**፪፡-የሚከተሉትን ግሶች በመጠቀም በምሳሌው መሰረት በሀላፊ ጊዜ ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

ምሳሌ፡-ወሰደ

ኤርሚያስ ትናንት የገዛውን ጫማ ወሰደ፡፡

ሀ. ዘራ

ለ. ጠበቀ

ሐ. ወደደ

መ. ለበሰ

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስርአተ ነጥብ በጽሁፍ ውስጥ ሁለት ጠቀሜታ እንዳለው ተምረናል። ይኸውም የጽሁፍን ሀሳብ አሻሚ ባልሆነ መንገድ መረዳት እንዲቻል ማድረግና ጽሁፍ እንዴት መነበብ እንዳለበት ጥቆማ መስጠት እንደሆነ ተረድተናል። ደብዳቤ ሀሳብ ማስተላለፊያ አንዱ መንገድ መሆኑንና የመስሪያ ቤትና የግል ደብዳቤ ተብሎ እንደሚታወቅ፣ የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ከመስሪያ ቤት ወደመስሪያ ቤት፣ወይምወደግለሰብ ወይም ደግሞ ከግለሰብ ወደመስሪያ ቤት የሚፃፍ ሲሆን፣ የግል ደብዳቤ ደግሞ ከግለሰብ ወደግለሰብ የሚፃፍ መሆኑን አይተናል። ለፈሊጣዊ አነጋገር ፍቺ ሰጥተናል። ለቃላት ተመሳሳይ፣ አውዳዊ ፍቺ እና ሲጠብቅ ሲላላ የሚኖረውን ፍቺ በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ሰርተናል። በሀላፊ ጊዜ የቀረቡ ዓረፍተ ነገሮችን ለይተናል። የሀላፊ ጊዜ ተጠቅመን ዓረፍተ ነገር መስርተናል።

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. የመስሪያ ቤት ደብዳቤ ከግል ደብዳቤ የሚለይበትን ባህሪ ግለጹ።
2. ስርዓተ ነጥብ በጽሑፍ ውስጥ ያለውን አገልግሎት በምሳሌ አስደግፋችሁ ተናገሩ።
3. የሚከተሉትን ቃላት በማጥበቅና በማላላት አረፍተ ነገር ሰርታችሁ አሳዩ።

   ሀ. አረዱት ሐ. ዓባይ ሠ. አርማ

   ለ. ሰፊ መ. ከፋ ረ. ሰባ

4. ለሚከተሉት ፈሊጣዊ አነጋገሮች አረፍተ ነገር ስሩባቸው።

   ሀ. ራሱን ቀበረ ሐ. ሰባራ ስንጥር

   ለ. ልቡ ቀና መ. ቀን ወጣ

# ምዕራፍ አስር


## ሴቶችን ማብቃት

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች**

- ✓ የተሰማችሁን ምክንያታዊ ሆናችሁ ትገልፃላችሁ፡፡
- ✓ ተዘበራርቀዉ ያሉትን ቃላት አስተካክላችሁ ጥምር ቃል ትመሰርታላችሁ፡፡
- ✓ የሰው የህይወት ታሪክ ትጽፋላችሁ፡፡
- ✓ ስርዓተ ነጥቦች ያላቸውን አገልግሎት ተረድታችሁ ታነባላችሁ፡፡
- ✓ ርዕቱና ኢርቱዕ ግሶችን በዓረፍተ ነገሮች ዉስጥ ትለያላችሁ

# ክፍል አንድ ማዳመጥ

‹‹ህልመኛዋ ወጣት››



## ቅድመ ማዳመጥ

መልመጃ፡- 49

ሀ፡-ተማሪዎች መምህራችሁ ሲያነቡላችሁ ከማዳመጣችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልስ ስጡ።

1. ስዕሎቹን በመመልከት የተረዳችሁትን ግለፁ?
2. በርዕሱና በስዕሎቹ መካከል ምን አይነት ግንኙነት ያለ ይመስላችኋል?//
3. በአካባቢያችሁ ስኬታማ የሆኑ ሴቶችን ታውቃላችሁ? የስኬታቸውስ ሚስጥር ምን ይመስላችኋል?

## የማዳመጥ ሂደት

**2፡-መምህራችሁ‹‹ህልመኛዋ ወጣት››በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ ሲያነቡላችሁየድርጊት ቅደም ተከተሉን በጥሞና እያዳመጣችሁ ባዶ ቦታውን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡**

ሀ. የቤቱን ስራ በመስራት _______________ ትወጣለች፡፡

ለ. ወርቅነሽ _____ ቤተሰቦቿን ከማገገልገል ይልቅ ለብቻዋ ማሰብ ጀመረች፡፡

ሐ. ‹‹የት ሄድሽ ?›› ሲሏት አባቷ ________ብላ ወደአክስቴ መሄድ እፈልጋለሁ አለቻቸው፡፡

መ. ዕድሜዋ __________ ስለነበር በክፍል ውስጥ ትልቋ እሷ ነበረች፡፡

ሠ. የተለያየ __________ ቢያጋጥማትም ተቋቁማ ውጤታማ መሆን ችላለች፡፡

ረ. መንግስትንና ባለሀብቶችን ____________ ትምህርት ቤት አስገነባች፡፡

**፫፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሰረት ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያይታችሁ በቃል መልስ ስጡ፡፡**

ሀ.ገፀ ባህሪያዋ ያጋጠማትን መሰናክሎች ተቋቁማ ማለፍ የቻለችው እንዴት ነበር?

ለ. ወርቅነሽ ወደ አዲስ አበባ ባትመጣ ኖሮ ምን አይነት ህይወት የሚኖራት ይመስላችኋል?

ሐ. ‹‹የዚሁ እጣ ፋንታ ተቋዳሽ ነበረች›› የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል?

መ. የወርቅነሽ ወንድሞች ቢወዷትም ስራ ሊያግዟት ያልቻሉት ለምን ነበር?

ሠ. ተማሪዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ ታሪክ በድርጊት ቅደም ተከትል ተናገሩ፡፡

4፡-ተማሪዎች ከላይ ካዳመጣችሁት ምንባብ ያገኛችሁትን ቁም ነገር ተወያዩና በክፍል ውስጥ በየተራ ንግግር አድርጉ።

# ክፍል ሁለት፡- ማንበብ

## ጀግኒት ትችላለች



ሎሬት የትነበርሽ ንጉሴ



ዶ/ር እሌኒ ገብረ መድህን



ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ



ፓይለት አምሳሌ ጓሉ

## ቅድመ ንባብ

**መልመጃ፡- 50**

**፩፡- ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡**

1. ከላይ በስዕሉ የቀረቡት ሴቶች ታዋቂ የሆኑበትን ምክንያት ገምቱ፡፡
2. በሀገራችን ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ሴቶች ቁጥር አናሳ መሆን ምክንያት ምን ይመስላችኋል?

**2፡-የሚከተሉትን ቃላት በመነጠልና በማጣመር አንብቡ፡፡**

| ነጣጥሎ ማንበብ | አጣምሮ ማንበብ |
|---|---|
| የ -ተ-ፈራረመ - አቸ-ኣቸው - ን | የተፈራረመቻቸውን |
| የ- አ - ፀደቀ - አች-ኣ ቸው - ን | ያፀደቀቻቸውን |
| የ - ማይደርሱ - በት | የማይደርሱበት |
| ባለ - ሙያ - ዎች - ን | ባለሙያዎችን |

## የንባብ ሂደት

**‹‹ጀግኒት ትችላለች ›› በሚል ርዕስ የቀረበውን መረጃ ሰጪ ምንባብ ዋና እና ዝርዝር ሀሳቦቹን እየለያችሁ ድምጽ ሳታሰሙአንብቡ፡፡**

በአንድ ሀገር የስርዓተ ፆታ እኩልነት እዲሰፍን፣ተገቢው የስርዓተ ፆታ ተግባቦትና መተሳሰብ እንዲኖር፣የሴቶች መብት እንዲከበር፣ እኩል ተሳታፊነትና ተጠቃሚነታቸው በአግባቡ እንዲረጋገጥ በትምህርት መደገፍ አለበት፡፡ አለበለዚያ አድሏዊ የስርዓተ ፆታ አመለካከትና ማህበራዊ እሴቶች፣ደንቦችና እምነቶች የሴቶችን የመማር መብት እውንነት ያደናቅፋሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ደረጃዎች የሚማሩ ሴቶች ቁጥር አናሳ ይሆናል፡፡ቤተሰብ የአንድ ማህበራዊ ትስስር የሚጀመርበት መነሻ ተቋም እንዲሆን የሚጠበቅ

ቢሆንም አድሏዊ ስርዓተ ፆታ ባለበት ማህበረሰብ የመብት ረገጣ የሚጀመርበትና የሚበረታታበት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ በዚህም ወላጆች ወንዶች ልጆቻቸውን ኀበዝ ሴቶቹን ደግሞ ሰነፍ አድረገው ሊቆጥሩ ይችላሉ፡፡ ወንዶችን በመደገፍ፣በማበረታታት በአንፃሩ ደግሞ ለሴቶች ድጋፍ እና ማበረታታት የማይደረግ ከሆነ የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ማስፈን አይቻልም፡፡ ይህ ደግሞ ሴቶችን ለማብቃት በሚሰራው ስራ እንቅፋት ይሆናል፡፡ በቤት ውስጥም የእኩልነት መብታቸው ተነፍጎ እንደወንዶች ታውቃላችሁ፣ ትችላላችሁ፣ እየተባሉ የማያድጉ ከሆነ በትምህርት አቀባበላቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅዕኖ ያሳድርባቸዋል፡፡በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ይቀንሳል፡፡ በራስ መተማመናቸውም ይጎዳል፡፡ እነዚህና መሰል ስርዓተ ፆታዊ አድሎዎች የሴት ተማሪዎችን ውጤታማነት በእጅጉ ይፈታተናሉ፡፡

ትምህርት ቤቶችም ቢሆን በስርዓተ ፆታ ምክንያት ለሚፈጠረው የትምህርት ልዩነት ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ወንድ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸው ነፃነት ሰፊ ነው፡፡ በብዙ ትምህርት ቤቶች መፀዳጃ ቤቶች፣የቤተሙከራ መቀመጫዎች፣ የስፖርት ሜዳዎች፣ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች የተመቹ ናቸው፡፡

የመማሪያ መጽሐፍቱም በሴቶች ትምህርት ላይ ያላቸው አሉታዊ ተፅዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ በተለያዩ መፅሀፍት ውስጥ ያሉትን ምሳሌዎች ብንመለከት እንኳን ወንዶችን ዶክተር፣ኢንጅነር፣ ፓይለት፣ተመራማሪ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ ስዕሎቹም እንዲሁ ወንዶቹን ሲዝናኑ ሲጫወቱና ሲመራመሩ ያሳያሉ፡፡ ሴቶቹን ግን በቤት ውስጥ ተግባራት ተሰማርተው ቤት ሲጠርጉ፣ልብስ ሲያጥቡ፣ምግብ ሲያዘጋጁና ዝቅተኛ በተባሉ ስራዎች ላይ ሲሳተፉ ያሳያሉ፡፡‹‹ ወንድ ወደችሎት ሴት ወደማጀት›› የሚለውን ብሂል አንቅሮ በመትፋት ሴቶቸን ማብቃት እንደሚቻል ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ አይነት የሴቶችን ሚና አሳንሶ ማቅረብና ማሳየት ሴቶች በትምህርት ልቀው ራሳቸውን አሻሽለው በከፍተኛ

ውሳኔ ሰጭ ቦታዎች ላይ የመሳተፍ ህልማቸውን ስለሚጎዳ ሁሉም ሰው ሊጠነቀቅ ይገባል፡፡

1. ተማሪዎች እስከአሁን ካነበባችሁት ታሪክ ምን ተገነዘባችሁ?
2. ከዚህ ቀጥሎ ያለው የምንባብ ክፍል ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

ስለሆነም የሴቶችን ድርብ ሀላፊነት ለማቃለልና የስራ ተነሳሽነታቸውን የበለጠ ለማጎልበት መማር የሚገባቸውን ሁሉ ለማስተማር ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡የባህሪ፣ ያስተሳሰብና የአሰራር ለውጥ ማምጣት የሚቻለው በትምህርት ነው፡፡ ሴቶች የመማር እድሉን ካገኙ የራሳቸውን ፍላጎት በራሳቸው የመወሰን፣ የሚፈልጉትን ስራ የመስራት በራሳቸው ተማምነው የመኖር ብቃት ይኖራቸዋል፡፡ በመማራቸው የእድገት እንቅፋት የሆኑት ኋላቀር አመለካከቶች ቀስ በቀስ ይወገዳሉ፡፡ ለሁሉም ፆታዎች ፍትሃዊ ትምህርት እንዲያገኙ ትምህርት ለሁሉም የሚለውን መርህ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለተግባራዊነቱም ሴት ልጆች ትምህርት ጀምረው እንዳያቋርጡ ትምህርት ቤቶችን ከመኖሪያ አካባቢ በቅርብ መገንባት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በከፍተኛ አመራር ላይ ያሉ ሴቶችን በአርአያነት ማቅረብ የሴቶችን አቅምና ተሳትፎ ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ ኢትዮጵያም ሴቶችን ለማብቃት የስርዓተ ፆታ እኩልነትን ለማስፈን፣አድሎአዊና ኢፍትሃዊ አሰራርን፣ ፆታን ማዕከል ያደረገ ጥቃትን ከመከላከል አንፃር የህግ ማዕቀፎችን በመጠኑም ቢሆን አዘጋጅታለች፡፡ ከታች እስከ ላይ መዋቅሮችን ዘርግታ ሴቶችን በተለያዩ የሀላፊነት ደረጃዎች ላይ እያሳተፈች ትገኛለች፡፡ተቋማትን መስርታ፣በጀት በጅታና ባለሙያዎችን አሰማርታ በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡ በተጨማሪም የተፈራረመቻቸውንና ያፀደቀቻቸውን ዓለም አቀፋዊ፣አህጉራዊና ክልላዊ ስምምነቶችን እንዲሁም በህገ መንግስቱ ያፀደቀቻቸውን ድንጋጌዎች በማክበርና በማስከበር ረገድ ጠንካራ ስራ በመስራት ሴቶችን ለማብቃት እየሰራች ትገኛለች፡፡ሴቶች እድሉን ካገኙ በየትኛውም ደረጃ

መብቃትና ማንኛውም የሰው ልጅ የደረሰበትን የማይደርሱበት ምንም አይነት ምክንያት የለም፡፡ ለዚህም ምስክሩ በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልልቅ ደረጃና ድንቅ ድንቅ ስራዎችን የሰሩ ሴቶችን ታሪክ ማየት ያስፈልጋል፡፡

### አንብቦ መረዳት

፫፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ ‹‹እውነት›› ትክክል ካልሆነ ደግሞ ‹‹ሐሰት›› በማለት ምክንያት እየሰጣችሁ በቃል መልሱ፡፡

ሀ. የስርዓተ ፆታ እኩልነት እንዲሰፍን በትምህርት መደገፍ አለበት፡፡

ለ. ማህበረሰቡ ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች  ክብር በመስጠቱ የሴቶችን እኩልነት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ሐ. የሴቶችን የመማር እድል ለማሳደግ ትምህርት ቤቶች በቅርብ እርቀት መገንባት አለባቸው፡፡

መ. ከፍተኛ ቦታ ላይ የደረሱ ሴቶችን በአርአያነት ማቅረብ ሌሎች ሴቶችን አያበረታታም፡፡

ሠ. በኢትዮጵያ የስፖርት ሜዳዎች ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች የተመቹ ናቸው፡፡

ረ. ኢትዮጵያ የሴቶችን መብት ለማስከበር አለማቀፋዊ ስምምነቶችን ፈርማለች፡፡

4፡- ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረትአውዳዊ ፍቻቸውን ጽፋችሁ አሳዩ፡፡

ምሳሌ፡- ተነፍጎ (አንቀፅ አንድ)  ተከልክሎ

ደንብ(አንቀፅ አንድ)  መተዳደሪያ ህግ

ሀ.  እንዲሰፍን (አንቀጽ አንድ)

ለ. ማዕቀፎች (አንቀጽ አምስት)

ሐ. ትስስር(አንቀጽ አንድ)

መ. ሚና (አንቀጽ ሶስት)

ሠ. አርአያ (አንቀጽ አራት)

ረ. ማኅልበት (አንቀጽ አራት)

ሰ. መዋቅር (አንቀፅ አምስት)

## ክፍል ሶስት፡- ቃላት

### ቃላትን በምዕላድ መከፋፈል

**መልመጃ፡- 51**

**፩፡-ለሚከተሉት ቃላት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡-ሀቀኛ- ቃል አባይ ማድነቅ - ማኮሰስ

ሀአድሏዊ

ለ. እውን

ሐ. መግባባት

መ. ድሎት

ሠ. ክብር

ረ. ማጀት

ሰ. አናሳ

**2፡-ቀጥለው የተዘበራረቁ ቃላት አስተካክላችሁ በማጣመር ጥምር ቃል መስርቱና ፍቺ ስጡ፡፡**

ምሳሌ፡-ስርዓት-ስነ፡- ስነ ስርዓት(ህግ፣ደንብ)

ወለድ-ልብ፡- ልብ ወለድ(ዝርው የስነ-ጽሑፍ ክፍል፣የፈጠራ ስራ)

ሀ. ጥበብ-ኪነ

ለ. ምግባር-ስነ

ሐ. ቃላት- መዝገበ

መ.ሰናይ- ምግባረ

ሠ.ገጠም-ኩታ

ረ. ትምህርት-ስርዓተ

ሰ. ድስት - ብረት

**፫፡-የተሰመረባቸውን ቃላትና ሀረጋት ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡**

1. ህፃኑ ልጅ የብር ፍልቃቂ ይመስላል፡፡

   ሀ. በጣም ደስ የሚል ለ. አስቀያሚ

   ሐ. በጣም የሚያስጠላ መ.ነጭ የሆነ

2. የብር አሎሎ የመሰለው አይኗ አላፊ አግዳሚውን ያንከራትታል፡፡

   ሀ. ሞጭሟጫ ለ. ትንንሽ

   ሐ. ትልልቅ መ. ጌጣጌጥ

3. አፍንጫው ስንደዶ የመሰለ ነው፡፡

   ሀ. ደፍጣጣ ለ. አስጠሊታ

   ሐ. ቀጥ ያለ መ. የተጣመመ

4. የወተት አረፋየመሰለው ጥርሷ ስትስቅ ላየው አፍ ያስከፍታል፡፡

   ሀ. ችምችም ያለ ጥርስ ለ. የበለዘ ጥርስ

   ሐ. ጉራማይሌ ጥርስ መ. በጣም ነጭ ጥርስ

5. የሌሊቱ ፅልመት ተገፎ ብርሃን ሲወጣ ሁሉም ሰው ከመኝታው ተስፋን ይዞ ይነሳል፡፡

ሀ. ጨለማው ተወግዶ ለ. ጨለማው ተተክቶ

ሐ. ብርሃን አስወግዶ መ. ምሽትን ቀይሮ

6. ሙዚቀኛው በራሱ ቅኝት የራሱን ቅላፄ በመፍጠር ሙዚቃ አወጣ፡፡

ሀ. ጩኸት ለ. እንጉርጉሮ

ሐ. ሙሾ መ. የዜማ አይነት

4፡-በምሳሌው መሰረት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላዱን በመለየት በሰንጠረዥ ውስጥ ጻፉ፡፡

| ተ/ቁ | ቃላት | ነፃ ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ ሀ | ልጆቻቸውን | ልጅ | - ኦች፣- ኣቸው፣- ን |
| ለ. | ሴትነት | ሴት | - ነት |
| 1. | ገበሬዎች | | |
| 2. | ባርኔጣቸው | | |
| 3. | ደብተሬ | | |
| 4. | ቤታቸው | | |
| 5. | ዘመዶቻቸውን | | |
| 6. | እርሳሶች | | |
| 7. | ቤተሰቦቻችሁን | | |

# ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

## የህይወት ታሪክ

### ማስታወሻ

#### የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያ

- የህይወት ታሪክ የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ ሲኖር አወንታዊ ወይም አሉታዊ ተግባሮችን ሊያከናውን ይችላል፡፡ መልካም ነገርን ለትውልድ ያበረከተ ሰው ስሙ ለዘላለም ሲወደስ፣ለሀገርና ለወገን ኩራት እንደሆነ ይኖራል፡፡‹‹መልካም ስም ከመቃብር በላይ ይውላል›› የሚባለው ለዚህ ነው፡፡ የህይወት ታሪክ አፃፃፍ በሁለት ይከፈላል፡፡ ይኸውም የራስ የህይወት ታሪክና የግለሰብ የህይወት ታሪክ በመባል ይታወቃል፡፡

#### የራስ የህይወት ታሪክ

- የራስ የህይወት ታሪክ የሚባለው አንድ ሰው በህይወት እያለ የራሱን የህይወት ታሪክ ራሱ ሲጽፈው ነው፡፡
- የራስየህይወት ታሪክ ለመፃፍ የሚያስብ ሰው ከስሜት ነፃ ሆኖ ሳይጨመር ሳይቀይስ መፃፍ እንዳለበት ማመን ይገባዋል፡፡ ከዚያም የሚከተሉትን መመሪያዎች በመከተል መፃፍ ይቻላል፡፡
    - የትውልድ ስፍራና የትውልድ ዘመን መግለፅ
    - ስለ አስተዳደግ ሁኔታ መግለፅ
    - የትምህርት ደረጃ መግለፅ
    - በህይወት ዘመን ያበረከቱትን ጉልህ አስተዋፅዖዎች በቅደም ተከተል መፃፍ
    - ታሪኩን በቅደም ተከተል ማደራጀት
    - ታሪኩን በቀላልና በግልፅ የቋንቋ አጠቃቀም ማቅረብ፡፡

#### የግለሰብ የህይወት ታሪክ

- የአንድ ሰው የህይወት ታሪክ በሌላ ጸሀፊ ሲጻፍ የግለሰብ የህይወት ታሪክ

ይባላል፡፡ የግለሰብ የህይወት ታሪክ ሲጻፍ ሰውየው በህይወት ዘመኑ እያለ ያበረከተውን አወንታዊም ሆነ አሉታዊ አስተዋፅዖ ሳንጨምር ሳንቀንስ መጻፍ አለበት፡፡

- የህይወት ታሪክ ልቦለድ ወይም የፈጠራ ስራ መሆን የለበትም፡፡ ይህ ማለት ግን ፀሀፊው እንጨት እንጨት ባለ የቋንቋ አጠቃቀም ታሪኩን እንደወረደ ያቅርበው ማለት አይደለም፡፡
- የግለሰብ የህይወት ታሪክ ሲጻፍ የሚከተሉትን መመሪያዎች መከተል አስፈላጊ ይሆናል፡፡
    - ታሪኩ ስለሚፃፍለት ግለሰብ የተፃፉ ፅሁፎች ካሉ በማንበብ አልያም ግለሰቡን የሚያውቁ ሰዎችን በማነጋገር መረጃ ማሰባሰብ
    - ግለሰቡ የተወለደበትን ቦታና የትውልድ ዘመን መግለፅ
    - ስለ አስተዳደጉ ሁኔታ በዝርዝር ማቅረብ
    - የግለሰቡን የትምህርት ደረጃ መግለፅ
    - ግለሰቡ ያበረከታቸውን አስተዋፅዖዎች መፃፍ
    - የግለሰቡን አጠቃላይ ታሪከ ቀላልና ግልፅ በሆነ የቋንቋ አጠቃቀምመግለፅ
    - ግለሰቡ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየ የሞተበትን ዘመን መፃፍ
    - ስለ ግለሰቡ ታሪክ መረጃ የሰጠን አካላት በማመስገን መግለፅ
    - ስለግለሰቡ የተነበበ መፅሀፍ ካለ በዋቢነት ማቅረብ፡፡

➢ **መልመጃ: 52**

**፩፦መምህራችሁ ደቂቃ ይያዙላችሁና ከዚህ በታች የቀረበውን የህይወት ታሪክጥንድ ጥንድ ሆናችሁ አንብቡ፡፡**

## ጳውሎስ ኞኞ

ጳውሎስ ኞኞ ቁልቢ አካባቢ ህዳር 11 ቀን 1926ዓ.ም ተወለደ፡፡ ትምህርቱን ከአራተኛ ክፍል ቢያቋርጥም ላዛሪስት ሚሽን አዳሪ ትምህርት ቤት ገብቶ ነበር፡፡ ዳሩ ግን እናቱ ገና የሁለት አመት ህፃን ሳለ ከአባቱ ጋር ተለያይተው ስለነበር በተዘዋወሩበት ቦታ ሁሉ ይዘውት እየሄዱ ነበር ያሳደጉት፡፡ ከእናቱ ጋር መሆን ኑሮን ለማሸነፍ የተጠቀመባቸው አያሌ የስራ አይነቶችና ስልቶች የጳውሎስን ብልህና ብሩህ አዕምሮ ያሳያሉ፡፡እንቁላል፣ፓስታ፣የሎሚ ጭማቂ(ራሱ እየጨመቀ)፣ጭራ፣የመላዕክትንና የአርበኞችን ስዕል እያዘጋጀ ይሸጥ ነበር፡፡

በወር ስምንት ብር እየተከፈለው በእርሻ ሚኒስቴር ውስጥ ስራ የጀመረው ጳውሎስ የኋላ ኋላ በጽሕፈት ሰራተኝነት ወደ ጤና ጥበቃ ተዛውሮ አዲስ አበባ ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ገባ፡፡ በዚሁ ስፍራ ላይ እያለ ለጋዜጣ አንዳንድ ጽሑፎችን መላክ ጀመረ፡፡ ቀስ በቀስ እጁን እያፍታታ ወደ ስነ-ፅሁፍ ሙያ ብቅ ሲል የጋዜጠኝነት ዓለም ጠራው፡፡ ያን ጊዜ ‹‹የኢትዮጵያ ድምፅ›› የምትባልና በሀገር ፍቅር ስር የምትተዳደር ሳምንታዊ ጋዜጣ ነበረች፡፡ ጳውሎስ ሰማንያ ብር የሚገኝበትን ስራ ትቶ በሀምሳ ብር ደመወዝ የድምፅ ጋዜጣ ሰራተኛ ሆነ፡፡ ችሎታውን የተመለከቱ ሀላፊዎችና ባለስልጣኖች እውቅ ጋዜጠኛ እንደሚወጣው ተነበዩለት፡፡

የብዕሩንም ድምፅ በድምፅ ጋዜጣ በኩል ማሰማት ጀመረ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተፈጥሮ በታደለው የማስተባበር፣ የመቀስቀና የማቀናጀት ጥበብ ጋዜጣዋን ለህዝብ በስፋት አስተዋወቀ፡፡ በዓመት አስር ሺህ ተገምቶ የነበረው የስርጭት

ቁጥርም በወር ወደ ሰላሳ ሺህ ደረሰ፡፡ ይህም አዲስ ዘመን ጋዜጣን እንዲወድቅ(ገበያው በእጅጉ እንዲቀንስ) በማድረጉ ጳውሎስ በመንግስት ባለስልጣኖች ተግሳፅ ደረሰበት፡፡

ጳውሎስ የተቸገረን መርዳት ቋሚ ተግባሩ ነበር፡፡ በዚህ መልኩ የፈፀመው ተግባር አያሌ ቢሆንም በተለይ በ1965ዓ.ም ከወሎ በረሀብ ተሰደው የመጡ ወገኖቻችንን አንድ ቦታ አሰባስቦ ‹‹የተራቡ ወንድሞቻችንን ፋሲካን እናስፈስክ! ›› የሚል ጥሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ አውጥቶ ተገቢውን እርዳታ ማድረጉ ይታወሳል፡፡

ጳውሎስ በጋዜጦች ላይ ከጽሑፍ አቅራቢነት እስከ አዘጋጅነት ለበርካታ ዓመታት ሰርቷል፡፡ከዚህ ውጭ የአራዳው ታደሰ፣ የጌታቸው ሚስቶች፣የኤዎቹ ገረዶች፣አስደናቂ ታሪኮች፣የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት፣ አፄ ምኒልክ ወዘተ. መጽሐፍትን ደርሶና አዘጋጅቶ ለህዝብ አቅርቧል፡፡ይህ በራሱ ከፍተኛ ትግልና ጥረት ካሰበው ግብ ለመድረስ የበቃ ህዝባዊና ተወዳጅ ጋዜጠኛ ግንቦት 29 ቀን 1984ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡

ምንጭ፡-ተግባራዊ የአማርኛ ትምህርት ማጠናከሪያ 1999፣88-89

## 2፡- ቀጣዮቹን ጥያቄዎች ባነበባችሁት መሰረት በጽሑፍ መልሱ፡፡

1. ከላይ ያነበባችሁትን የህይወት ታሪክ በድጋሚ ስርዓተ ነጥቦቹን ጠብቃችሁ ድምጻችሁን በማሰማት አንብቡ፡፡
2. ጳውሎስ ኞኞ በሚል ርዕስ የቀረበውን የህይወት ታሪክ ገምግሙና የጽሑፉን አወንታዊና አሉታዊ ጎኖች ለይታችሁ በማውጣት በክፍል ውስጥ ተወያዩ፡፡

## መልመጃ 53

የህይወት ታሪክ አፃፃፍ መመሪያን ተከትላችሁ የአንድ ግለሰብ የህይወት ታሪክ ፃፉና በክፍል ውስጥ አንብቡ።

## ክፍል አምስት፡- ሰዋስው

### ርቱዕና ኢርቱዕ

➢ **መልመጃ፡- 54**

፩፡-የሚከተሉትን ተቀላቅለው የቀረቡትን ቃላት ርቱዕ ወይም ኢርቱዕ በማት ለይታችሁ በሰንጠረዡ ውስጥ ፃፉ።

በላ ተደበደብ ሰበረ ተሰበረ ተለወጠ ተመታ
ተሰነጠቀ ተሰራ ሳለ ሸለመ ተበላ ተቀየረ

ጠጣ ተሰወረ ላጠ መታ ፃፈ ተወዳደረ

| ተ/ቁ | ርቱዕ | ኢርቱዕ |
|---|---|---|
| ምሳሌ | ላጠ | ተቀየረ |
| | ፈላ | ተለወጠ |
| 1 | | |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |
| 5 | | |
| 6 | | |
| 7 | | |
| 8 | | |

**2፡-የሚከተሉትን ቃላት በምሳሌው መሰረት ወደ ተገብሮ በመቀየር በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡**

**ምሳሌ፡- ፈጨ=ተፈጨ**

**ፈለጠ=ተፈለጠ**

**ሀ. ረሳ** **መ. መረቀ**

**ለ.ሰረቀ** **ሠ. መከረ**

**ሐ. ጋገረ** **ረ. ቀባ**

**፫፡- የሚከተሉትን ግሶች ገቢርና ተገብሮ በመጠቀም ዓረፍተ ነገር ስሩባቸው፡፡**

**ምሳሌ፡-ቀጠለ**

**ገቢር = አለሙ የተቋረጠውን የመብራት ገመድ ቀጠለ፡፡**

**ተገብሮ = ተቋርጦ የነበረው የመብራት ገመድ በአለሙ ተቀጠለ፡፡**

**ሀ. ባረከ** **ሐ. ቦጨቀ** **ሠ. ለወጠ**

**ለ. ቆለፈ** **መ. ፈለገ** **ረ. ነቀለ**

## ማጠቃለያ

ተማሪዎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በምንባቡ መሰረት ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ መስጠት የቻልን ሲሆን አውዳዊ ፍች ማለት ቃላት እንደ አገባባቸው የሚሰጡት ትርጉም ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ለቃላት ተቃራኒ እና ተመሳሳይ ፍችዎችን ለመስጠት ሞክረናል፡፡ቃላትን እርስ በእርሳቸው በማጣመር ድርብ ቃል መስርተናል፡፡ ድርብ ቃል ማለት የተለያየ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በማጣመር ቃላቱ በፊት ከሚሰጡ ፍቺ የተለየ ፍች እንዲሰጥ ማድረግ ነው፡፡

እንዲሁም ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይተን በመጻፍ አሳይተናል፡፡ በመጨረሻም የህይዎት ታሪክየራስና የግለሰብ ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል አይተናል፡፡የራስ ህይወት ታሪክ አንድ ሰው የራሱን የህይወት ታሪክ ሲጽፍ ሲሆን፣ የግለሰብ የህይወት ታሪክ ደግሞ የአንድ ሰው የህይወት ታሪክ በሌላ ጸሀፊ ሲጻፍ እንደሆነ ተረድተናል፡፡

## የክለሳ ጥያቄዎች

1. ቀጥለው ለቀረቡት ቃላት መዝገበቃዊ ፍች ስጡ፡፡

   ሀ. ሀራጅ — ሐ.ማጀት

   ለ. መሰሪ — መ.ማሞካሸት

2. የሚከተሉትን ቃላት በማጣመር ድርብ ቃል መስርቱ፡፡

   ሀ. ገጠም- ኩታ — ሐ. አደር-ላብ

   ለ. መንግስት-ቤተ — መ. አደር-አርብቶ

3. ከሚከተሉትን ቃላት ውስጥ ነፃና ጥገኛ ምእላዶችን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

   ሀ. ደስታችንን — ሐ.ተማሪዎቻችሁን

   ለ. ስልጣኑን — መ. መለኮታዊነቱን

4. በራስ እና በግለሰብ የህይዎት ታሪክ አጻጻፍ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ግለፁ፡፡

| የቃላት ፍች | |
|---|---|
| ቃል | ፍች |
| ሁለንተና | ሁለመና፣ጠቅላላ አካል፣መላ ሰውነት |
| ህቡዕ | ድብቅ፣ ሚስጥራዊ፣ ይፋ ያልሆነ |
| ህብር | የልዩ ልዩ ቀለማት ቅንብር፣ጠባይ፣ ባህሪ፣ ለዛ |
| ሙዳ | በልክ በልክ የተቆረጠ የስጋ ቁራጭ |
| ማህበር | ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ሰዎች የሚመሰርቱት ድርጅት |
| ማሳ | ተደጋግሞ የታረሰ፣ የታየመ መሬት |
| ማጀት | የምግብ ማብሰያ ክፍል፣ ጓዳ፣ ማድ ቤት |
| ምናብ | በስሜት ህዋሳት የማይደረስባቸውን ነገሮች በህሊና |
| | እንዲደረስባቸው የሚያድርግ ተፈጥሮአዊ ሀይል |
| ሞፈር | የእርሻ መሳሪያ፣የገበሬ እቃ፣ |
| ቀንበር | እርሻ ጊዜ በሁለቱ በሬዎች ትከሻ ላይ የሚቀመጥ በምራን |
| | የሚታሰር የእርሻ መሳሪያ ነው |
| ቀውስ | እብድ ፣ ወፈፌ፣ ንክ |
| ቆፈን | ብርድ፣ ቅዝቃዜ፣ ውርጭ |

| | |
|---|---|
| ተግዳሮት | መኮፈስ፣ ትዕቢት፣ ማናለብኝነት፣ |
| ትውፊት | የተወረሰ እምነት፣ ነባር የአኗኗር አባባል፣ ወግ፣ታሪክ፣ ባህል |
| አርአያ | አምሳል፣የመልክ ምሳሌ፣ አብነት |
| አሻራ | ጣትን ቀለም አስነክቶ በማንኛውም ነገር ላይ ሲጫኑት |
| | የሚተወውምልክት፣ የቡና ገለፈት፣ገለባ |
| አውጫጭኝ | ወንጀል የሰራ ሰው ህዝቡ ተሰብስቦ ማጋለጥ፣ መጠቆም |
| አጥቢያ | አካባቢ፣ ሰበካ፣ ቀበሌ፣ቀዬ፣ ንጋት፣ ማግስት |
| እሾህ | በልዩ ልዩ ዛፎች ላይ የሚገኝ የሚዋጋ አሜከላ፣ ተንኮለኛ፣ ክፉ |
| እንከን | ጥፋት፣ጉድለት፣ ህፀፅ፣ ነውር፣ ነቀፋ |
| እውን | ምናባዊና ህሊናዊ ብቻ የሆነውን በራሱ ህልውና ካለውና ነባራዊ ከሆነው ለመለየት የሚጠቅም |
| ወንፊት | ከአክርማ፣ ከሰንደዶ የሚሰራ ማንዘርዘሪያ፣ ወሬኛ |
| ዝርያ | የትውልድ ሀረጉ የሚታወቅ፣ በደም ግንኙነት የተሳሰረ ዝምድና |
| ደባ | ተንኮል፣ ሴራ፣ ተሸሽገ፣ተደበቀ |
| ጥበብ | ዘዴ፣ዕውቀት |
| ፅልመት | ጨለማ ፣ጥቁረት |

| ፈሊጣዊ አነጋገሮች | ፍቻቸው |
|---|---|
| ሀሳቡን ጣለ | ተረጋጋ |
| ሆዱን ሰጠ | ሚስጥሩን ገልጦ አወያየ |
| ልቡ ተነሳ | ለመሄድ ተቻኮለ |
| መንታ ልብ | ወላዋይ |
| ስመ ጥር | ታዋቂ |
| ቃሉን ሰጠ | መሰከረ |
| ነብር ሆነ | ተቆጣ |
| አድሮ ቃሪያ | የማይሻሻል |
| የቀለም ቀንድ | ምሁር |
| የውሃ ሽታ | ደብዛው የጠፋ |
| ደሙ ፈላ | ተናደደ |
| ድርብ ድል | በስኬት ላይ ስኬት |
| ጆሮ ሰጠ | አዳመጠ |
| ግብረ ገብ | መልካም ስነ-ምግባር |

## ዋቢ መፅሀፍት

ሀዲስ አለማየሁ፡፡ (1996 ዓ.ም)፡፡ ፍቅር እስከ መቃብር፡፡ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሔኖክ ያሬድ፡፡ (2005 ዓ.ም)፡፡አበበ ቢቂላ የተወለደው መቼ ነው፡፡ ሪፖርተር ጋዜጣ

መዘመር ግርማ (2011 ዓ.ም)፡፡ ሁቱትሲ የወጣቷ ልብ አንጠልጣይ ትውስታዎች የትርጉም ስራ፡፡

ማርታ እሸቱና ነፃነት ጌትነት፡፡ (2004 ዓ.ም) ፡፡ የአማርኛ ቋንቋ የተማሪው መማሪያ መፅሀፍ 10ኛ ክፍል፡፡አዲስ አበባ፣በት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ሜሪ ጄን ግሌይና ሳባ ገ/መድህን ፡፡ (2007 ዓ.ም)፡፡ ተምሳሌት፡፡ ፅሀይ የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራዊ ቅንጅት አሳታሚ ድርጅት፡፡

ሰለሞን ሐለፎም፡፡(1997 ዓ.ም) ፡፡ የድርሰት አፃፃፍ፡፡አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድጅት፡፡

ሳሙኤል አየለና ታሪኳ መላኩ፡፡ (1997 ዓ.ም)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሳባ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡(2005 ዓ.ም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስትቲትዩት፡፡(1995 ዓ.ም)፡፡ የኤች አይ ቪ ኤድስ ትምህርት፡፡አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሪፖርተር ጋዜጣ፡፡ (2009 ዓ.ም)፡፡ ኪንና ባህል፣ታትሞ ከወጣው ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

ባየ ይማም፡፡ (2010 ዓ.ም)፡፡ አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አልፋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ሙሉጌታ ይመር፡፡(2007 ዓ.ም)፡፡ ሁለገብ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ አጋዥ መፅሀፍ፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

ትምህርት ሚኒስተር፣ሴቭ ዘ ችልድረን እና የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ በጋራ ትብብር፡፡ (2008 ዓ.ም)፡፡ ለምግብነት የሚውሉ የጓሮ አትክልቶች በሚል የተዘጋጀ አጋዥ መፅሀፍ፡፡

አለም እሸቱ፡፡(1999 ዓ.ም)፡፡ ተግባራዊ የአማርኛ ትምህርት ማጠናከሪያ ከ7-10ኛ ክፍል፡፡ ብራና ማተሚያ ድርጅት፡፡

አለቃ ደስታ ተ/ክለወልድ፡፡(1962ዓ.ም)፡፡ አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፣በአርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አምሳሉ አክሊሉ፡፡ (1981 ዓ.ም)፡፡ በአለም የታወቁ አጫጭር ልቦለዶች፡፡ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፤

ዘሪሁን አስፋው ፡፡(2004 ዓ.ም)፡፡ የስነ-ፅሁፍ መሰረታውያን፡፡ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

የአብክመ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ (2001 ዓ.ም)፡፡ የባህል ልማት መሰናክሎች ቅኝት፡፡ ባህርዳር፣(ያልታተመ)፡፡

የአዲስ አበባ አስተዳደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡(2007 ዓ.ም) ፡፡ባህል ቱሪዝም፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ።(2007ዓ.ም)። የአማርኛ መማሪያ መፅሀፍ 7ኛ ክፍል።አዲስ አበባ፣ቦሌ ማተሚያ ድርጅት።

የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ። (2012 ዓ.ም)። የጥላቻ ንግርርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ።ሀያ ስድተኛ አመት ቁጥር 26 ገፅ 12339። አዲስ አበባ ብርሃንና ሰላም መተሚያ ድርጅት።

ደረጀ ገብሬ።(1996 ዓ.ም) ።ተግባራዊ የፅህፈት መማሪያ።አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያድርጅት።

ደበበ ኃ/ጊዮርጊስ።(2008 ዓ.ም)። ኮሜት አጋዥ መፅሃፍ ከ9-10ኛ ክፍል። አዲስ አበባ፣ አስቴት ነጋ አሳታሚ ድርጅት።

ጌታሁን አማረ።(2009 ዓ.ም)። ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ። አዲስ አበባ፣ አልፋ አሳታሚ ድርጅት።

ፋንታሁን እንግዳ። (2000 ዓ.ም) ። ታሪካዊ መዝገበ ሰብ ከጥንት እስከ ዛሬ። አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

# የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ 1 | ፪ 2 | ፫ 3 | ፬ 4 | ፭ 5 | ፮ 6 | ፯ 7 | ፰ 8 | ፱ 9 | ፲ | 10 |
| ፲፩ | ፲፪ | ፲፫ | ፲፬ | ፲፭ | ፲፮ | ፲፯ | ፲፰ | ፲፱ | ፳ | 20 |
| ፳፩ | ፳፪ | ፳፫ | ፳፬ | ፳፭ | ፳፮ | ፳፯ | ፳፰ | ፳፱ | ፴ | 30 |
| ፴፩ | ፴፪ | ፴፫ | ፴፬ | ፴፭ | ፴፮ | ፴፯ | ፴፰ | ፴፱ | ፵ | 40 |
| ፵፩ | ፵፪ | ፵፫ | ፵፬ | ፵፭ | ፵፮ | ፵፯ | ፵፰ | ፵፱ | ፶ | 50 |
| ፶፩ | ፶፪ | ፶፫ | ፶፬ | ፶፭ | ፶፮ | ፶፯ | ፶፰ | ፶፱ | ፷ | 60 |
| ፷፩ | ፷፪ | ፷፫ | ፷፬ | ፷፭ | ፷፮ | ፷፯ | ፷፰ | ፷፱ | ፸ | 70 |
| ፸፩ | ፸፪ | ፸፫ | ፸፬ | ፸፭ | ፸፮ | ፸፯ | ፸፰ | ፸፱ | ፹ | 80 |
| ፹፩ | ፹፪ | ፹፫ | ፹፬ | ፹፭ | ፹፮ | ፹፯ | ፹፰ | ፹፱ | ፺ | 90 |
| ፺፩ | ፺፪ | ፺፫ | ፺፬ | ፺፭ | ፺፮ | ፺፯ | ፺፰ | ፺፱ | ፻ | 100 |
| ፪፻ | 200 | ፫፻ | 300 | ፬፻ | 400 | ፭፻ | 500 | ፮፻ | 600 | |
| ፯፻ | 700 | ፰፻ | 800 | ፱፻ | 900 | ፲፻ | 1000 | ፳፻ | 2000 | |
| ፴፻ | 3000 | ፵፻ | 4000 | ፶፻ | 5000 | ፷፻ | 6000 | ፸፻ | 7000 | |
| ፹፻ | 8000 | ፺፻ | 9000 | ፻፻ | 10000 | | | | | |

# አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 6ኛ ክፍል